
ክርስቶስን
መከተል
ቴዎዶር ሄ. ኢበልስቲን

# በዚህ
# መጽሐፍ ውስጥ...

ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሐጢአትና ደህንነት የሚያስረዱ ፲፮ ትምህርቶች ተካተዋል። የመጨረሻው ትምህርት አንድ ሰው እንዴት ክርስቲያን ሊሆን እንደሚችል ያብራራል። በዚህ ትምህርት ውስጥ የደህንነት ደረጃዎችንና የሐጢአተኛ ጸሎት ቀርበዋል።

ክርስቲያኖች ያልሆኑትን ሰዎች ከአዳኛቸው ጋር ለማስተዋወቅ ይህንን መጽሐፍ ተጠቀም። አዲስ ክርስቲያኖችም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማገዝ ይህ መጽሐፍ ጠቃሚ መሣሪያ ነው።

መጽሐፉ ቀለል ባለ መንገድ - በሉተዘጋጀ ልጆች፣ ታዳጊ ወጣቶችና ውስብስብ አሳቦችን በቀላሉ ለመረዳት የሚቸገሩ ሰዎች በእጅጉ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ ብለን እናምናለን።

መምህራን እንደ በርሊን፣ ቦስተን፣ ሃኖይ፣ ሆስተን፣ ሳንስ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ማኒላ፣ ሞንትሪል፣ ታይፐይና ታምፓ በመሳሰሉት የዓለም ክፍሎች ይህንን መጽሐፍ ተጠቅመዋል።

ከነዚህ መምህራን ከተሰጡት አስተያየቶች ከሆስተን የተገኘው የሚከተለው ነው፡ «ክርስቲያኖች ምን ያምናሉ? የሚለው መጽሐፍ ለክፍላችን ቀጣዩ መማሪያ ነበር። መጽሐፉን እንዳጠናቀቅን ሁለት ተማሪዎች በክርስቶስ አመኑ።»

እንደ የበርሊን መጋቢ እንደሚሉት፣ «በበርሊን ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት የሚቻልበት ጥሩ መንገድ የቋንቋ ትምህርት ነው... ከቋንቋ ትምህርት በተጨማሪ የኔ ተማሪዎች ክርስቲያኖች ምን ያምናሉ? የሚለውንም መጽሐፍ ተጠቅመዋል። ይህ መጽሐፍ ተማሪዎቹን ከክርስቶስ ወንጌል ጋር በማስተዋወቁ በኩል ጠቃሚ እገዛ አበርክቷል።»

Prepared by:
ANP
PO Box 8974
Addis Ababa
Ethiopia

[illegible]

# ክርስቶስን መከተል

በአፍሪካ ለሚገኙ
አዳዲስ የናዝሬን ቤተክርስቲያን ምእመናን
የተዘጋጀ መሠረታዊ የእምነት መግለጫ (ካቴኪዝም)

ቴዎዶር ፒ. ኤስልስቲን

ትርጉም
ግርማዊ
ሚሊዮን ወልዱ በክረጽዮን

አርማት
ቁምላቸው ፋንታሁን

1995

**Following Jesus Together**
Amharic

ክርስቶስን መከተል

Copyright 2003
First printing 1000 copies.

Translated into Amharic from the English book
Following Jesus Together
Theodore P. Esselstyn

Translators: Girmawi
Million Woldu Bekresion
Editing: Kumlachew Fantahun
Cover art: Roman Tadesse

Prepared by:
ANP
PO Box 8974
Addis Ababa
Ethiopia

# መቅድም

በአፍሪካ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ውስጥ አንድ ሰው የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ለአንድ ዓመት ሙሉ የአባልነት ትምህርት መከታተል እንዳለበት የተረዳሁበትን የቀጠና ጉባኤ አሁንም ድረስ አስታውሳለሁ::
ይህን የተረዳሁት በዚያን ዓመት የቀጠናው ጉባኤ የተወሰኑ አዳዲስ ክርስቲያኖችን የናዛሪን ቤተክርስቲያን አባላት አድርጎ እንዲቀበል ከጠየቅሁ በኋላ ነበር:: በወቅቱ ከቀጠናው ዋና መጋቢያን አንዱ ይህ ሊሆን እንደማይችል ገለጹልኝ:: ለዚህም ምክንያቱ አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነበት ጊዜ አንሥቶ ወደ ጊዜያዊ አባልነት እስኪገባና ትምህርቶቹን አጠናቆ ናዝራዊ እስኪሆን ድረስ አንድ ዓመት ይወስድ ነበር::
ይህም ቅድሚያ በሚሰጣቸው መንፈሳዊ፣ ድርጅታዊና ሥነምግባራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በሦስት ወራት የሚጠናቀቅ ጠበቅ ያለ የክትትል ትምህርት ስለመስጠት እንዳስብ አደረገኝ::
ብረትን መቀጥቀጥ የሚያስፈልገው በጋለበትና ሊተጣጠፍ በሚችልበት ሰዓት ላይ ነው:: የቤተክርስቲያን ዕድገት ጥናቶች እንደሚነግሩን፣ አዳዲስ ክርስቲያኖችን ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለመምራት እጅግ አመቺዎቹ ጊዜያት ክርስቲያኖቹ እጅግ የሚደሰቱባቸውና አዲሱ ሕይወት ቅርጽ መያዝ የሚጀምርባቸው ከደህንነት ቀጥለው የሚገኙ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ናቸው:: ይህ ከተፈጥሯዊ ልደት ጋር ተመሳሳይ ነው:: ልጆችን ከትልቅነታቸው ጊዜ ይልቅ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት በቀላሉ በፈለግነው መልክ ልንቀርጻቸው እንችላለን::
ከተጨማሪ ጥናት እንደተገነዘብሁት፣ ለአሥራ ሁለት ወራት የሚዘልቅ ረዥም ትምህርት አማኙ በአዲስ ልደት ባገኘው ነጻነትና ሰላም ደስ እንዳይሰኝ ከማድረጉም በላይ መነቃቃቱን በመቀነስ ጉልበቱን እንደማያዳክም ተረድቻለሁ::

በአመራር ደረጃ በነዚህ ጉዳዮች ላይ በምንነጋገርበት ወቅት ለአፍሪካ አዳዲስ የናዛሪን አባላት የሚዘጋጀውን ካቴኪዝም (በጥያቄና መልስ የሚቀርብ መንፈሳዊ ትምህርት) በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ የትምህርት አገልግሎት ዳይሬክተር ሆነው ከሚሠሩት ከዶ/ር ቲ. ኤስልስቲን የበለጠ ብቃት ያለው ሰው እንደሌለ ተገነዘብን::
ዶ/ር ኤሰልስቲን ከፍተኛ ብቃት ያላቸው የትምህርት ባለሙያ ከመሆናቸውም በላይ፣ በአፍሪካ ውስጥ ያደጉ በመሆናቸው የአፍሪካን ባሕልና የአኗኗር ስልቶች በማጤን መሠረታዊ ጉዳዮችን መሠረታዊ ካልሆኑት ለመለየት የሚችሉ ሰው ናቸው::
ይህ መጽሐፍ በምእመኖቻችን እጅ ለእግዚብሔር ክብርን እንዲያመጣ ጸሎታችን ነው::
ዶ/ር ሪቻርድ ኤፍ. ዛነር
የአፍሪካ ሪጅን ዳይሬክተር

# ማውጫ

መቅድም ...................................................... 3

የሁለተኛው እትም መግቢያ ...................................................... 5

1. የናዛሪን ቤተክርስቲያን ...................................................... 6
2. ስለ እግዚአብሔር የምናምናቸው ነገሮች ...................................................... 12
3. ሰውና ደህንነቱ ...................................................... 18
4. ደህንነትና መቀደስ ...................................................... 24
5. መጽሐፍ ቅዱስ - የህይወት መመሪያችን ...................................................... 29
6. ናዛሪኖች በጸጋ ያድጋሉ ...................................................... 35
7. የህይወትን ጉዳዮች መጋፈጥ ...................................................... 41
8. ቤተክርስቲያን ...................................................... 47
9. የናዛሪን ቤተክርስቲያን ታሪክ ...................................................... 53
10. የአፍሪካ ክልል ...................................................... 59
11. ናዛሪኖች አብረው ይሠራሉ ...................................................... 65
12. የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ...................................................... 70

# የሁለተኛው እትም መግቢያ

የመጀመሪያው እትም ከተጻፈ በኋላ በአፍሪካ ክልል በምትገኘው የናዛሪን ቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ዕድገቶች ታይተዋል:: ዓለምአቀፋዊቷም ቤተክርስቲያን እንዲሁ አድጋ ተስፋፍታለች:: ይህም ብዙዎች አሀዛዊ መረጃዎች እንደገና እንዲሻሻሉና ግልጽ ያልነበሩት አንዳንድ አሳቦች ይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ አስፈላጊ አድርጓል::

ይሁንና፣ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ለአዳዲስ አባላት መጋቢው ለሚሰጠው ትምህርት የመማሪያ መጽሐፍ ሆኖ ማገልገል ነው:: ትምህርቱ ለ12 የአርባ አምስት ደቂቃ ትምህርቶች የተዘጋጀ ነው:: መጋቢው በሳምንት አንድ ትምህርት እያስተማረ በሦስት ወራት ሊፈጽም ወይም በአንድ ሳምንት ከአንድ የሚበልጡ ትምህርቶችን በማስተማር ለክፍለጊዜው የሚያስፈልጉትን ሳምንታት ሊያሳጥር ይችላል::

የዚህ መጽሐፍ ዋና አሳብ አዳዲስ አባላት ቤተክርስቲያንን ከማወቅ አልፈው፣ እንዴት መኖር፣ በፍሬያማ መልኩ መሥራትና በቤተክርስቲያን ዕድገት ውስጥ መሳተፍ እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ማገዝ ነው:: የናዛሪን ቤተክርስቲያን እምነት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተለመደው መልኩ ተካቷል:: ስለ ቤተክርስቲያኒቱ ታሪክ አጠር ያለ ትምህርት መስጠቱ አዲሱ አባል የቤተክርስቲያኒቱን ዋና ዋና አስተምህሮዎች ምንጭና ከሌሎች አብያተክርስቲያናት ጋር ያላትን ግንኙነት እንዲገነዘብ ይረዳዋል:: ናዛሪኖች በአፍሪካ የሚጋፈጧቸው ነገሮች፣ ማለትም ቤተክርስቲያኒቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላት ማኅበራዊ አቋም፣ የአምልኮ ስልትና የቤተእምነት አደረጃጀትም ተብራርተዋል:: እኛ የናዛሪን ቤተክርስቲያን አማኞች እግዚአብሔር በዓለም ለውጥ እንድናመጣ ይጠብቃል ብለን እናምናለን:: ሕይወታችንን በመንፈስ ቅዱስ ሀይል እየኖርን ክርስቶስን ልንከተልና ተባብረን ልንሠራ ይገባል:: ክርስትናን መረዳት ያለብን የእምነቶች ክምችት አድርገን ሳይሆን የአምንታዊና ድልነሺ አኗኗር አድርገን ነው:: ተልዕኮአችን ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ህዝብ ነው::

ይህ መጽሐፍ አፍሪካ ውስጥ የምትገኘው የናዛሪን ቤተክርስቲያን ክልላዊ አማካሪ ኮሚቴ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት የተዘጋጀ ነው:: በሥራው ውስጥ ብዙ ግለሰቦች መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመምረጥና በመገምገም፣ በማረምና ለህትመት በማዘጋጀት እገዛ አድርገዋል::

ዶ/ር ቴዎዶር ፒ. ኤስልስቲን
የትምህርት አገልግሎቶች ዳይሬክተር

# ምዕራፍ 1
# የናዛሪን ቤተክርስቲያን

## የናዛሪን ቤተክርስቲያን ማናት?

የናዛሪን ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን ለማምለክ፣ ለማገልገልና ይበልጥ እርሱን ለመምሰል በአንድነት የተጣመሩና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ቤተሰብ ነች።

የናዛሪን ቤተክርስቲያን በዓለም ከ110 በሚበልጡ አገሮች ውስጥ ህብረቶችን መሥርታለች። የቤተክርስቲያኒቱ ዓለምአቀፍ ማዕከል በአሜሪካ ውስጥ ሚዚሪ ካንሳስ ከተማ ውስጥ ይገኛል። በ1985ቱ ጠቅላላ ጉባኤ ቤተክርስቲያኒቱ በአሥራ አምስት የተለያዩ ክልሎች እንድትከፋፈል ተወስኗል። ከነዚህም መካከል ከሰሃራ በረሃ በታች የሚገኘው የአፍሪካ ክፍል አንዱ ነው።

## ናዛሪኖች የሚባሉ ሰዎች እነማናቸው?

የናዛሪንን ቤተክርስቲያን የሚቀላቀል ግለሰብ ሁሉ ደህንነትን እንዳገኘና መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ ውስጥ እንዲያድር የሚሻ መሆኑን ይመሰክራል። በተጨማሪም፣ ተልእኮአችንን በጋራ እንወጣ ዘንድ ቤተክርስቲያንን በሚችለው ዓቅም ሁሉ ለመደገፍ ፈቃደኛ መሆኑን ይመሰክራል።

ይህም ናዛሪኖች እግዚአብሔር ከፈጸሟቸው ሐጢአቶች ይቅር እንዲላቸው እንደጠየቁት ያስረዳል። ከተሳሳተው መንገድ ተመልሰው ትክክለኛውን አካሄድ ለመከተል በመትጋት ላይ ናቸው። የእግዚብሔር መንፈስ ቅዱስ ሕይወታቸውን በመቆጣጠር ወደ አዳኒና ፍሬያማ ሕይወት እንዲመራቸው ይፈልጋሉ። ይህም ራስን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠትንና መንፈስ ቅዱስ የኛን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እንዲያስማማ መፍቀድን ይጠይቃል።

## የናዛሪኖች ባሕርያት ምንድናቸው?

በናዛሪን ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ (መምሪያ) ውስጥ የሚገኙ አጠቃላይ ደንቦች ስለ ናዛሪኖች ሦስት መሠረታዊ ባሕርያት አጭር መግለጫ ይሰጣሉ። እነዚህም፣

1. ክፉ መራቅ
2. መልካምን ማድረግና
3. ከቤተክርስቲያን ጋር የተሟሟቀ ህብረት እያደረጉ መኖር ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ (ገላትያ 5:22) እኛ እጅግ ጠቃሚዎች ናቸው የምንላቸውን ባሕርያት በመለየት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች መሆናቸውን

ያስረዳል:: እነዚህም፣ «ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነትና ራስን መግዛት» ናቸው:: እነዚህ ነገሮች የአንድን ሰው ማንነት ይገልጻሉ::
አንድ ሰው የሚያከናውናቸው ተግባራት የሚመነጩት ከማንነቱ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እኛ አገልጋዮች መሆናችንን በተደጋጋሚ ያስረዳል:: ፊልጵስዩስ 2:1-11 የክርስቶስን አሳብ እንድንይዝ ያሳስበናል:: ይህም እግዚብሔርንና ሰዎችን የማገልገል ፍላጎት ነው:: ክርስቶስ ራሱ ችግርተኞችን በምንረዳበት ጊዜ እርሱን እያስገልን መሆናችንን አስረድቷል (ማቴዎስ 25:31-46)::
አብረን በምንሠራበት ጊዜ ለእግዚአብሔር በምንሰጠው ምስጋናና አምልኮ፣ እንዲሁም ለሰዎች በምናከናውናቸው አገልግሎቶች ከፍተኛ ውጤት እናሳያለን:: ምእመናን ሁሉ በችሎታቸው፣ በገንዘብ ዓቅማቸው እየተባበሩና ጌታን በህብረት እያመለኩ በአንድነት ሊሠሩ ይገባል::

## የናዝሪኖች ዓላማ ምንድነው?

ክርስቲያኖች በውስጣቸው በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሐጢአትን የሚረታ ውጤታማና አዎንታዊ ሕይወት ሊኖሩ እንደሚችሉና እንደሚገባ የሚያስረዳውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ለማስተማር እግዚአብሔር የናዛሪንን ቤተክርስቲያን እንዳስነሣት እናምናለን:: ጆን ዌስሊ ይህንን የሕይወት አቅጣጫ «ክርስቲያናዊ ፍጹምነት» ሲል ጠርቶታል:: ተስፋን፣ ዕርቅን፣ ስምምነትንና ህብረትን የሚያመጣው አዎንታዊ መልእክት ነው:: ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ መልእክት በግለሰቡና በእግዚብሔር መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ያተኩራል:: ይህ ከእግዚብሔር ጋር የሚኖረን ግላዊ ግንኙነት ጤናማ ቤተሰባዊ፣ የጉርብትናና ማህበራዊ ግንኙነቶች እንዲኖሩን ያደርጋል:: ተገቢና ጤናማ የግል አመለካከት እንዲኖረንም ያግዛል::

## ናዛሪኖች የቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጁት ለምንድነው?

የናዛሪን ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ የተዘጋጀው በቤተክርስቲያኒቱ ጠቅላላ ጉባኤ ነው:: በየአራት ዓመቱ ከሚደረግ ጠቅላላ ጉባኤ በኋላ አዲስ የመተዳደሪያ ደንብ እትም ይወጣል:: በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ አጭር ታሪካዊ መግለጫ፣ እምነት፣ ጉባኤው የተስማማባቸው ደንቦችና ሰዎችን በአባልነት ለመቀበል የሚያስችሉ መመዘኛዎች ተካተዋል:: መተዳደሪያ ደንቡ ስለ ቅዱስ ቁርባን፣ ጥምቀትና ሌሎች የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች የሚያብራራ ክፍል ያለው ሲሆን፣ ወደ አገልግሎት ስለ መግባትም የሚያስረዳ ሌላ ክፍል አለው:: የመተዳደሪያ ደንቡ አብዛኛው ክፍል በሦስቱ የአደረጃጀት ደረጃዎች (ማለትም በአጥቢያ፣ በቀጠናና በጠቅላላ ቤተክርስቲያን ደረጃዎች) ስለሚካሄዱ አስተዳደራዊ ደንቦች ያብራራል::

በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት መሥራቱ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ናዛሪኖች ሥራዎቻቸውን እንዲያስተባብሩ ይረዳቸዋል። ይህም የክርስቶስ አካል ለሆነችው ቤተክርስቲያን ተገቢ ነው።

## የናዛሪን ቤተክርስቲያን እንዴት ተመሠረተች?

የናዛሪን ቤተክርስቲያን በይፋ የተመሠረተችው በ1908 በፓይለት ፖይንት፣ ቴክሳስ ነበር። ይህች ቤተክርስቲያን ተመሳሳይ የቅድስና አኗኗር ገደድ የነበራቸው አያሌ የሰሜን አሜሪካ አብያተክርስቲያናት ውህደት ውጤት ነች።

የጆን ዌስሊና የቀደምት ሜተዲስት አማኞች አገልግሎት በአሥራ ስምንተኛው ክፍለዘመን በአውሮፓና አሜሪካ የነበረችው ቤተክርስቲያን መሠረታዊ የክርስቲያን መመዘኛን በማጤን መንፈስ ቅዱስ የምእመናንን ሕይወት መቆጣጠር እንዳለበት እንድትገነዘብ አነቃቃት። ይህም እንቅስቃሴ በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለዘመን በአሜሪካና በእንግሊዝ በተከሰቱት ታላላቅ የቅድስና መነቃቃቶች ተጠናክሮ መልክ ያዘ። እነዚህ አብያተክርስቲያናት እርበርሳቸው ህብረት ለማድረግ በመፈለጋቸው ቤተእምነቶችንና ማህበራትን ለማቋቋም ተነሣሡ። በዚህም ጊዜ ሁለት የተራራቁ ተቃራኒ አሳቦች ቀረቡ። አንደኛው ወገን በመንፈሳዊ ስጦታዎች ውጫዊ መገለጫነት ላይ በማተኮር ለጴንጠቆስጠያዊ እንቅስቃሴ መሠረት ጣለ። ሌላኛው በውስጣዊ ለውጥ አስፈላጊነት ላይ በማተኮር ለቅድስና ቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ፈር ቀደደ። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ የናዛሪን ቤተክርስቲያን በቁጥር ትልቋ ቤተእምነት ነበረች። በዓመታት ውስጥ ከአሥራ ስድስት የሚበልጡ ማህበራት ወይም ቤተእምነቶች ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር ተዋህደዋል። የናዛሪን ቤተክርስቲያን የሚለው ስም በሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ የነበረችው ማህበረምእመናን ስያሜ ነበር። የዚህች ማህበረምእመናን መሪ ዶ/ር ፊንሐስ ኤፍ. ብረሲ ሲሆኑ፣ በመመጀመሪያዎቹ ውህደቶች ላይ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

## የቤተእምነቱ መለያ ባህርያት ምን ምንድናቸው?

የናዛሪን ቤተእምነት የሚለዩ አያሌ ባህርያት አሉ። የመጀመሪያው በቅድስና ላይ ትኩረት መስጠቱ ነው። ይህም በእግዚብሔር መንፈስ ቅዱስ ሀይል መኖርን የሚያመለክት ነው። ሁለተኛው ወደ ዓለም ሁሉ እንድንሄድ የሚጠይቀው የታላቁ ተልዕኮ አስገዳጅ መልእክት ነው። ይሄኛው ገጽታ ለቅድስና አኗኗር ወሳኝ በመሆኑ ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር የተዋሃዱ ቤተእምነቶች ሁሉ በሌሎች አገሮች ውስጥ የሚያገለግሉ ሚሲዮናውያን አሏቸው።

ስለዚህም፣ ገና ከመጀመሪያው ጀምሮ የሚሲዮን ክፍል ቅድሚያ ተሰጥቶት እናገኛለን። ሦስተኛው የወጣቶች ትምህርት ነው። አብዛኞቹ ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር የተዋሃዱት አብያተክርስቲያናት የመጽሐፍ ቅዱስ

ኮሌጆች ብቻ ሳይሆኑ እንደ ሊብራል አርትስ (ሁብረተሰባዊና ተፈጥሮአዊ ሳይንስ የሚያስተምሩ) ዓይነት ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ነበሯቸው። አራተኛው ለየት ያለ የማህበረምእመናዊና መዋቅራዊ አስተዳደር ቅይጥነት ነው። ይህም ቤተክርስቲያኒቱ እንደ አንድ አካል በዓለም ሁሉ ልትደርስ የምትችልበትን አስተዳደራዊ መዋቅር ሰጥቷታል።

## ናዛሪኖች የሚያመልኩት እንዴት ነው?

በዓለም ዙሪያ የሚገኙ የናዛሪን አብያተክርስቲያናት የሚያካሂዷቸው የአምልኮ ፕሮግራሞች የተለያዩ ናቸው። ልዩነቶቹም በቋንቋ፣ በልማዶች፣ በአለባበስ፣ በመዝሙር፣ በቀለም፣ በምጽዋቶች፣ በአሰባበክ ስልቶች፣ በሕንጻ ስልቶች፣ በመድረክና በምእመናን አቀማመጥ ሊገለጹ ይችላሉ።
ይህም ሆኖ ሁላችንንም የሚያስተሳስሩ የጋራ ነጥቦች አሉን። የእግዚአብሔር ቃል ስብከት ሁልጊዜም የአምልኮ ፕሮግራሙ እምብርት ነው። ይህንን አሳብ ለማገላት ስንል ብዙውን ጊዜ ምስባኩን ከመድረኩ ማዕከል ላይ እናቆመዋለን። ስብከቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን እንዳለበት እናምናለን። ሊታወጅ የሚገባው የእግዚአብሔር ቃል ነው። በዕለታዊ ሕይወታችን እንዴት መመላለስ እንዳለብን የሚያስተምረን የእግዚአብሔር ቃል ነው።
የናዛሪን ቤተክርስቲያን የአምልኮ ፕሮግራሞች የወንጌል ስርጭት ትኩረት የሚታይባቸው ናቸው። ፕሮግራሞቹ በአምላኪዎቹ መለወጥና ዕድገት ላይ አፅንኦት ይሰጣሉ። በዚህም ምክንያት መሠውያው ሁልጊዜም ክፍት ነው። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝተን ለሐጢአታችን ይቅርታንና ደህንነትን የምናገኝበት ወይም ከእግዚብሔር ጋር በነጻነት ልንነጋገር የምንችልበት ስፍራ በመሆኑ ነው። ስብከቱና መዝሙሮቹ አምላኪው ይህንን እርምጃ እንዲወስድ ለማነቃቃት ታቅደው የሚዘጋጁ ናቸው። ዓላማውም በክርስቲያኑ ዕድገት ውስጥ አዎንታዊ ለውጥን ማምጣት ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ በትክክል ለመኖርና ለመጪውም ዓለም ለመዘጋጀት እንፈልጋለን። ለዚህም የምእመናን እገዛ ተገቢውን ድጋፍ ያስገኝልናል።
ጸሎት፣ ውዳሴ፣ ደስታ፣ ምስጋናና ምስክርነት ሁሉ የአምልኮ ፕሮግራሙ አብይ አካላት ናቸው። የመዝሙሮችና የአዝማቾች ዝማሬ፣ እንዲሁም እግዚአብሔር በሕይወታችን ያደረገውን መመስከር የእያንዳንዱ የአምልኮ ፕሮግራም ዋነኛ ክፍል ነው። የአምልኮ ፕሮግራሙ በተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች የሚታገዝ ሲሆን፣ ምንም ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያ የሌላቸው ብዙ የአፍሪካ አብያተክርስቲያናት በድምፃቸው ብቻ ያዜማሉ።
የናዛሪን ቤተክርስቲያን አምልኮ ሁልጊዜም በመስጠት ይለያል። ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነ እናምናለን። እኛ የሀብቱና የፍጥረታቱ ተንከባካቢዎች ነን። ይህንንም የምንገልጸው ከምናገኘው ገቢ ሁሉ (ገንዘብ፣ እህል ወይም ማንኛውም ነገር) አንድ አሥረኛውን ለእግዚአብሔር

በመስጠት ነው። ይህ የአሥራት መርህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በግልጽ ሁኔታ የተመሠረተ ሲሆን (ዘሌዋውያን 27፣ ዘዳግም 12፣ ሚልክያስ 3)፣ እስራኤላውያን ግን ከአምልኮ ይልቅ ወደ ሕጋዊ መመዘኛነት ለወጡት (ማቴዎስ 23:23)። ክርስቶስ አንድ አሥረኛው ብቻ ሳይሆን ያለን ንብረት ሁሉ የእግዚብሔር መሆኑን በመግለጽ መሠረታዊውን መርህ እንደገና አጽንቶታል (ማርቆስ 8:34-38፣ ማቴዎስ 25:14-30)። ክርስቶስ ክርስቲያኖች ሁሉ መስቀሉን በመሸከምና እርሱ የጀመረው የማዳን ሥራ ተካፋይ በመሆን ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ለርሱ አሳልፈው እንዲሰጡ ይፈልጋል።

ናዛሬኖች ክርስትና ምትሃታዊ ሃይማኖት ነው የሚል መልእክት ሊያስተላልፉ የሚችሉ ትርጉመ-ቢስ ሥርዓቶችን ከማስተናገድ ይቆጠባሉ። የቤተክርስቲያን አልባሳት እምብዛም ከአገልግሎት ላይ አይውሉም። የትኛው ዓይነት ልብስ ወይም ሥርዓት ሰውን ሊቀድስ አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ለእግዚብሔር ከሁሉም የሚሻለው ልብስና ትርጉም ያለው መሥዋዕት የልብና የሕይወት ቅድስና ነው። ሻማዎች፣ ዕጣኖች፣ መስቀሎች ወይም ሥርዓታዊ ድግግሞሾች ከአምልኮ ጋር ተዛማጅነት የላቸውም። አምልኮ የህብረት፣ የማዳመጥ፣ የዕድገት፣ የምልጃና የውዳሴ ጊዜ ነው። በአምልኮ ውስጥ ስሜት ብቻ ሳይሆን ሁለንተናችን መሳተፍ አለበት። አንዳንድ ጊዜ ትርጉም በማይሰጡ ቃላት አማካኝነት የሚገለጽ ከልክ ያለፈ ስሜት መንፈሳዊነት ሳይሆን፣ የሰው ልጅ ባህርይ ደካማነት ምልክት ነው።

ለማጠቃለል ያህል፣ ጥሩ የናዛሬን አምልኮ አማኞች ከእግዚብሔር ጋር የሚገናኙበት፣ ለርሱም ያላቸውን ውዳሴ፣ ፍቅርና መስጠት የሚገልጹበትና አለማውያን ደግሞ እግዚብሔርን አግኝተው ወደርሱ የሚመለሱበት ነው። አማኞች በዕለታዊ ሕይወታቸው ይበልጥ እርሱን እየመሰሉ ይሄዳሉ።

## የናዛሬኖች እምነቶች ምን ምንድናቸው?

በናዛሬን ቤተክርስቲያን የመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ያላቸው አሥራ አምስት የእምነት አንቀጾች አሉ። አጭር የእምነት መግለጫ አንቀጽም አለ።

1. በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንድ አምላክ እናምናለን።
2. በእስትንፋስ-እግዚብሔር የተሰጡት የብሉይና አዲስ ኪዳና መጻሕፍት ለእምነትና ለክርስቲያናዊ አኗኗር የሚጠቅመውን እውነት ሁሉ እንደያዙ እናምናለን።
3. ሰው ከወደቀ ተፈጥሮ ጋር ስለተወለደ፣ ባለማቋረጥ ወደ ክፉት እንደሚያዘነብል እናምናለን።
4. እስከ መጨረሻው ድረስ ንስሐ ለመግባት እምቢ የሚሉ ሰዎች ተስፋ በሌለው ሁኔታ ለዘላለም እንደሚጠፉ እናምናለን።

5. የክርስቶስ ስርየት ለሰው ልጆች ሁሉ ስለሆነ፣ ንስሐ ገብቶ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ እንደሚጸድቅ፣ ዳግም እንደሚወለድና ከሐጢአት አገዛዝ እንደሚድን እናምናለን::
6. በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ዳግም ከተወለዱ በኋላ አማኞች ሙሉ በሙሉ መቀደስ እንዳለባቸው እናምናለን::
7. መንፈስ ቅዱስ ለአዲስ ልደትና ለአማኞች ሁለንተናዊ ቅድስና ምስክርነት እንደሚሰጥ እናምናለን::
8. ጌታችን ዳግም እንደሚመለስ፣ ሙታን እንደሚነሡና የመጨረሻው ፍርድ እንደሚሰጥ እናምናለን::

## የናዛሪኖች አኗኗር እንዴት ያለ ነው?

ናዛሪኖች ክርስትና የአኗኗር ዘይቤ እንደሆነ ይገነዘባሉ:: ይህንን የአኗኗር ስልት ክርስቶስ «ፍቅር» በሚል አንድ ቃል ጠቅለል አድርጎ ገልጾታል:: ክርስቶስ በዮሐንስ 14:15፣ «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ» ብሏል:: እግዚአብሔርን መታዘዝ፣ አካሉ ለሆነችው ቤተክርስቲያን ታማኝ መሆን፣ ለራሳችን፣ ለቤተሰባችንና ለአገራችን ሃላፊነትን መውሰድ ከዚያ ፍቅር የሚመነጩ ነገሮች ናቸው::

በተግባራዊ መልኩ ሲተረጎም ይህ ናዛሪኖች በመደበኛነት የቤተክርስቲያንን አምልኮ እንደሚካፈሉ፣ ጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንደሚያካሂዱ፣ ብሎም በአጥቢያ ቤተክርስቲያን የአገልግሎት ስፍራ እንደሚሹ ያሳያል:: በተጨማሪም፣ ናዛሪኖች በሥራ ቦታቸው፣ በማህበረሰቡ ውስጥና በአገራቸው ታማኝ አገልጋዮች ለመሆን ይሻሉ:: ደህንነት መልካምን ሕይወት እንድንኖር የሚያስችለን የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ እንደሆነ ያውቃሉ:: ደህንነት በመልካም ሥራ፣ የቤተክርስቲያን አባል በመሆን ወይም በመጠመቅ አይገኝም::

የናዛሪኖች የአኗኗር ስልት በአሁኑ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር መመሳሰስና ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር ለመመሳሰስ የመናፈቅ ሕይወት ነው::

## ምዕራፍ 2
# ስለ እግዚአብሔር የምናምናቸው ነገሮች

## ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ከየት ይጀምራል?
«ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና» (ዕብራውያን 11:6)። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት የሚጀምረው በርሱ ካመንንበት ጊዜ አንሥቶ ነው። ይህም የእምነት ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር ህልው እንደሆነ፣ ለኛ እንደሚገደው በማመን እንጀምርና በዚያው እምነት ላይ ተመሥርተን ተግባራዊ እርምጃዎችን እንወስዳለን። ናዛሬኖች ስለ እግዚአብሔር ባህርያት የምናምናቸው ነገሮች *በመምሪያው* (መተዳደሪያ ደንቡ) ውስጥ በሚገኙ የመጀመሪያዎቹ ሦስት «የእምነት አንቀጾች» ውስጥ ተዘርዝረዋል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከቀረበው ማብራሪያ ጋር እነዚህን አሳቦች *ከመምሪያው* ማንበብ ይኖርብሃል።

## በአንድ አምላክ እናምናለን?
ዘዳግም 6:4-5 እንደሚለው፣ «እስራኤል ሆይ፣ ስማ፣ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጽምም ነፍስህ በፍጹምም ሀይልህ ውደድ» ያለው አንድ አምላክ ብቻ ነው። ሌሎች አማልክት ሁሉ በሰዎች አእምሮና እጆች የተሠሩ ናቸው። ስለሆነም፣ እንደ እግዚአብሔር ዓይነት የአምላክነት ባህርይ የላቸውም።

## የእግዚአብሔር ወሰኖች ምንድናቸው?
እግዚአብሔር ወሰን የለውም። እግዚአብሔር ከቶውንም አይሞትም። እርሱ ከምንገነዘበው ነገር ሁሉ በላይ ግዙፍ፣ ኃያል እና ታላቅ ነው። እግዚአብሔር በኛ ውስን አጽናፈዓለም የተገደበ አይደለም። ይልቁንም ለአጽናፈዓለሙ ዳርቻ፣ መዋቅርና ተግባራትን በፈጣሪነት ጥበቡ አብጅቷል። እግዚአብሔር ያልተገደበ መሆኑንና ከአጽናፈዓለማችን እንደሚልቅ ለመግለጽ ወሰንየሌለው እና የላቀ የሚሉትን ቃላት እንጠቀማለን።

## እግዚአብሔር ከዓለም ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት አለው?
እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው። የፈጠራ ተግባሩም የዓለማችን ገጽታ ሁሉ የሚንቀሳቀስበትን ህግ አስገኝቷል። እግዚአብሔር ዓለምን እንዲሁ ሳይተው በጥበቡ ታላቅነት ማስተዳደሩን ቀጥሏል። እግዚአብሔር

ሰዎች ዓለምን ይንከባከቡ ዘንድ ሃላፊነት ሰጥቷቸዋል (ዘፍጥረት 1:28)። ክርስቶስ ይህ ያሁኑ ዓለም እስኪያበቃ ድረስ ይህ ሕግ እንደሚቀጥል ተናግሯል (ማቴዎስ 5:18)።
እግዚአብሔር በቀጣይነት በዓለም ውስጥ የሚያከናውናቸው ተግባራት ስለሥራው የተለያዩ ገጽታዎች ብዙ ማብራሪያዎችን ይጠይቃሉ። እግዚብሔር አፍቃሪና መሐሪ አምላክ ነው። እርሱ በቅንነት የሚፈርድ ቸር አምላክ ነው። የተሳሳተ ተግባር ሲፈጸም ይቆጣል። እርሱ የሚወዳቸውን ያርማቸዋል። ሌሎችን አማልክት ስንከተል ይቀናል። እግዚብሔር ስናጠፋ የሚይዘን ፖሊስ ሳይሆን መልካም ጓደኛ ነው። በልባችን ውስጥ ማደሪያውን ሲሠራ የምህረትን መቀመጫ እንጂ የፍርድን ችሎት አይመሠርትም። እርሱ የሚመጣው እርዳታንና ጸጋን ለማምጣት ነው።
እግዚአብሔር እኛን የፈጠረን የባሮች እጥረት ስለነበረበት አይደለም። ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 17:24-25 እንደገለጸው እግዚአብሔር ምንም ነገር አይጎድለውም። እርሱ ያለኛ አንዳች ነገር የሚጎድለው ሳይሆን በራሱ ሙሉ ነው። እግዚአብሔር የሚፈጥረው የመስጠት፣ የማፍቀር፣ የመገንባት፣ የመፍጠር ባሕርይ ያለው አምላክ ስለሆነ ነው። እርሱ አጥፊ፣ ጎጂ፣ እኛን ማስጨነቅ የሚወድ አምላክ አይደለም። ከኛ ጋር ህብረት ማድረግን ይወዳል።

## እግዚአብሔር ምን ይመስላል?
እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ይናገራል። ይህ የርሱ ቀዳሚ ባህርይ ነው። በመሠረቱ ይህ ማለት እውነትን፣ ምህረትንና ፍቅርን በሁሉም የሕይወቱ አቅጣጫዎች አዋህዶ የያዘ ማለት ነው። ቁጣን፣ በቀልንና ፍርድን አስፈላጊ በሚሆኑበት ጊዜ ይጠቀምባቸዋል። እግዚአብሔር ሰው ከቅድስናው እንዲካፈል ቢፈልግም፣ የሰውን ጥፋተኝነት ያውቃል። ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ እንመርጥ ዘንድ ሕይወቱን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ሰጥቷል። ፍቅሩ፣ ጽድቁና ምህረቱ የሚመነጩት ከቅድስናው ነው። እግዚአብሔር ምህረቱንና ፍቅሩን የሚገልጸው ፍቅሩና እውነቱ፣ ጽድቁና ምህረቱ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን ውስጥ እንዲያድሩ በማድረግ ነው።

## ክርስቶስ እግዚአብሔር አባታችን እንደሆነ ገልጾአል
ክርስቶስ በማቴዎስ 6:9-13 ለደቀመዛሙርቱ የአባታችን ሆይ ጸሎት ባስተማረ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር እጅግ ሥዕላዊ አሳብ ሰጥቶናል። እግዚአብሔር አባታችን ነው። ይህ ሥዕል እግዚአብሔር ለኛ እንደሚጠነቀቅና የቤተሰቡ አባል እንዳደረገን ያመለክታል። እርሱ የበላያችንና ጌታችን ሲሆን፣ ፍላጎቶቻችንን፣ ህልሞቻችንንና ችግሮቻችንን ይዘን የምንሄደው ወደርሱ ነው። እርሱ ለራሳችን

ሃላፊነትን በመውሰድ እንድናድግ ይጠብቃል። ይህም አባት ከልጆቹ እነዚህን እንደሚጠብቅ ዓይነት ነው።

## እግዚአብሔር እንዴት ሦስትና አንድ ሊሆን ይችላል?

ይህ ምሥጢር ነው። ይህ እግዚአብሔር እኛ ከምንኖርባት አጽናፈዓለም በላይ በመሆኑ እኛ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የማንችለው እውነት ነው። እግዚአብሔር አንድ መሆኑን ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ይገልጽልናል (ለምሳሌ፣ ዘዳግም 6:5።) ። ነገር ግን ራሱን በሦስት አካላት ለመግለጥ ፈልጓል። እርሱ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህንን እውነት አዕንተን የምንናገረው መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ አምላክ እንደሆነ (ዮሐንስ 1 እና 17)፣ መንፈስ ቅዱስም አምላክ እንደሆነ ስለሚናገር ነው (ሮሜ 8:1-27፣ ኤፌሶን 3:14-21)። በዘጸአት 3 እግዚአብሔር ስሙን ለሙሴ በገለጸ ጊዜ፣ «እኔ እኔ ነኝ» ብሏል። ለዚህ ምናልባትም ምሳሌ መጠቀሙ ሳይረዳ ይቀርም። ሙዝ በምትልጥበት ጊዜ አንድ ሙዝ እንደሆነ ትናገራለህ። ነገር ግን የሙዙን ጫፍ ይዘህ ጨመቅ ብታደርግ ሦስት ነገሮችን ታገኛለህ (ልጣጩ፣ የሚበላው ክፍልና ፍሬው መሆኑ ነው።) ሙዙ አንድ ቢሆንም ሦስት ሆኖ ታገኘዋለህ። እያንዳንዱ ክፍል ልክ እንደሌላው ነው። ከሦስቱም የሙዝ ክፍሎች የምናገኘው ጣዕም ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር ሙዝ እንዳልሆነ እናውቃለን። ነገር ግን እርሱ በሦስትነትና በአንድነት የተገለጸ አምላክ ነው። ሦስቱም አካላት በተናጠልም ሆነ በአንድነት አንዱን አምላክ ይወክላሉ። ለዚህ ነው ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ተመሳሳይ ግንኙነት እንዳለን የሚያስረዱት። ሁለቱም እንደ አብ ሁሉ አምላክ ናቸው (ሮሜ 8:9-11፣ ገላትያ 2:19-3:14)።

## ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው?

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ እንክብካቤና ምሕረት የሚያሳይ ሕያው መግለጫ ነው። ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ክርስቶስ ፈጣሪ እንደሆነ በመግለጽ፣ «ቃልም ሥጋ ሆነ» ይላል። ይህም ክርስቶስ ሰውና አምላክ የመሆኑን ተአምር ያሳያል። ክርስቶስን አምላክና ሰው ብሎ ለሁለት መክፈል አይቻልም። ነገር ግን እርሱ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው። ይህም ልናብራራ የማንችለው የተገለጠ እውነት ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ችግሮቻችንን፣ ውስንነቶቻችንንና ሥቃዮቻችንን እንደሚሸከም፣ ሐጢአቶቻችንን በራሱ ላይ እንዳኖረና የኛኑ ዓይነት ሞት ተሠቃይቶ እንደሞተ እናውቃለን።

## ክርስቶስ ለሰው ልጅ ምን አደረገ?
እኛ ሕይወትን እናገኝ ዘንድ ክርስቶስ መከራ ተቀብሎ ሞቷል። ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብና ፍቅሩን እና ሕይወቱን እንዲካፈል ለማድረግ እግዚአብሔር ሰው ሆነ። ዮሐንስ 3:16 ይህንን ዓላማ ስለሚገልጽ ምናልባትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሁሉም በላይ የታወቀ ጥቅስ ሳይሆን አይቀርም። በርሱ የሚያምኑ ሰዎች የሕይወት እንጂ የሞት ተካፋይ እንዳይሆኑ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጣ። ክርስቶስ በተግባሩና በትምህርቱ ሕይወትን፣ ፍቅርን፣ እውነትንና ተገቢውን አኗኗር እንድናገኝ አድርጓል። እርሱ እንዳለው፣ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ። በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» (ዮሐንስ 14:6)።

## ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን አለን?
አዎ፣ እርሱ ዛሬም አለ። እርሱ ሐጢአትን ከቅጣቶቹ ሁሉ ጋር ድል ነስቷል። ክርስቶስ ለኛ ሊማልድና መንፈስ ቅዱስን ሊልክልን ወደ ሰማይ ዐርጓል። ከዚህም የተነሣ ደህንነትን ሊሰጠን ችሏል። ሞት ክርስቶስን ሊያጠፋው አልቻለም። እግዚአብሔር ከሞት አስነሥቶታልና (ፊልጵስዩስ 2:9)። ይህም የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ነው። ከዚህም የተነሣ አንድ ሰው ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር በሚሰጥበት ጊዜ እግዚአብሔር ይህንን ሰው በድንቅ ሁኔታ ለውጦ ለብዙዎች በረከት ያደርገዋል።

## ክርስቶስ አሁን ለኛ ምን እያደረገ ነው?
ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ሆኖ ባለማቋረጥ ይማልድልናል። እርሱ ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር ሊቀካህናታችን ነው። በዚህ ዓይነት ሁልጊዜም ለኛ የሚበጀንን ያደርጋል።

## መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው?
አዎ፣ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሆነ አሀዱ-ሥሉስ አምላክ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል። ሮሜ 8:1-27 እና ኤፌሶን 3:14-21 መንፈስ ቅዱስም አምላክ እንደሆነ ያሳያሉ። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የሚኖርና አብሮን የሚሠራ የእግዚአብሔር አካል ነው።

ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ ይመጣ ዘንድ ወደ አብ መመለሱ አስፈላጊ እንደሆነ ተናግሯል (ዮሐንስ 16:7-14)። አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በራሱ ምርጫ ሰው በመሆን ስለተወሰነ፣ በአንድ ጊዜ ከሰዎች ሁሉ ጋር ለመሆን አይችልም ነበር። መንፈስ ቅዱስ ግን በዚህ መንገድ የተወሰነ አይደለም። እርሱ በሁሉም ስፍራ የሚገኙትን ሰዎች

ሊያገለግል ይችላል:: መንፈስ ቅዱስ በበዓለሃምሳ ቀን ወደ ክርስቶስ ተከታዮች ላይ በመምጣቱ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አዲስ ግንኙነት ተጀመረ::
የዚህ አዲሱ ግንኙነት እምብርት ቤተክርስቲያን (አማኞች) ነች:: በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ቤተመቅደሱን በሕዝቡ መካከል በማድረግና መንፈሱን በቤተመቅደሱ ውስጥ በማኖር ለቤተክርስቲያን መሰናዶ እንዳደረገ እንመለከታለን:: የሐዋርያው ጳውሎስና የሐዋርያው ዮሐንስ ጽሑፎች እንደሚያስረዱት፣ ይህ መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ እንደሚያድር የሚያሳይ ምሳሌ ነበር (1ኛ ቆሮንቶስ 3:16፣ ዮሐንስ 14-16)::

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንድነው?

መንፈስ ቅዱስ በሰዎች መካከል የሚሠራ እግዚአብሔር ነው:: በሐጢአታችን እንድንወቀስና ንስሐ እንድንገባ ለማበረታታት ሲል በሕይወታችን ውስጥ ይሠራል:: ንስሐ በምንገባበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ይቅርታን በማምጣት የክርስቶስን ደም በሕይወታችን ውስጥ ተግባራዊ ያደርገዋል:: ይህም ማለት በክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስም ያስተምረን ዘንድ ወደ ሕይወታችን ይገባል ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ ይመራናል፣ ያርመናልም:: ሕይወታችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እንድንሰጥ ያበረታታናል:: ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር በምንሰጥበት ጊዜ ውስጣዊ ሰውነታችንን በክርስቶስ ደም በማንጻት በእግዚአብሔር ህልውና መገኘት የሚሞላንና መስጠታችንን የሚቀበለው መንፈስ ቅዱስ ነው:: በዚህ ዓይነት ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር በመሥራት ደህንነትንና መቀደስን ያመጣልናል:: ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ዕለት በዕለት አሸናፊ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንድንኖር ያስችለናል:: በምንሳሳትበት ጊዜ እያረመን ወደ እውነት ይመራናል:: ስሕተቶቻችንን እርመን ሆን ተብሎ ከሚሠራ ሐጢአት የጸዳ ሕይወት እንኖር ዘንድ የትህትና መንፈስ እንዲኖረን ይረዳናል::

## መንፈስ ቅዱስ በሕይወቴ ውስጥ የሚሠራው እንዴት ነው?

ከመዳናችን በፊት መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወታችን እንደሚመጣና ንስሐ እንድንገባ እንደሚያበረታታን ቀደም ሲል ገልጸናል:: ይህ የመጀመሪያው መሪ ጸጋ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ለሐጢአታችን ይቅርታን በማድረግ የክርስቶስን ደም በሕይወታችን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ቀደም ብለን ተመልክተናል:: ይህንን ደህንነት ብለን እንጠራዋለን:: በተጨማሪም፣ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፈን በምንሰጥበት ጊዜ በልባችን ውስጥ ለማደር እንደሚመጣም

ተመልክተናል:: ይህንን መቀደስ እንለዋለን:: ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ይሄ ብቻ አይደለም::
መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ ብቁ ምስክሮች እንድንሆን ያስችለናል:: ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ እስኪመጣላቸው ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ ነግሯቸዋል:: ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፈን ስንሰጥና መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ሲያድር ፍሬያማ ምስክሮች እንሆናለን:: ሕይወታችን ይታደስና መንፈስ ቅዱስ ለክርስቶስ የምንመሰክርበትን ሀይልና ጥበብ ይሰጠናል:: (ማቴዎስ 4:1፣10፣ ሉቃስ 2:26፣12:1፣ የሐዋርያት ሥራ 5:32፣13:4፣16:6 አነጻጽር::)
መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችንም ያመጣልናል:: የርሱ ስጦታዎች ለቤተክርስቲያን አስፈላጊ የሆኑትን ተግባራት እንድናከናውን ያስችሉናል:: አንዳንዶች ሰባኪዎች፣ ነቢያት፣ ሐዋርያት ወይም አስተማሪዎች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል:: እንደ ጥበቡና ለቤተክርስቲያን ያስፈልጋል ብሎ በሚያስበው መሠረት፣ ጥበብን፣ ማስተዋልን፣ የቋንቋ ችሎታንና ሌሎችንም ብዙ ስጦታዎች ይሰጠናል:: (1ኛ ቆሮንቶስ 7:7፣12: መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ከሁሉም የሚበልጠው ስጦታ የዘላለም ሕይወትና የእግዚብሔር ፍቅር ናቸው:: ሮሜ 6:23፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 13::)
ከሁሉም በላይ፣ እርሱን ከተከተልን መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ሁሉ ፍሬን ያፈራል:: ይህም ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ የዋህነትና ራስን መግዛት ነው (ገላትያ 5:22-23):: መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን የሚሰጠው እንደ ፈቃዱ ነው:: እርሱን የተቀበሉት ሁሉ ስጦታቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል::

# ምዕራፍ 3
# ሰውና ደህንነቱ

## ሰውን የምንረዳው እንዴት ነው?
«ከእምነት አንቀጾቻችን» ሦስቱ ስለ ሰውና የሐጢአት ችግሮች ይናገራሉ:: እነዚህም አምስተኛ፣ ስድስተኛና ሰባተኛ አንቀጾች ናቸው:: በዚህ ምዕራፍ እነዚህን አሳቦች እንመረምራለን::

## ሰው የእግዚአብሔር ፍጡር ነው?
እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል እንደፈጠረው እናምናለን:: ዛሬ ብዙ ሰዎች ሰው የማሰብ ክህሎት ብቻ ያለው እንስሳ እንደሆነ ይናገራሉ:: ይህ አመለካከት ሰው ከሌሎች እንስሳት ጋር ያለውን ግንኙነት ያጎላል:: የሰውን ስህተቶችና ክፋቶች ከአለማወቅ እንደመነጩ ይቆጥራል:: እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት የሰውን ሥነምግባራዊ ችግር በአግባቡ ሊጋፈጥ አይችልም:: ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በመመልከት ስለ ሰው የተሻለ ግንዛቤ ያገኛል:: ሰው እግዚአብሔር በአምሳሉ የፈጠረው ፍጡር ነው:: ይህ ሰውን ከእንስሳት ወደላቀ የሃላፊነት ደረጃ ሲያስቀምጥ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ ሰው ፍጡር መሆኑንና ስህተቱም በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ዓመፅ መሆኑን ይገነዘባል:: ይህንን ዓመፅ ሐጢአት ብለን እንጠራለን::
እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ በኋላ፣ «እጅግ መልካም ነው» ብሏል (ዘፍጥረት 1:31):: ይህም ማለት የሰው ሰውነት፣ አእምሮ፣ ስሜቱ፣ ዝንባሌው፣ መንፈሱ፣ ባጠቃላይም የሰው የአካል ክፍል ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት «መልካም» ነው ማለት ነው:: እግዚአብሔር ሰውን «በአምሳሉ» ፈጥሮታል:: ይህም ሰው የእግዚአብሔር ባህርይ ተካፋይ መሆኑን ያሳያል:: ሰው ወደ መኖር የመጣው በአጋጣሚ በተፈጠረ የዝግመተ ለውጥ ክስተት ሳይሆን፣ ሁሉን በሚችል አምላክ የፈጠራ ውሳኔ ነው:: ስለሆነም፣ ሰው እንደ ፈጣሪው ሁሉ ሃላፊነት ያለበት ፍጡር ነው:: ሊኖር የሚገባውም ዓላማውን ተግባራዊ የሚያደርግ ሕይወት ነው:: ለዚህ ነው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት በማይፈጥርበት ጊዜ ባዶነት የሚሰማው::

## ፍጡር የሆነው ሰው ነጻ ነው?
ሰው ፍጡር ነው:: ፍጡር መሆኑ ራሱ የሰውን ወሰንና ችሎታ ይገድባል:: ሰው በሰውነትና በአእምሮ የማደግ ችሎታ ተሰጥቶታል:: ሰው ድጋፍ ሰጭን ይፈልጋል:: ይህም ከምንኖርባት ዓለም የሚገኝ ነው:: በተጨማሪም፣ ሰው በእውቀቱ ክልል ውስጥ የማሰብና በእውቀቱ ክልል

ውስጥ የመምረጥ ችሎታ ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ቀልድ ሳይሆን እውነት ነው፡፡ ይህ ከሁለት ወይም ከዚያ ከሚበልጡ አማራጮች መካከል አንዱን የመወሰን ችሎታ ነው፡፡ ከነዚህ ምርጫዎች መካከል አንዳንዶቹ ጥሩዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ ሰጥፎዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እያወቁ እጅግ መልካም ከሆነው ያነሰ ነገር መምረጡ ሐጢአት ነው፡፡ ክፋትን ሆን ብሎ መምረጥ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ከሰጠን ደህንነት ወደኋላ መመለስ ነው፡፡ ሰው መልካም ወይም ክፉ ሊመርጥ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል፣ እግዚአብሔር ውስን አይደለም፡፡ እርሱ ሁሉን ቻይና ሁሉን አዋቂ ነው፡፡ እርሱ ደካማ ባለመሆኑ የምርጫ ነጻነት በሰጠው ውስን ፍጡር ውሳኔ አይሸበርም፡፡ ለውስን የሰው ልጅ እንዲህ ዓይነት ምርጫዎችን እየሰጠ ሁሉን ለመቆጣጠር ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ከምርጫዎች ጋር በማጋፈጥ የሰውን ልጆች ባሕርያት ለማሳደግ መርጧል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እግዚብሔር ሰዎች ቁጥጥር ስለተደረገባቸው ወይም የሆነ ሽልማት ስለሚያገኙ ሳይሆን ከልባቸው እውነተኞች እና መልካሞች እንዲሆኑ ስለሚፈልግ ነው፡፡

መልካሙን ወይም ክፉውን መምረጥ የዌስሊያን መሠረታዊ ዶክትሪን ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሰው መምረጥ መቻሉ ለተግባራቱ ሃላፊነት እንደሚወስድ ያሳያል፡፡ ሥነምግባራዊ ተፈጥሮውን የማሳደግ ችሎታ አለው፡፡ «ጥሩ» ወይም «መጥፎ» ሰው የመሆን ብቃት አለው፡፡ ሁለተኛ፣ ሰው መምረጥ መቻሉ ተግባሩ በወደፊት ሕይወት ላይ ተጽእኖ እንደሚያስከትል ያመለክታል፡፡ የእስራኤል ነቢያት ባለማቋረጥ ይህንን እውነት ሰብከዋል፡፡ የሐጢአት መንገዶች ወደ ጥፋት እንደሚመሩና ንስሐ ከገቡ ግን የወደፊቱ ሕይወት የተለየ እንደሚሆን ለህዝቡ ገልጸዋል፡፡ ምርጫቸው እውነተኛ ካልሆነ ንስሐቸው እውነተኛ ሊሆን አይችልም፡፡

## ሰው ሐጢአተኛ ነው?

አዎ፣ አለጥርጥር ሰው ሐጢአተኛ ነው፡፡ ሰው መልካም ሆኖ ቢፈጠርም፣ አሁን ባለበት ሁኔታ ግን ብዙ ክፋት አለበት፡፡ ችግሩ የተከሰተው የመጀመሪያው ሰውና ከሱ በኋላ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ትእዛዛቱን በመጣስ በእግዚአብሔር ላይ ለማመፅ መምረጣቸው ነው፡፡ በዚህም ተግባሩ ሰው ከእግዚአብሔር መራቅ ብቻ ሳይሆን ራሱን ጎድቷል፡፡ የሥራውም መዘዝ እግዚአብሔር በፈጠረው ዓለም ውስጥ ሞትን ማምጣት ነበር፡፡

ምናልባትም ሐጢአት ያስከተለውን ችግር ሁለት ገጽታዎች ለመረዳት ይህንን ምሳሌ መጠቀሙ ይረዳ ይሆናል፡፡ አንድ የመኪና ሥራ ባለሙያ አንዲት ቆንጆ መኪና ሠርቶ ለጓደኛው ሰጠው፡፡ መኪናይቱ በሁሉም ረገድ ውብ ስለነበረች ለፈጣሪዋና ለባለቤቷ የደስታ ምንጭ ሆነች፡፡ የመኪናዋ ሠሪ ጓደኛው መኪናውን እንዴት መንከባከብ እንዳለበት እያስተማረ ሳለ ጓደኛው ግን የራሱን ህግ አውጥቶ በራሱ አቅጣጫ መተለም የሚችል ብቁ ሰው አድርጎ ራሱን ቆጠረ፡፡ ለጓደኛው ጀርባውን ሰጥቶ መኪናውን ይዞ

በመውጣት ገለበጣት። በዚህ ጊዜ ሌሎች ችግሮች ተደቀኑበት። መኪናውን እንዴት ሊንከባከብ እንደሚገባ ሊያስተምረው ከሚችለው ባለሙያ ጓደኛው ጋር ከመቀያየሙም በላይ፣ መኪናይቱንም አበላሽቷታል። መኪናይቱ አሁን የተሠራችለትን ዓላማ ለመፈጸም ሁለት ነገሮች ያስፈልጓት ነበር። በመጀመሪያ፣ ወደ ቀድሞ ሁኔታዋ ለመመለስ ጠጋኝ ያስፈልጋት ነበር። አለዚያ መኪናይቱ በአግባቡ ልትሠራ አትችልም። ሁለተኛ፣ ለመኪኖች የሚያስፈልገውን ሁሉ እያሟላ በጥንቃቄ የሚነዳ ሰው ያስፈልጋት ነበር።
ይህ ታሪክ የሰው ልጅ ያለበትን አጣብቂኝ ያመለክታል። ሰው በሁሉም ረገድ ጥሩ ሆኖ ከመፈጠሩም በላይ፣ እግዚአብሔር የፈጠረውን ዓለም የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር። የሕይወቱን አቅጣጫና ዓላማ ለማግኘት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ ሲኖርበት፣ ሰው ግን የራሱን አቅጣጫ ይዞ ለመጓዝ በመፈለጉ ሐጢአትን ፈጸመ። ከዚህም የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ግንኙነት ሊቋረጥና ራሳችንንና ዓለምን ልንጎዳ ቻልን። ደስታና እርካታ ተለይቶን የውሸት ተስፋንና ዓላማዎችን እናሳድዳለን።
ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ለዚሁ ችግር መፍትሔ ለመስጠት ነው። በመጀመሪያ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረንን ህብረት ለማደስ በመስቀል ላይ ሞተ። ይቅር ሊለንና ሕይወታችንን ሊያስተካክል በመስቀል ላይ ሞተ። መስቀሉ የሐጢአትን ይቅርታ ያገኘንበትና ሕይወታችን የተስተካከለበት ስፍራ ነው። ክርስቶስ አሁን ተከታዮቹን ሁሉ በዚህ የማዳኑ ተግባሩ ለማሳተፍ ይፈልጋል። ለዚህም ነው፣ «ከኋላዩ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ። መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ» የሚለው (ማርቆስ 8:34)። ሁለተኛ፣ በውስጣችን እንዲኖር፣ እንዲያስተምረንና ሕይወታችንን በአግባቡ የምንቆጣጠርበትን ሀይል እንዲሰጠን ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን ላከልን። ለክርስቲያኑ የቅድስና ሕይወት አስፈላጊነት አጽንኦት የሚሰጠው ለዚህ ነው። እግዚአብሔር እንደገና የተቆጣጣሪነትን ስፍራ መያዝ አለበት። ክርስቶስ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥና በየጊዜው የሚያድግ ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል። ይህ በእግዚአብሔር ጸጋ ማደግ ለክርስቲያናዊ አኗኗር ወሳኝ ነው። ይህም ጸሎትን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን፣ እግዚአብሔርንና ሰዎችን ማገልገልን፣ እንዲሁም ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ህብረት ማድረግን የሚጠይቅ ነው።

## ሐጢአት በሰው ነጻነት ላይ ያስከተለው ውጤት ምንድው?

ሁለት እውነቶችን መግለጽ ይኖርብናል። አንደኛ፣ የመጀመሪያው ሰው አዳም የተሳሳተ ነገር ለማድረግ መርጧል። ይህም እሱም ሆነ ዘሮቹ ትክክለኛውን ነገር የመፈጸም ብቃት እንዳይኖራቸው አድርጓል። ያለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ማንም ሰው ያለማቋረጥ ትክክለኛውን ነገር ሊመርጥ አይችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ጸጋ እንደሚሰጠን

እናምናለን:: ሁለተኛ፣ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የመምረጥ ብቃት አለን:: በየትኛውም ጊዜ ከደህንነት በኋላም እንኳዋን ቢሆን አንድ ሰው ልክ እንደ አዳም የተሳሳተ ነገር ለመፈጸም ሊመርጥ ይችላል:: አንድ ሰው የተሳሳተ ነገር ለማድረግ ቢመርጥ ንስሐ እስካልገባ ድረስ ለዘላለሙ ሊጠፋ ይችላል::

## ሐጢአት ምንድነው?

ሁለት ዓይነት ሐጢአቶች አሉ:: አንደኛው፣ አንድ ግለሰብ ስህተት መሆናቸውን እያወቀ ሆን ብሎ የሚፈጽማቸውን ተግባራት የሚያመለክት ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ የመጀመሪያው ሐጢአት ወይም ውድቀት ብለን የምንጠራው ነው:: ውድቀት ከሐጢአት የተነሣ በሰዎቻችን፣ በዓለማችንና በግንኙነቶቻችን ውስጥ የሚገኝ ጎጂ ገጽታ ነው::

ሐጢአት መጀመሪያ ወደዚህች ዓለም የመጣው በአዳምና ሔዋን አለመታዘዝ ነው:: የሐጢአት ተግባራቸው እነሱን ብቻ ሳይሆን ዓለምን በሙሉ ጎድቷል:: ይህም በነሱ ላይ በመጣውና ለኛም በተረፈው መርገም አማካኝነት ሊገለጽ ይችላል:: ሞት ወደ ዓለም ገባ:: እነሱም ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ህብረት አጥተው ለራሳቸው ክብርን አጥተዋል:: እግዚአብሔር የገነትን በር በእሳት ሰደድ አጠረባቸው:: እነርሱም ራቁትነታቸውን ለመደበቅ ሞከሩ:: ይህ ጉዳት በመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችንና በዓለማችን ላይ ደርሷል:: ከዚህም የተነሣ ወደፊት የሚመጡ ትውልዶች ሁሉ የተጎዳው ዓለም አካል በመሆናቸውና የተበላሸ ባሕርይ ተካፋዮች በመሆናቸው፣ ከእግዚአብሔር ተለይተዋል:: የክርስቶስ ጸጋ ካልበዛልን በስተቀር ተስፋ የለንም::

ይህ ማለት ሰዎች ሁሉ ጨርሶ ክፉዎች ናቸው ማለት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ያቀደላቸውን ሊሆኑ አልቻሉም ማለት ነው:: ሐጢአት ከሕይወታቸው እንዲርቅ ከፈለጉ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ተመልሰው ሊታረቁና ከሐጢአታቸው ንስሐ ሊገቡ (ይህንን ደህንነት ወይም ዳግም ልደት እንለዋለን)፣ ብሎም በልባቸው ሊለወጡ ይገባል (ይህንን መቀደስ እንለዋለን):: ከዚያ በኋላም ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረጋቸውን መቀጠል አለባቸው:: ዘፍጥረት 6:5፣ ኤርምያስ 17:9-10፣ ሮሜ 3:9-10፣23፣ ኤፌሶን 2:3)

## ሐጢአት ከሕይወታችን የሚወገደው እንዴት ነው?

ክርስቶስ ሐጢአትን ከሕይወታችን ያስወግደዋል:: ደሙ ሁለት ነገሮች በሕይወታችን እንዲፈጸሙ ያደርጋል:: በመጀመሪያ፣ የሐጢአት ተግባሮቻችንን በማጠብ ይቅርታንና ከእግዚብሔር ጋር የመመላለስን ጸጋ ያላብሰናል:: ሁለተኛ፣ ደሙ ውስጣዊ ሰውነታችንን በማጠብ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ህብረት እንዲኖረን ያደርጋል:: ይህም እርሱ በውስጣችን ስላለ መንፈሱ ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር ያደርጋል:: በቀጣዩ

ምዕራፍ መንፈስ ቅዱስ ሰውን በማዳን የሚያናውነው ተግባር ሰውን ከመቀደስ ተግባሩ ጋር እንዴት እንደሚለይ እንመለከታለን:: የሐጢአት መወገድ ብቸኛ የደህንነትና የመቀደስ ገጽታ አይደለም:: እነዚህ ልምምዶች ከእግዚአብሔር፣ ከሌሎች ሰዎችና ከራሳችን ጋር የሚኖሩን ግንኙነቶች መለወጣቸውንም ያካትታሉ::

## ሐጢአት ወደ አማኙ ሕይወት ተመልሶ ሊመጣ ይችላል?

አዳም ፍጹም ሆኖ የተፈጠረ ሲሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም እና ንቁ ግንኙነት ያደርግ ነበር:: ነገር ግን በተፈተነ ጊዜ ሐጢአትን ፈጸመ:: ምንም ያህል ለብዙ ዓመታት በክርስትና ሕይወት ቢቆይ ወይም በቤተክርስቲያን ውስጥ ምንም ያህል ከፍተኛ ሥልጣን ቢኖረው፣ ማንኛ ውም ሰው በሐጢአት ሊፈተን ይችላል:: ሁላችንም ልንፈተንና የተሳሳተ ተግባር ለመፈጸም ልንመርጥ እንችላለን:: የተሳሳተውን ነገር ከመረጥን ለስህተታችን ንስሐ መግባት አለብን:: ኃጢአት ስለፈጸምን ብቻ እግዚአብሔር ከቤተሰቡ ውስጥ እንደማያባርረን መገንዘቡ ተገቢ ነው:: እርሱ ወደ ቤተሰቡ ስላስገባን የትኛውም የቤተሰብ አባል ሐጢአት በፈጸመ ጊዜ በንስሐ እንዲመለስ አጥብቆ ይሻል (ሕዝቅኤል 18:24፣ ሉቃስ 8:13፣ ገላትያ 5:4፣11፣ 2ኛ ጴጥሮስ 3:17::):: ከጸጋ መውደቁ የግድ አይደለም:: ይሁዳ «ከውድቀት ሊጠብቀን ለሚችለው» ለክርስቶስ አሳልፎ እየሰጠን በመጸለይ ይህንን እውነት አስታውሶናል::

## ደህንነት፣ መንግሥተሰማይና ሲኦል

ሙሉ መዳን አሁን በሕይወቴ ታላቅ ለውጥ አምጥቷል:: ይህ ደህንነት መልካም አስተዋጽኦ የማደርግ ቀና ሰው እንድሆን አስችሎኛል:: ከበደል ሸክም ነጻ ወጥቻለሁ:: ለራሴ፣ ለሌሎችና ለእግዚአብሔር ቀና አመለካከት ይኖረኛል:: እነዚህ ለውጦች አስደናቂዎች ናቸው:: ክርስቶስ ሰው የሆነው በዚህ ምድር ሕይወቴን መልካም ለማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ከሁላችንም ጋር ሊካፈል ስለሚፈልገው የዘላለም ሕይወት ነው::

ነገር ግን ሕይወት ከጊዜ ጋር አያበቃም:: የዘላለም ሕይወት አለ:: ይህ ሰዎች ከሞት በኋላ የሚገቡበት ዘላለማዊ ሕልውና ከእግዚአብሔር ጋር ወይም ከእግዚአብሔር ተለይተው የሚገፉት ነው:: ንስሐ ከገባን፣ የክርስቶስ ደም ካዳነንና ሕይወታችንን ከለወጠው የዘላለሙን ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር እናሳልፋለን:: ካልሆነ ግን ዘላለምን ከእግዚአብሔር ውጭ እናሳልፋለን::

እንደ ራእይ በመሳሰሉት መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር ሰዎች ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር የምንካፈለውን ሕይወት ፍጹማዊነት በጨረፍታ አሳይተውናል:: እነዚህ ጸሐፊዎች ከእግዚአብሔር ጋር

ስለምንኖርባት መንግሥተሰማይ ራእዮችን አይተዋል:: አንዳንድ ጊዜ በዚህ ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔር ህልውና ወይም (ኃልዎት) ሲበዛ፣ መንግሥተሰማይን እንደቀመስን እናውቃለን:: መንግሥተሰማይ እግዚአብሔር የሚገኝበት ስፍራ እንደሆነ በውስጣችን ይሰማናል::
በሌሎች ተምሳሌቶች የእግዚአብሔር ሰዎች ለዘላለም እግዚአብሔር በሌለበት ስፍራ ተዘግተው የሚኖሩ ሰዎች ስፍራ ምን ያህል አስከፊ፣ አሠቃቂ፣ አሳፋሪ፣ ክፉና አጥፊ እንደሆነ ገልጸዋል:: ይህም ሲኦል ነው:: ሲኦል ለሰዎች ሳይሆን ለዲያብሎስና ለመላእክቱ የተዘጋጀ ስፍራ እንደሆነ ተገልጾአል:: ወደዚህ ዘላለማዊ ሲኦል የሚሄዱት ከዲያብሎስ ጋር የሚተባበሩ ሰዎች ብቻ ናቸው:: እግዚአብሔር ዲያብሎስን አሸንፎ ከዚህ የሐጢአት ቅጣት ነጻ የሆነ ስፍራ አዘጋጅቶልናል::

## ምዕራፍ 4
# ደህንነትና መቀደስ

## የእምነት አንቀጾች
ይህ ምዕራፍ በቁጥር ስምንት፣ ዘጠኝና አሥር ውስጥ የተጠቀሱትን የእምነት አንቀጾች ያብራራል። እነዚህም አንቀጾች ስለ ኃጢአ፣ ደህንነትና ቅድስና ያስረዳሉ።

## ደህንነትና ቅድስና ምንድናቸው?
«ደህንነት» የሚለው ቃል ከሥራዎቻችን መዘዞች መትረፍን ያመለክታል። «መቀደስ» ለእግዚአብሔር መለየትን ያሳያል። ክርስቲያኖች እነዚህን ሁለት ቃላት በተለያዩ መንገዶች ይጠቀማሉ።
በተሟላ ትርጉሙ «ደህንነት» የሚለው ቃል ሰው ከሐጢአት ተግባሩ ነጻ በሚወጣበት ጊዜ የሚከሰቱትን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል። ይህም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ከሚያዘጋጀው የደህንነት ሥራ ይጀምርና በክፋት የኋላ ኋላ ድል መነሣት ያከትማል። አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ ፍችዎችን ለማመልከት በቅጽሎች እንጠቀማለን። ለምሳሌ፣ *የመጀመሪያ* ደህንነት ንስሐ መግባትንና ይቅርታ ማግኘትን ሲያመለክት፣ *ሙሉ* ደህንነት መንፈስ ቅዱስን መቀበልን ያመለክታል። የመጨረሻው ደህንነት ወደ መንግሥተሰማይ መሄድን ያሳያል።
ብዙውን ጊዜ ደህንነት የሚለው ቃል ለሐጢአት ይቅርታ ተተኪ ሆኖ ያገለግላል። ይህንን የመጀመሪያው የጸጋ ሥራ እንለዋለን። የዚህን ልምምድ ጥልቅነት የሚገልጹ የተለያዩ ቃላት አሉ። እነዚህን ቃላት በተናጠል እንመለከታለን።
«መቀደስ» የሚለው ቃልም ሰፊ ፍች አለው። ይህ ቃል ከደህንነት ጋር ይመሳሰላል። ለዚህም ምክንያቱ ቅድስና አማኙን ንጹሕ ማድረግን የሚያመለክት ሲሆን፣ ደህንነት ግለሰቡ በሥራው ምክንያት ከሚደርስበት ቅጣት ነጻ የሚሆንበት ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በምንመላለስበት ጊዜ ከገጠመኞቻችን ሁሉ ጋር የሚዛመዱ የመንጻትና ነጻ የመውጣት ገጽታዎች አሉ። ለዚህም ነው ብዙውን ጊዜ «የመጀመሪያው ቅድስና» የሚሉት ቃላት በደህንነት ጊዜ የሚከሰተውን ሁኔታ ለማብራራት የሚያገለግሉት። ናዛሬኖች ግን ብዙውን ጊዜ ቅድስና የሚለውን ቃል የሚጠቀሙት የልብን መንጻት ለማመልከት ነው። አንዳንድ ጊዜ ይህንን ከ«መጀመሪያው ቅድስና» ለመለየት ስንል «ሁለንተናዊ ቅድስና» ብለን እንጠራዋለን። የዚህን ልምምድ የተለያዩ ገጽታዎች ለመግለጽ የተለያዩ ቃላት አገልግለዋል።

## ሊድንና ሊቀደስ የሚችለው ማነው?
መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ የሚያምን ማንኛውም ሰው ደህንነትን ሊያገኝና ሊቀደስ እንደሚችል ያስረዳል። እግዚአብሔር ምርጫውን ሰጥቶናል። አምነን ለመዳን ልንመርጥ እንችላለን። ይህንን ደህንነት ለማግኘት ኢየሱስ ክርስቶስን ከማመንና እርሱን ከመታዘዝ ውጭ ምንም ዓይነት ገንዘብ መክፈል ወይም ምንም ዓይነት ተግባር መፈጸም የለብንም። ማመንና መታዘዝ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። (1ኛ ዮሐንስ፣ ማቴዎስ 11:28፣ ዮሐንስ 1:9፣ 3:17፣ ሮሜ 1:20-21፣ 2:14-15፣ ቲቶ 2:11፣ 11 ጴጥሮስ 3:9)

## ንስሐ መግባቱ የግድ አስፈላጊ ነውን?
ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት ለሚፈልግ ሰው ሀሉ ንስሐ መግባት መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ንስሐ መግባት ማለት ሐጢአቴንና በደሌን አውቄ ከክፋት ወደ እግዚብሔር መመለስ ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በመውቀስና በመገፋፋት ንስሐ እንድንገባ ያስችለናል። ይህንን የመጀመሪያው ጸጋ ብለን እንጠራዋለን። ይህም ከደህንነት በፊት የሚገለጥ ጸጋ ነው። ይህንን ጸጋ ለመቀበል ካልፈለግን የእግዚአብሔርን ማዳን ልንቀበል አንችልም።

ንስሐ መግባት ያበላሸነውን ነገር ማስተካከልን ይጨምራል። እዚህ ላይ ካሳ የሚለው ቃል ወሳኝ ይሆናል። ይህም ከዚህ በፊት የፈጸምሁትን ጥፋት ማስተካከል ከቻልሁ፣ ማስተካከል አለብኝ ማለት ነው። ይህንን ለማድረግ አለመፈለግ ከሐጢአት ተግባሮቻችን ውጤቶች ከመራቅ ይልቅ ይህንኑ ለማድረግ እንደምንመርጥ ያሳያል። ዘኪዎስ ወደ ክርስቶስ በተመለሰ ጊዜ ካሳ ለመክፈል መፍቀዱን ወዲያውኑ አስታውቋል። ከሰረቀው አራት እጥፍ መልሷል። ይህም ወደ እግዚአብሔር እንዴት ባለ ጉጉት እንደተመለሰ ያሳያል (ሉቃስ 19:8)። ክርስቶስም ደህንነት ወደ ዘኪዎስ ቤት መምጣቱን አውጇል።

## የእግዚአብሔር ጸጋ ምንድነው?
የእግዚአብሔር ጸጋ ችግሮቹ የደረሱብን በራሳችን ጥፋት ቢሆንም እንኳዋን ወደ ሰው ልጆች ለመምጣትና ለመርዳት ያለው ፈቃደኝነት ማለት ነው። ከዚህ ቃል ጋር የሚመሳሰሉ የመጽሐፍ ቅዱስ አሳቦች ምሕረትና ጥልቅ ፍቅር ናቸው።

የእግዚአብሔር ጸጋ ግንኙነቶቻችንን ሁሉ ይዳስሳል። የመጀመሪያ ጸጋ እግዚአብሔር ሐጢአተኞች ሳለን እኛን ለማዳን የሚወስደውን እርምጃ ያሳያል። የመጀመሪያው የጸጋ ሥራ የሐጢአትን ይቅርታ ማግኘትና ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ጋር መቀላቀል ነው። ሁለተኛው የጸጋ ሥራ ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን መስጠት ነው። ይህም ከመንፈስ

ቅዱስ ሙላት ጋር አብሮ የሚመጣ ነው:: በጸጋ ማደግ ከእግዚአብሔር ጋር በሚመሳሰስ ሰው ሕይወት ውስጥ የሚፈጸም የማያቋርጥ እድገት ነው:: ይህም ለመጀመሪያው ጸጋ ምላሽ ከሰጠንበት ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ምድር እስከምንሰናበትበት ጊዜ ድረስ የሚቀጥል ነው:: ለዚህም ብቸኛው መመዘኛ መንፈስ ቅዱስን መታዘዝ ነው::

**ለመጀመሪያው የጸጋ ሥራ ብዙ ቃላት ለምን አስፈለጉ?**
ለመጀመሪያው የጸጋ ሥራ የቀረቡት ብዙ ቃላት እያንዳንዳቸን ስለ ልምምዱ የተለያዩ እውነቶችን እንድንገነዘብ ይረዱናል::

**ደህንነት** ልምምዱ በተሳሳተ ተግባራችን ምክንያት ይደርስብን ከነበረው ቅጣት መትረፋችንን ያመለክታል::

**ቤዛነት** ራሳችንን ነጻ ልናወጣ እንደማንችልና ኢየሱስ ክርስቶስ ከክፉ ልማዶቻችንና ተግባሮቻችን ሊያላቅቀን እንደሚገባ ያስረዳል::

**ዳግም ልደት** ይህንን የጸጋ ተግባር የሚያጠናቅቀውን ሙሉ የአዲስ ሕይወት ነጻነት ያሳያል::

**ጽድቅ** ክርስቶስ ለፈጸምነው በደል ይቅርታ እንዳደረገልንና ልንቀበለው ከሚገባን ቅጣት እንዳዳነን ያመለክታል::

**አዲስ ልደት** ይቅርታን ባገኘን ጊዜ መንፈሳዊ ሕይወት ወደ ልባችን እንደሚመጣ ያስረዳል::

**ልጅነት** እግዚአብሔር እኛን የቤተሰቡ አካል እንደሚያደርግ ያሳያል:: በልጅነት መብታችን ከክርስቶስ ጋር አብረን የምንወርስ ስንሆን፣ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ባሕርይ እንድናሳይ ይጠበቅብናል:: ይህ እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ፍቅር የሚያመለክት ግሩም ጽንሰሐሳብ ነው::

**ሁለተኛውን የጸጋ ተግባር ለመግለጽ ለምን ብዙ ቃላትን መጠቀም አስፈለገ?** ሁለተኛው የጸጋ ሥራ በሕይወታችን ውስጥ ብዙ ነገሮችን ያጠቃልላል:: እነዚህን ገጽታዎች ለመግለጽ የተለያዩ ቃላት አገልግለዋል::

**ቅድስና** የናዛሪን ቤተክርስቲያን መገለጫ (ጭብጥ) ነው:: እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲቀደስና ከቅድስናው እንዲካፈል ይፈልጋል (ዘሌዋውያን 1:44፣

1ኛ ጴጥሮስ 1:16)። ይህ ቅድስና ከራሳችን ሳይሆን ከክርስቶስ እንደሚመነጭ ስለሚያስታውሰን ብዙውን ጊዜ ክርስቲያናዊ ቅድስና ብለን እንጠራዋለን።

መቀደስ ምናልባትም የቅድስናን ልምምድ ለማመልከት እጅግ አዘውትረን የምንጠቀምበት ቃል ሳይሆን አይቀርም። ይህም ውስጣዊ ሰውነታችን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት መለወጡን የሚያመለክት ነው። እርሱ የቆሸሸውን ያነጻዋል። የረከሰውንም ይቀድሰዋል።

ክርስቲያናዊ ፍጹምነት ጆን ዌስሊ በጣም የሚወደው አገላለጽ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲቀደስ በተደጋጋሚ ጥሪውን ያቀርባል (ፊልጵስዩስ 3:15፣ ዕብራውያን 13:21፣ 1ኛ ጴጥሮስ 5:10፣ 1ኛ ዮሐንስ 4:17)። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየቀረበ በሚመጣበት ጊዜ ጉድለቶቹን ይበልጥ የመመልከት ብቃት ይኖረዋል። ይህም ፍጹምነት የሚለው ቃል እንዲጎረብጠን ያደርጋል። ይህም ሆኖ፣ ቃሉ የእግዚአብሔር ዓላማ እኛን ፍጹም ማድረግ መሆኑን ስለሚያመለክት እጅግ ጠቃሚ ነው። ዌስሊ ይህ ቃል የልብን ብስለትና የፍጹም ልብን አመለካከት እንጂ እንከንየለሽ ፍጹማዊነትን እንደማያመለክት ለመግለጽ ክርስቲያን የሚለውን ቅጽል በአስተዋይነት ተጠቅሟል።

የልብ ቅድስና የእግዚአብሔር መንፈስ ባሕርያችንን ከክፉ ወደ መልካም ለመለወጥ በልባችን ውስጥ በመሥራቱ ላይ ያተኩራል።

የበረከት ሙላት በእግዚብሔር ጸጋ አማካኝነት ከሐጢአት ሀይል ነጻ መውጣታችን በይቅርታና ዳግም ልደት እንደማያበቃ ያሳያል። ይህንን ሙሉ በሙሉ የምንቀበለው የክርስቶስ ደም ውስጣዊ ሰውነታችንን እንዲያነጻ በምንፈቅድበት ጊዜ ብቻ ነው።

ራስን መሠዋትና ሙሉ መሰጠት እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ በሚያከናውነው ተግባር ውስጥ ድርሻችን ምን ሊሆን እንደሚገባ የሚያመለክቱ አገላለጾች ናቸው። አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትን ለመመሥረት ይችል ዘንድ የራሱን ፈቃድ ለእግዚአብሔር ፈቃድ አሳልፎ መስጠት አለበት። ጳውሎስ ይህንን «ለራስ መሞት» ሲል በተደጋጋሚ ገልጾታል (1ኛ ቆሮንቶስ 15:31፣ ፊልጵስዩስ 1:21፣ ገላትያ 2:20፣ 5:24፣ ሮሜ 6:6)። ክርስቶስ፣ «የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን» ባለ ጊዜ ለዚህ እውነታ ምስክርነቱን ሰጥቷል (ማርቆስ 14:36)።

በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ሁለተኛውን የጸጋ ሥራ የሚያከናውነውና በሕይወታችን ውስጥ የሚያድረው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ያመለክታል:: «በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተናል» የምንለው በዚህ ጊዜ ነው:: ከዚህ በኋላ በሕይወታችን ተጠቅሞ ሌሎችን በሚገባ ሊያገለግልና እንድንሆንለት ወደሚፈልገው ሕይወት ሊለውጠን ይችላል::

## እንግዲህ ሁለንተናዊ ቅድስና ምንድነው?

ሁለንተናዊ ቅድስና እግዚብሔር ለእማኙ መስጠት የሚሰጠው ምላሽ ነው:: መንፈስ ቅዱስ የክርስቲያኑን ውስጣዊ ሕይወት በማንጻት በልቡ ውስጥ ያድራል:: ከዚያም የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወቱ ውስጥ ይነግሣል:: የዚያም ሕይወት ዓላማ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል:: ከዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ከሚኖረን ቀጣይና የቅርብ ግንኙነት ውስጥም ሰላምና ሙሉነት ይመነጫሉ::

መንፈስ ቅዱስ በልባችን አደረ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው በመኖር ፈቃዱን የምንፈጽምበትን ሀይል አግኝተናል ማለት ነው:: ይህም ለሕይወትና ለአገልግሎት የምንጠቀምበት እንጂ መንፈሳዊነታችንን ለሰዎች የምናሳይበት አይደለም::

## የራሳችንን ግላዊ የጸጋ ሁኔታ እንዴት ልናውቅ እንችላለን?

የእግዚአብሔር መንፈስ ከመንፈሳችን ጋር በመመሳከር ያለንበትን የጸጋ ሁኔታ ይገልጻል (ሮሜ 8:16):: መዳናችንን ወይም መቀደሳችንን ለመግለጽ ለልባችን ቀጥተኛ ምስክርነትን በመስጠት፣ በመጽሐፍ ቅዱስና በሌሎች ክርስቲያኖችም ይጠቀማል::

## የተቀደሰ ሰው ለመንፈሳዊ አደጋዎች ሊጋለጥ ይችላል?

መቀደስ አንድን ሰው የማይደፈር መንፈሳዊ ጀግና አያደርገውም:: በሐጢአት ሊፈተንና ሊወድቅ ይችላል:: ይህ ግለሰቡ ስህተቶችን እንዳይፈጽም አያግደውም:: አንድ ሰው ስህተትን ከፈጸመ መልሶ ማስተካከል አለበት:: ስህተትን ለማረም አለመፍቀድ ሐጢአት ነውና:: ከሰው ልጅ ውድቀት በፊት አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ህብረት እያላቸው ሐጢአት መፈጸማቸውን መዘንጋት የለብንም:: ይህ የሰው ልጅ ሁኔታ ነው:: በፊታችን የምንመርጣቸው ነገሮች የተቀመጡ ሲሆኑ፣ ትክክለኛውን ወይም የተሳሳተውን ነገር የመምረጥ ችሎታ አለን:: መቀደስ ይህንን እውነት አይለውጠውም:: ከብዙ ዘመናት በፊት ነቢዩ ሚክያስ እግዚአብሔር ከሰዎች ምን እንደሚፈልግ ገልጾአል (ሚልክያስ 6:8):: እነዚህም፣ «ፍትህን ማድረግ»፣ «ምሕረትን መውደድ»፣ እና «ከእግዚአብሔር ጋር በትህትና መመላለስ» ናቸው:: እነዚህ የተቀደሱ ክርስቲያኖች ሊፈጽሟቸው የሚገቧቸው መሠረታዊ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: ፍትህ፣ ምህረትና ትህትና ከእግዚአብሔር ጋር የሚመላለስ ሰው ተለይቶ የሚታወቅባቸው መለያዎች ናቸው::

## ምዕራፍ 5
# መጽሐፍ ቅዱስ-የሕይወት መመሪያችን

## መጽሐፍ ቅዱስ ምንድነው?
መጽሐፍ ቅዱስ ለደህንነታችን አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር የገለጠበት መጽሐፍ ነው። ይህ የሥነመለኮታችንም ሆነ የሥነምግባራችን መሠረት ነው (የእምነት አንቀጽ 4)።

## መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ነው?
መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊና ቅዱስ መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት መዝግቦ ይዟል። የተጻፈውም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን እውነት፣ ፍትህና ፍቅር ያሳያል። በሰው ልጆች ምክንያት እግዚአብሔር የሚሰማውን ደስታና ሀዘን ይገልጣል።

## መጽሐፍ ቅዱስ ምትሃት ነው?
መጽሐፍ ቅዱስ የምትሃት መጽሐፍ አይደለም። እግዚአብሔር ሰዎችን በምትሃት አማካኝነት የሚፈውስ አምላክ አይደለም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅሶችን እያወጡ መደርደሩ እግዚአብሔር ሰዎች የሚፈልጉትን እንዲያደርግ አያስገድደውም። የሚፈጽመውን የሚወስነው ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።
በአንድ ቤት ውስጥ የተቀመጠ መጽሐፍ ቅዱስ ቤቱን ቅዱስ አያደርገውም። መጽሐፍ ቅዱስን ይዞ መዞር ግለሰቡን ቅዱስ አያደርገውም። በሽያጭ መደብር ውስጥ የተቀመጠ መጽሐፍ ቅዱስ መደብሩን አይቀድሰውም። መጽሐፍ ቅዱስን መቶ በመማል ውሸትን መናገሩ ሰውዬውን ለበሽታ አይዳርገውም። መጽሐፍ ቅዱስ የምትሃት መጽሐፍ አይደለም።

## መጽሐፍ ቅዱስ የሰው መጽሐፍ ነው?
መጽሐፍ ቅዱስ በሰው የተጻፈ የሰው መጽሐፍ ነው። የእያንዳንዱን ጸሐፊ የአጻጻፍ ስልት በግልጽ መለየት ይቻላል። በውስጡም ሰቆቃዎችና መዝሙሮች፣ ታሪኮች፣ ሕጋዊ ድንጋጌዎች፣ ውሎች እና ቃል ኪዳኖች ይገኛሉ። በተጨማሪም፣ የትንቢት ዜና መዋዕል፣ ታሪኮች፣ ስብከቶች፣ ደብዳቤዎች፣ ራእዮች፣ ምሳሌዎች፣ ትምህርቶችና ሌሎችም ብዙ ነገሮች አሉበት። እነዚህ ሁሉ ሰብአዊ የሥነጽሑፍ ቅርጾች ናቸው። በክርስቶስ ውስጥ የምንመለከተው የሁለትዮሽ ባህርይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም

ይታያል:: መጽሐፍ ቅዱስ በተመሳሳይ ጊዜ ፍጹም መለኮታዊና ፍጹም ሰብአዊ ነው::

## መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት አገኘን?

መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ከ2000 በሚበልጡ ዓመታት ውስጥ ነው:: የትኞቹ ክፍሎች እጅግ ጥንታዊ እንደሆኑ መናገር ያዳግታል:: መጽሐፍ ቅዱስ መቼ፣ የት፣ ወይም በማን እንደተጻፈ ዘርዝሮ አይናገርም:: ሙሴ ከቀደምት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰኑትን በመጻፍና በማሰባሰብ የበኩሉን አስተዋጽኦ አድርጓል:: የነዚህ ክፍሎች ቅጂዎች በእስራኤልና በይሁዳ ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎ ውስጥ በጥንቃቄ ተቀምጠዋል:: መጀመሪያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ያሚቀበሉት ከካህናት ወይም ከነቢያት ነበር:: በኋላ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያስተምርበት ዋንኛ መንገድ ሆነ:: የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ቀዳሚ ባለሥልጣን መሆኑ የተገለጸበት የመጀመሪያው የጽሑፍ ማስረጃ የሚገኘ ው በ2ኛ ነገሥት ምዕራፍ 22 ውስጥ ነው:: በዚህ ክፍል በቤተመቅደስ ዳግም ግንባታ ወቅት ከተገኘው የቃል ኪዳን መጽሐፍ የቀረበውን ንባብ ንጉሥ ኢዮስያስ ሲታዘዝ እንመለከታለን::

ብሉይ ኪዳን ሦስት የዕድገት ደረጃዎች ነበሩት:: የመጀመሪያው ደረጃ አምስቱ «የሙሴ መጻሕፍት» እንደ እግዚአብሔር ሕግጋት እውቅና ያገኘ በት ነበር:: ይህ የሆነው እስራኤል በምርኮ በተወሰደችበት ወቅት ነበር::

እንደ እግዚአብሔር ቃል እውቅና የተሰጠው ሁለተኛው የብሉይ ኪዳን ክፍል የነቢያት መጻሕፍትና ስለነቢያት የተጻፉ መጻሕፍት ነበሩ:: (ከነዚህ መጻሕፍት አብዛኞቹ የታሪክ መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ::) እነዚህን መጻሕፍት የሚለየው ቁልፍ ሐረግ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» የሚለው ነው:: በክርስቶስ ዘመን እነዚህ መጻሕፍት ነቢያት በመባል ይታወቁ ነበር::

ሦስተኛውና የመጨረሻው ስብስብ መዝሙራትንና ሌሎች ጽሑፎችን ያካተተ ነበር:: ይህም ታሪኮችን፣ መዝሙሮችንና ምሳሌዎችን ያጠቃልላል:: ክርስቶስ ከሞተ ከ60 ዓመታት በኋላ ድረስ የነዚህን መጻሕፍት ይዘቶች የማሰባሰቡ ተግባር ቀጥሎ ነበር:: ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የነዚህ መጻሕፍት ብዙ እትሞች በስርጭት ላይ ነበሩ:: ዋንኞቹ እትሞች በግብጽ፣ በባቢሎንና በኢየሩሳሌም ተጠብቀው ይገኙ ነበር:: በግብጽ ተቀምጦ የነበረው ክፍል ሴፕቱዋጀንት በሚል ስያሜ በግሪክ ቋንቋ ተተርጉሞ ቀርቧል:: ይህም የጥንቷ ቤተክርስቲያንና የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የብሉይ ኪዳን ሊሆን በቅቷል:: በባቢሎን የነበረው ስብስብ አይሁዶችና ፕሮቴስታንቶች የሚጠቀሙበት ሜዞሬቲክ እትም ለመሆን በቅቷል:: በኢየሩሳሌም የተቀመጠው ስብስብ ግን ጠፍቷል:: ይህ የሆነው ምናልባትም ሮማውያን ከተማይቱን ባወደሟት ጊዜ ሳይሆን አይቀርም::

አዲስ ኪዳንን ለመጻፍ ግን ረዥም ጊዜ አልወሰደም፡፡ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ በ100 ዓመታት ጊዜ ውስጥ አዲስ ኪዳን ተጽፎ ተጠናቋል፡፡ በአራተኛው ክፍለዘመን የትኞቹ መጻሕፍት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሊካተቱ እንደሚገባ ቤተክርስቲያን ውሳኔ አስተላለፈች፡፡ በዚህም መሠረት አዲስ ኪዳን ወንጌላትን (የክርስቶስን ታሪክ)፣ መልእክቶችን፣ የቀድሞይቱን ቤተክርስቲያን ታሪክና የተለያዩ ራእዮች ባካተተ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡

## የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጥሩ እንደሆነ እንዴት ላውቅ እችላለሁ?

የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበራት የሚያከናውኗቸው ትርጉሞች በተቻለ መጠን ትክክል ለመሆን ይጥራሉ፡፡ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶችን በተመለከተ፣ በ1611 የኪንግ ጄምስን እትም ያዘጋጀው ኮሚቴ ያከናወነው የጠራ ተግባር በግልጽ የሚታይ ነው፡፡ ነገር ግን አሁን ያ ቋንቋ ዘመን አልፎበታል፡፡ ስለሆነም፣ አሁን ግሩም ትርጉሞች እየተዘጋጁ ወጥተዋል፡፡ ከፍተኛ ተቀባይነት ካገኙት የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች መካከል ሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርዥን፣ ኒው አሜሪካን ስታንዳርድ ባይብል፣ ኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን፣ ኒው እንግልሽ ባይብልና ኒው ኪንግ ጄምስ ቬርዥን ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ታላላቅ ምሁራን የሚገኙባቸው ኮሚቴዎች የሥራ ውጤቶች ናቸው፡፡ የናዛሪን ምሁራን የኤንአይቪና ኤንኤኤስቢ የትርጉም ኮሚቴ አባላት ሆነው ሠርተዋል፡፡

(የአማርኛ ትርጉሞችን በተመለከተ፣ ሰፊ ጥናት ባይደረግም እ.አ.አ. በ1962 ለታተመውና በቅርቡ «አዲሱ መደበኛ ትርጉም» በሚል ርእስ ለቀረበው እትም ጥሩ አስተያየቶች ሲሰጡ እንሰማለን፡፡)

## መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው?

አዎን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ሰዎች ስህተቶችን እንዳይፈጽሙ እንደጠበቃቸው እናምናለን፡፡ እነዚህ የእምነት መግለጫዎች ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት መግለጫዎችን በአመክንዮ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ይህም ሆኖ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት የሚያመለክቱ ብዙ ጠቋሚዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉትን መጠቃቀስ ይቻላል፡፡

- ከ2000 ለሚበልጡ ዓመታት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት በሕይወታቸው እንደተለማመዱ መስክረዋል፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሕይወትና ወደፊት ስለሚከሰቱት ነገሮች የተናገራቸው አሳቦች እውነት መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

በራሳችን ሕይወት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ብንታዘዘው ወይም ባንታዘዘው ስለሚከተሉን ነገሮች የተናገራቸው ነገሮች እውነት ሆነው እንደሚገኙ እንመለከታለን።

## መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ መንገዶች የሚተረጎመው ለምንድነው?

መጽሐፍ ቅዱስ ሰብአዊም መለኮታዊም ነው። ይህም ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ሊረዱት እንደሚችሉ ያሳያል። በመጀመሪያ ደረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ዓይነት የሥነጽሑፍ ቅርጾች እንዳሉና እያንዳንዱ የሥነጽሑፍ ቅርጽ የራሱ ዓላማ እንዳለው፣ ከዚህም የተነሣ በተለየ መንገድ መተርጎም እንዳለበት መገንዘብ አለብን። ይህንን አሳብ እስኪ እናብራራው። ክርስቶስ፣ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» ብሏል። ነገር ግን ሻማ ነኝ ወይም የመብራት ብርሃን ነኝ አላለም። ይህን ሲል ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት እርሱ ወደ ዓለም የሚያመጣው እውነት ግንዛቤን እንደሚፈጥር መጠቆሙ ነበር።

## መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ላጠና ይገባኛል?

ለእያንዳንዱ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን በአግባቡ ለመረዳት መማሩ ጠቃሚ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የሚያግዙ ብዙ የመመሪያ መጻሕፍት አሉ። የአፍሪካ ናዛሪን ህትመቶች የትኞቹን መጻሕፍት ልታገኝ እንደምትችል ሊያማክርህ ይችላል። ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያግዙ አንዳንድ መመሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን በተገቢው አመለካከት ጀምር። መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈሳዊ ቫይታሚን ክኒኖች ስብስብ ወይም ክፋውን የሚያርቅ ምትሃት ሳይሆን ቅዱስ መጽሐፍ ነው።
2. መጽሐፍ ቅዱስን ራስህ አጥናው። የማጥኛ መርጃዎች እገዛ ቢያደርጉልህም ለግል ጥናት ምትክ አይሆኑም።
3. አንድን ጥቅስ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላውን ታሪክ አንብብ። ጥቅሱን ለመረዳት ጥቅሱ የሚገኝበትን ዓውደንባብ መረዳቱ ጠቃሚ ነው።
4. ምንባቡን መርምረው። ምን ዓይነት ሥነጽሑፍ እንደሆነ መርምረህ እወቅ። ጠቃሚ ቃላትን ለይተህ አውጣ። መዋቅሩን አጥና። አሳቡን ለመረዳት እንድትችል ያሰባሰብሃቸውን መረጃዎች አደራጅ።
5. ጥያቄዎችን ጠይቅ። ምን፣ የት፣ እንዴት፣ ለምን እና ማን የሚሉትን ጥያቄዎች ብትጠይቅ ምንባቡን የበለጠ ትረዳዋለህ።
6. መልሶችህን ተርጉም። መጽሐፍ ቅዱስን በምታጠናበት ጊዜ ልትመልሰው የሚገባህ ጥያቄ፣ «ይህ ለእኔ ምን ትርጉም ይሰጣል?» የሚለው ነው።
7. መልሶችህን ፈትን። ከምንባቡ ጋር መጣጣማቸውን ለመገንዘብ ትችል ዘንድ ድምዳሜዎችህን ፈትናቸው። ከአጠቃላይ የመጽሐፍ

ቅዱስ የእውነት ገለጻ ጋር መጣጣማቸውንም አረጋግጥ:: ካልሆነ፣ ድምዳሜዎችህን እንደገና ከልሳቸው::

## መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን እንድረዳ ያግዘኛል?

ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስ በሚመጣበት ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራን ነግሮናል (ዮሐንስ 16:13):: ይህም መንፈስ ቅዱስ እውነት ከሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በስምምነት እንድንኖር ይረዳናል ማለት ነው:: በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንድንረዳ ያግዘናል ማለት ነው::

ጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጎን ለጎን ይሄዳሉ:: መንፈስ ቅዱስ እኛን በሚያስተምርበት ጊዜ የሚጠቀምበት የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ይኖረን ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ለማጥናት የራሳችንን ድርሻ መወጣት አለብን:: በተጨማሪም፣ መንፈስ ቅዱስ የምናጠናውን እንድንገነዘብ ይረዳን ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ ለጸሎት ጊዜ መስጠት አለብን:: ከመጽሐፍ ቅዱስ የማገኘው እውነት መጀመሪያ ከራሴ ሕይወት ጋር መዛመድ አለበት:: እውነቱን ከሌሎች ሕይወት ጋር ማዛመዱ የእኔ ሥራ አይደለም--ምንም እንኩዋን ይህን በፍቅር መንፈስ ላደርገው ብሞክርም::

## መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ለእኔ በእኩል ደረጃ አስፈላጊ ነውን?

ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ፣ በእኩል ደረጃ ልናከብረው ይገባል:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ጊዜያት ለተለያዩ ሁኔታዎች ይናገራል:: የስኬታማነት ምሥጢሩ ትክክለኛውን ነገር በትክክለኛው ጊዜ ማድረግ መሆኑን ከመጽሐፈ ምሳሌ እንረዳለን:: ስለሆነም፣ ለተወሰነ ጊዜና ለጠቅላላ ጊዜ የሚናገሩትን እውነቶች ልዩነት መመርመር ይኖርብናል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንደምንረዳው፣ እንደ አሥርቱ ትእዛዛት (ዘጸአት 20) ያሉ ምንባቦች ከሁሉም ሁኔታ ጋር ይዛመዳሉ:: በመጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን የሚመስሉ ብዙ ምንባቦች የሚገኙ ሲሆኑ፣ እነዚህ ለሕይወታችን እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በቤት ጣሪያ መከታ ስለማድረግ (ዘዳግም 22:8) የሚናገሩ ዓይነት ጥቅሶች እንዲህ ዓይነት ቤት ለሚገነቡ ሰዎች ብቻ የሚያገለግሉ መሆናቸውን ከጥናታችን መገንዘብ እንችላለን:: እንዲህ ዓይነቶቹ አሳቦች ሃላፊነታችንን በአግባቡ መወጣት እንዳለብን የሚያሳዩ ናቸው:: ስለሆነም፣ ቤትን በምንሠራበት ጊዜ በጣሪያ ላይ ለሚሠሩት ሰዎች ጥንቃቄ ማድረግ ሃላፊነታችን ይሆናል::

የመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ሌሎች እውነቶች ከአንድ ስፍራ ጋር የሚዛመዱ ከሆነ *አካባቢያዊ* ይባላሉ:: ከሁሉም ስፍራ ጋር የሚዛመዱ ከሆኑ *ሁሉንአቀፍ (ዩኒቨርሳል)* ይባላሉ:: ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚሠሩ ከሆነ *ጊዜያዊ*፣ ሁልጊዜም ተግባራዊ የሚሆኑ ከሆኑ *ዘመን የማይሽራቸው* ይባላሉ:: ይህንን በመንገድ ላይ ምልክቶች ማብራራት ይቻላል::

አካባቢያዊ- ለአንዲት ስፍራ ብቻ የሚሠራውን ምልክት ያመለክታል:: ሁሉንአቀፍ-የፍጥነት መቀነሻ ምልክት እስካልተደረገ ድረስ የፍጥነት ገደብ ደንብ በመላ አገሪቱ ውስጥ ይሠራል:: ጊዜያዊ-ስለ ጥገና የሚያስጠነቅቁ ምልክቶች:: ዘመን የማይሽራቸው-የዳገት ምልክቶች::

## ለእውነት መታዘዝ

አንድ ሰው ዕድሜልኩን መጽሐፍ ቅዱስ እያጠና ሲቆይና ሙሉ አሳቡን ላይረዳ ይችላል:: የህይወት ምሥጢሩ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን እውነቶች ሁሉ ማወቅ አይደለም:: እውነቶቹን ሁሉ ለማወቅ ረዥም ዘመናትን ይጠይቃል:: የፍሬያማ ኑሮ ምሥጢሩ መንፈስ ቅዱስ የሚገልጽልንን እውነቶች ተግባራዊ ማድረግ ነው:: በዚህ መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ስኬታማ ጉዞ ልንመራና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ልናድግ እንችላለን:: እግዚአብሔር ለሚያሳየን እውነቶች አለመታዘዝ የኋላ ኋላ ወደ መንፈሳዊ ሞት ይመራናል:: ስለሆነም፣ የምናውቀውን እውነት ልንታዘዝ ይገባል::

# ምዕራፍ 6
# ናዛሪኖች በጸጋ ያድጋሉ

## መንፈስ ቅዱስ በጸጋ እንድናድግ ይረዳናል
የክርስትና ሕይወት ባለበት የሚረግጥ አይደለም። ሁልጊዜም ምርጫዎች ያጋጥሙናል። ትክክለኛውን እርምጃ ለመውሰድ ከመረጥን በመንፈሳዊ ሕይወታችን እናድጋለን። ትክክል ያልሆነውን እርምጃ ለመውሰድ ከመረጥን ግን ከእግዚአብሔር እንርቃለን። መንፈስ ቅዱስ የተሰጠን ትክክለኛ ምርጫዎችን ለማድረግ እንዲረዳን ነው። የሐጢአትን ይቅርታ ካገኘንና መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ እንዲሠራ ከጋበዝን ፍሬያማ ተግባር ልናከናውን እንችላለን። ከሁሉም የላቀ ዕድገት የሚታይብን ከተቀደስን በኋላ ነው።

## መንፈሳዊ ዕድገት ስንል ምን ማለታችን ነው?
መንፈሳዊ ዕድገት የባህርያችን፣ እንዲሁም ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት አዎንታዊ ግንባታ ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ስለሚያዩኝ ብቻ ሳይሆን በውስጣዊ ማንነቴ መልካም እንድሆን ይጠብቅብኛል። በሕይወቴ ውስጥ የሚከሰተው የመንፈስ ፍሬ ዕድገት መንፈሳዊ ዕድገቴን ያመለክታል።

## መንፈሳዊ ታላቅነት ምንድነው?
ክርስቶስ፣ «ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን» ብሏል (ማቴዎስ 20:26)። ከፊልጵስዩስ 2:1-11 እንደምናነበው፣ ክርስቶስ ባሪያ ለመሆን ሲል ከመንግሥተሰማይ ወርዶ ወደ ምድር መጥቷል። እኛም እንደርሱ እንድንሆን ይፈልጋል። መልካም አገልጋይ የሚያገለግላቸው ሰዎች ከሁሉም ወደላቀ ደረጃ እንዲደርሱ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ማዚቱሌ ይህንን፣ «የመጀመሪያው ሃላፊነቴ ሌላው እንዲሳካለት ማገዝ ነው» ሲሉ ገልጸዋል።

## አገልጋይ መሆን ሌሎች ሕይወታችንን እንዲመሩ መፍቀድ ነውን?
ክርስቶስ ለሌሎች በጎነት ከፍተኛ ተግባር እንድናከናውን ይፈልጋል። ይህም ሆኖ፣ ልንኖር የሚገባን በመንፈስ ቅዱስ እንጂ በሌሎች ሰዎች ምሪት አይደለም። በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 «ፍቅር» የተባለው ይሄው ነው። በተጨማሪም፣ ክርስቶስ ዓላማውን ለኛ እንዳካፈለና ከዚህም የተነሣ ወዳጆቹ እንጂ ባሮቹ እንዳልሆንን ገልጾአል (ዮሐንስ 15:15)። ስለሆነም፣ ችሎታዎቻችንንና ፈጠራዎቻችንን ሁሉ በመጠቀም ለነዚህ ዓላማዎቹ

መሳካት ተግተን ልንሠራ ይገባል። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ መሥራት ነው። ይህም ክርስቶስ ስለ አገልጋይነት የሚናገረው አሳብ ትእዛዛትን ከመቀበል የበለጠ መሆኑን ያሳየናል። ይህም በዙሪያዬ ያሉትን ሰዎች በጎነት የሚሻ የአኗኗር ስልት ነው።

## እንዴት በጸጋ ላድግ እችላለሁ?

እግዚአብሔር ዓይኖቹን በኛ ላይ በማኖናት ይመራን ዘንድ በሚገባ እንድናውቀው ይሻል (መዝሙር 32:8)። መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ዓይነት ግንኙነት እንድንመራ ይረዳናል። እርሱ ራሳችንን በመግዛት እንድናድግ ይረዳናል። የሕይወት ምሪትንም ይሰጠናል።

ራስን መግዛት ማለት የምንመርጣቸውን ነገሮች መቆጣጠር ማለት ነው። አንዳንድ ነገሮችን መቆጣጠር እችላለሁ። በዚህ ጊዜ መልካሙን መምረጥ ይኖርብኛል። ሌሎች ነገሮችን መቆጣጠር አልችልም። በዚህ ጊዘ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን ምላሽ እንድሰጥ ሊረዳኝ ይችላል። ይህም የአኗኗር ዘይቤያችን እንደ አምልኮ፣ ጸሎት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና የቤተክርስቲያን ህብረት የመሳሰሉትን መልካም ተግባራት እንዲያሳይ ማድረግ ማለት ነው። በተጨማሪም፣ አዋኪ ነገሮችን ማስወገድ ማለት ነው። ክፉ ወይም አውዳሚ መዝናኛዎችን፣ ተግባራትን፣ መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችን እናስወግዳለን። ጓደኞቻችንን በጥንቃቄ እንመርጣለን። በሐኪም ከሚታዘዙት በስተቀር የትኞቹንም መደሃኒቶችና ሰዖች ከመጠቀም እንቆጠባለን። ብዙ ሰዎች እንደ አልኮልና ኒኮቲን (በሲጋራና በሌሎችም ነገሮች ውስጥ የሚገኝ አእምሮ አነቃቂ ቅመም) የመሳሰሉትን ነገሮች መጠቀማቸው ተቀባይነት እንዳላቸው አያመለክትም። ራሳችንን እንድንገዛ የሚረዳን መንፈስ ቅዱስ ነው።

ራስን መግዛት ማለት ስሜቶቻችንና ፍላጎቶቻችንን መቆጣጠር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ወሲባዊ ፍላጎቶቻችንን ለመቆጣጠር የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና ሀይል እንደሚያስፈልገን ገልጾአል (1ኛ ተሰሎንቄ 4:3)። ያዕቆብ መንፈስ ቅዱስ ካልረዳን አንደበታችንን ልንገዛ እንደማንችል አስረድቷል (ያዕቆብ 3)። የእግዚብሔር ሕግ ብዙ መመሪያዎችን የሚሰጠን ሲሆን፣ በልባችን ውስጥ ያለው የርሱ ፍቅር ሕጉን ለመጠበቅ እንድንፈልግ ያነሳሳናል። መንፈስ ቅዱስ ስሜቶቻችንንና ፍላጎቶቻችንን እንድንገዛና ትክክለኛ ምርጫዎችን እንድናደርግ ይረዳናል።

ራስን መግዛት ማለት ሀብቶቻችንን መቆጣጠር ማለት ነው። ጊዜያችንን፣ ችሎታችንንና ሀብታችንን ለምንጠቀምበት ሁኔታ ተጠያቂነት እንዳለብን መገንዘብ ይኖርብናል። እነዚህን ነገሮች የምንጠቀምበት መንገድ ለባህርያችን መጠናከርና በዙሪያችን ላሉት በምናደርገው አገልግሎት አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት።

ምሪት እግዚአብሔር የኛንና የሌሎችን ሰዎች ሕይወት በሚገነቡ ነገሮች ላይ ተሳታፊዎች እንድንሆን የሚፈልግ መሆኑን ያሳያል:: አዎንታዊ ተሳትፎ አሉታዊና የትችትን መንፈስ ያዳክማል:: መንፈስ ቅዱስ ምንም ዓይነት የመራርነት ሥር በሕይወታችን ውስጥ እንዳያድግ አጥብቆ ግድ ይለዋል:: (ዕብራውያን 12:15)::

## ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንዴት መሥራት ይኖርብኛል?

ከዳንሁና ከተቀደስሁ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በሕይወቴ ውስጥ ውጤታማ ተግባር እንዲያከናውን ለመፍቀድ ላደርጋቸው የሚገባቸው ሁለት ነገሮች አሉ:: ከነዚህም የመጀመሪያው ለጸሎትና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ መውሰድ ሲሆን፣ ሁለተኛው የክርስቶስ አካል የሆነችው የቤተክርስቲያን ክፍል ሆኜ መኖር እንዳለብኝ ማረጋገጥ ነው::

## የምጸልየውና መጽሐፍ ቅዱስን የማጠናው ለምንድነው?

ጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጎን ለጎን ይሄዳሉ:: መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናው እግዚአብሔር የሚናገረውን ለመስማት ነው:: ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ ተግባቦት ነው::
ጸሎት አምስት ገጽታዎች አሉት:: እነዚህም፣ ውዳሴ፣ ምስጋና፣ ኑዛዜ፣ ምልጃና ልመና ናቸው:: እግዚአብሔር መልካምና ለሰዎች የሚያስብ አምላክ ስለሆነ ሊወደስ ይገባል:: ምስጋና አመለካከት እንጂ የትህትና ቃላትን ማፈትለክ ብቻ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እንድናመሰግን ያበረታታናል (1ኛ ተሰሎንቄ 5:18):: እግዚአብሔር እንዲያድነንና እንዲቀድሰን በምንጠይቅበት ጊዜ እንናዘዛለን:: እግዚአብሔር በቀላሉ ከቤተሰቡ ውስጥ ለይቶ አያስወጣንም:: ነገር ግን በመጥፎ ተግባራችን የምንጸና ከሆንን፣ ከርሱ የተለየን እንሆናለን:: ምልጃ ስለ ሌሎች የምናቀርበው ጸሎት ነው:: ልመና ከእግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ነገር መጠየቅ ነው:: እግዚአብሔር እርሱን እንድንጠይቅ ጋብዞናል:: እርሱ ለጋሽ አምላክ ሲሆን፣ ራስወዳድነትንና ስግብግብነትን ይጠላል::

## በ«ክርስቶስ» ስም መጠየቅ ማለት ምን ማለት ነው?

«በክርስቶስ ስም» የሚሉት ቃላት እግዚአብሔር ሰዎች የሚፈልጉትን ለማድረግ የሚገደድባቸው ምትሃታዊ ቀመሮች (ፎርሙላዎች) አይደሉም:: ጸሎት ሰው አሳቡንና ፈቃዱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያስገኝ/እንዲያስልፍ ይረዳዋል:: ክርስቶስ «ያንተ ፈቃድ ይፈጸም» አለ እንጂ «እግዚአብሔር ሆይ የኔን ፈቃድ መፈጸም አለብህ» አላለም:: ዮሐንስ 14:14፣ «በስሜ አንዳች ነገር ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ» ይላል:: ይህም ከክርስቶስ ባህርይ (ስም) ጋር የሚጣጣም ነገር ከጠየቅን እንደሚያደርገው

ያሳያል። ክርስቶስ የሚፈልገውን ካወቅን፣ ሕይወታችንን ከሕይወቱ ጋር በማስተካከል ከዚህ ሁኔታ ጋር በሚስማማ መልኩ ከጠየቅን፣ «በስሙ» ጠይቀናል ማለት ነው።

## በክርስቶስ አካል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ይመራናል

ቤተክርስቲያን የክርስቶስ አካል ነች። አንድ እጅ ከተቆረጠ በኋላ ለብቻው በሕይወት ሊኖር እንደማይችል ሁሉ አንድ ክርስቲያንም ከሌሎች ክርስቲያኖች ተለይቶ ሊኖር አይችልም። የአካል ክፍል መሆን ማለት አብሮ ማምለክ፣ ማጥናት፣ መጸለይና መሥራት ማለት ነው። አካል እያንዳንዱን ክፍል የመደገፍና የማበረታታት አስተዋፅኦ ቢያበረክትም እንደ አንድ አካል መሥራት ይኖርበታል። አንዱ አካል ሲጎዳ ጠቅላላው ሰውነት ይጎዳል። አንዱ አካል ሲበረታ ጠቅላላው ሰውነት ብርታትን ያገኛል።

እርስበርሳችን እንረዳዳ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ለአካሉ ክፍሎች ስጦታዎችን ሰጥቷል (ኤፌሶን 4:12)። ጳውሎስ የሥልጣን ስጦታውን በመጠቀም ቤተክርስቲያንን አነጸአል (1ኛ ቆሮንቶስ 10:8)። እግዚአብሔር እኛን ለመርዳት ሲል መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሰጣቸውን (እንደ መጋቢዎቻችና መሪዎቻች ያሉትን) ሰዎች ምሪት ለመቀበል ባንፈልግ፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንገፋለን።

## የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች ምን ምንድናቸው?

በክርስቶስ አካል ውስጥ ተግባራዊ የምናደርጋቸውና ሥርዓቶች ብለን የምንጠራቸው ሁለት ነገሮች አሉ። እነዚህ የተቀደሱ ተምሳሌቶች ናቸው። ይህ ማለት ግን ምትሃታዊ ባህርያት አሏቸው ማለት አይደለም። እዚህን ሥርዓቶች መፈጸሙ አያድነንም። እነርሱም ቅዱስ ቁርባንና ጥምቀት ናቸው።

ቅዱስ ቁርባን የክርስቶስን ሕይወትና ሥራ ያስታውሰናል። ክርስቶስን የሚወድ ሰው ክርስቶስ ለኛ ሲል ስለፈጸመው የመሥዋዕትነት ሞቱ የሚያስረዳውን የእንጀራና የጽዋ ሥርዓት መፈጸም ይኖርበታል (1ኛ ቆሮንቶስ 11)። በናዛሬን ቤተክርስቲያን ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ማህበረምእመናን ቅዱስ ቁርባን እንዲወስዱ እንመክራለን።

ጥምቀት ሰውን ሊያድን አይችልም። ክርስቶስ በዮሐንስ አማካኝነት የውሃ ጥምቀት ወስዷል። እኛም የርሱ ተከታዮች መሆናችንን ለማሳየት በውሃ መጠመቅ እንዳለብን አዞናል። አንድ የተጠመቀ ሰው ወደ መንግሥተሰማይ ሊገባ የሚችለው የክርስቶስን አዳኝነት ከተቀበለ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት መጠመቅ እንዳለብን ስለማይናገር የትኞቹንም የጥምቀት ዓይነቶች እንቀበላለን። እነዚህም፣ መርጨት፣ ማፍሰስና መንከር ናቸው። ከነዚህ ሁሉ በጣም የተለመደው የጥምቀት

ዓይነት መንከር ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የልጆችን መጠመቅ ስለማይከለክል እኛም አንከለክልም:: ልጆችን ማስጠመቅ ወላጆች ክርስቶስን እየተከተለ እንዲያድግ የሚፈልጉ መሆናቸውን ከማሳየት ውጭ ደህንነትን ሊያስገኝ አይችልም:: ብዙውን ጊዜ ልጆችን ለጌታ አሳልፈን እንሰጣለን::

## እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ሁሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች እንዲሆኑለት ይፈልጋል?

ክርስቶስ ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲከተሉት ይጠራል:: እርሱን እንድንመስልና ፈቃዱን እንድንፈጽም ይፈልጋል:: በተጨማሪም ክርስቶስ በሕይወታችን የፈጸመው ተግባር ምስክሮች እንደሆንን ይናገራል:: ይሁን እንጂ እርሱ ሁሉም ሰው ሰባኪ፣ ወንጌላዊ ወይም ሚሲዮናዊ እንዲሆን አይጠራም::

**ምስክሮች:** ሐዋርያት 1:8 ደቀመዛሙርት የክርስቶስ ምስክሮች እንደሚሆኑ ይናገራል:: መመስከር ማለት የምታውቀውን እውነት በይፋ መናገር ማለት ነው:: ሕይወታችንና ቃላችን ለእግዚአብሔር ፍቅርና በሕይወታችን ውስጥ ለፈጸመው ለውጥ ያለሃፍረት ይመሰክራሉ::

**የስብከት ጥሪ:** እግዚአብሔር ከተከታዮቹ አንዳንዳቹ ከሁሉም በላይ ለመልካሙ የምሥራች ብሥራት ቅድሚያ እንዲሰጡ በልባቸውና በአእምሯቸው ጥሪውን ያሳድራል:: ለነዚህ ሰዎች ተገቢውን ስጦታና ጸጋ ይሰጣቸዋል:: እግዚአብሔር ጥሪውን እንድንቀበል ብቻ ሳይሆን ጥሪውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለውን ሥልጠና በመቀበል ራሳችንን እንድናዘጋጅም ይፈልጋል::

**የሚሲዮናዊነት ጥሪ:** እግዚአብሔር ከተከታዮቹ አንዳንዶቹ ቃሉን ወደ ምድር ሁሉ በመሄድ እንዲሰብኩ ይጠራቸዋል:: እንዲህ ዓይነት ሰዎች እንደ አስፈላጊነቱ በብዙ መንገዶች ሊያገለግሉ ይችላሉ:: ስለሆነም፣ እንዲህ ዓይነቱን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልኩ መሠልጠን ይኖርባቸዋል:: ናዛሬኖች ሁሉ ለታላቁ ተልእኮ መፈጸም ለሚያግዘው ለዚሁ አገልግሎት ራሳቸውን ክፍት ማድረግ ይኖርባቸዋል (ማቴዎስ 28:19-20)::

## የተቀደሱ ክርስቲያኖች ችግሮች ይገጥሟቸዋል?

ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ሲጸልይ (ዮሐንስ 17) በዚህ ዓለም ውስጥ እያለን እንድንጠበቅ እንጂ ከዚህ ዓለም ችግሮች እንድንከለል አልጠየቀም:: ክርስቶስ አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግሥት ብንሻ (ማቴዎስ 6:33) ዕለታዊ ፍላጎቶቻችን እንደሚሟሉ ቃል ገብቷል:: ክርስቶስ ባለ አደራዎች

አድርጎናል፡፡ ባለጸጎች ሊያደርገን ግን ቃል አልገባም፡፡ ተከታዮቹ እንድንሆን የሀብት፣ የጤንነት ወይም የሀይል ጉቦ አልሰጠንም፡፡

የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ሰላምንና ደስታን ያመጣል፡፡ ይሄ ጤናማ ነገር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግጋት መጠበቁ ለጤንነታችን አስተዋጽኦ ቢያደርግም፣ እግዚአብሔር ምንም ዓይነት በሽታ እንደማይደርስብን ቃል አልገባልንም፡፡ ችግሮች በሚገጥሙን ጊዜ መጥፎ መንፈስ ከውስጣችን እንዳይጠነሰስ ለመርዳት ቃል ገብቷል፡፡ እግዚአብሔር ይረዱን ዘንድ ዶክተሮችን አስነሥቷል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን በተአምራዊ መንገድ በመዳሰስ ይፈውሳል፡፡ ከምትሃት ወይም ከዲያብሎስ ዘንድ ፈውስን መሻት ስህተት መሆኑን እናምናለን፡፡ እግዚአብሔርን ብንታዘዝና የርሱን ጊዜ ብንጠብቅ፣ ጉዳታችንን ተጠቅሞ ሕይወታችንን ሊያጠናክርና ሌሎችን ሊያረታታ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ 7
# የሕይወትን ጉዳዮች መጋፈጥ

በተወሳሰበ ዓለም ውስጥ ስለምንኖር እግዚአብሔርን ከማያገለግሉና ብሎም እርሱን ከሚቃወሙ ሰዎች ጋር መኖራችን የግድ ይሆናል:: ስለሆነም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለሚያጋጥሙን ለነዚህ ችግሮች መመሪያዎችን ይሰጠናል::

## ለግላዊ አኗኗር የእግዚአብሔር ሕግጋት ምን ምንድናቸው?

ክርስቶስ ሕግጋትን በነዚህ ቃላት አጠቃሏል: «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ:: ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት:: ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፣ እርስዋም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት:: በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም ተሰቅለዋል» (ማቴዎስ 22:37-40):: ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 13 ውስጥ የፍቅርን ትርጉም በሚገባ አብራርቷል:: ፍቅር የእግዚአብሔርን ደንቦች ሁሉ የሚያስተሳስር መርህ ነው:: በዘጸአት 20 ውስጥ የሚገኙት አሥርቱ ትእዛዛት የእግዚአብሔር ህግጋት አጭር ማጠቃለያዎች ናቸው::

## ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ሕግጋት መጠበቅ አለባቸው?

እግዚአብሔር የሰጣቸው ሕግጋት የዕለት ጉዳዮቻችንን ለመጋፈጥ የሚያግዙን መመሪያዎች ናቸው:: ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው የደንቦች ሁሉ መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ውስጥ እንዲሰፍን ነው:: እርሱ በእግዚአብሔር መንገድ የምንኖር ሰዎች እንድንሆን አድርጎ ይለውጠናል:: አሥርቱን ትእዛዛት በሚገባ ብንመረምር አሁን ላለንበት ሁኔታ ለሚገጥሙን ነገሮች ተገቢ ምላሽ እንድንሰጥ ያደርጉናል::

## ሌሎች አማልክት አይኑሩልህ

ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ አምላክ የለም:: እርሱ ከቤተሰብ፣ ከአገር፣ ወይም ከሀብት በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው አምላክ ነው:: ሊመለክ የሚገባው እርሱ ብቻ ነው:: ከጦር መሣሪያዎች፣ ከሀብት ወይም ከሀይል ደህንነትን ለማግኘት የምናደርገው ጥረት ትክክል አይደለም:: ደህንነትን፣ ሀይልንና ሕይወትን ሊሰጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እርሱ በመንፈሳዊና ቁሳዊ ዓለማት ውስጥ የአሁኑንና የዘላለሙን ይቆጣጠራል::

## ማንኛውንም ጣዖት ለራስህ አታድርግ

ጣዖታትና የተቀረፀ ምስሎች ሰዎች አማልክት የሚፈልጓቸውን ነገሮች ያደርጉ ዘንድ ተጽዕኖ ለማሳደር ወይም አምላክን ወደራሳቸው ግንዛቤ ዝቅ

ለማድረግ የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች ናቸው:: እግዚአብሔር ይህ በፍጹም ስህተት እንደሆነ ይናገራል:: እግዚአብሔር ሰዎች የሚፈልጉትን እንዲያደርግ የሚያስገድደው ምንም ዓይነት ምትሃት የለም:: ሰዎች የእግዚአብሔርን ዓቅም የሚወስኑበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም:: «ቅዱሳን» ያማልዱልን ዘንድ የሚቀርበው ጸሎት የጣዖት አምልኮ ነው:: በመናፍስት ዓለም ውስጥ ያማልዱልን ዘንድ ለአያት ቅድማያቶቻችን መንፈስ የሚቀርበውም ጸሎት ያው የጣዖት አምልኮ ነው:: እግዚአብሔር ይህ ትክክል አይደለም ይላል:: ሰዎችን ማስታወስና ከሕይወታቸው መማር ስህተት ባይሆንም፣ እግዚአብሔር የምንፈልገውን እንዲያደርግልን ለማግባባት በነርሱ ልንጠቀም አንችልም::

## የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ

እግዚአብሔር ክብር የሚገባው አምላክ ነው:: ስሙን ጠርተን ተገቢ ያልሆኑትን ነገሮች ልንናገር አይገባንም:: የእግዚአብሔርን ስም ለርግማን ልንጠቀም አይገባንም:: «እግዚአብሔር ይህንን እንዳደርግ ነገረኝ» በሚል ሰበብ የራስን ምኞት መፈጸሙም ትክክል አይደለም:: እውነትን የሚናገሩ ለማስመሰል በእግዚአብሔር ስም መማል ለሌላ ጊዜ የምንዋሽ መሆኑን ያመለክታል:: የእግዚአብሔርን ስም ተጠቅሞ ሰዎች የምንፈልገውን ነገር እንዲያደርጉ ማግባባቱ እግዚአብሔርን አያስከብረውም::

ጥንቆላ «መንፈሳዊ ሀይልን» በመጠቀም እግዚአብሔር ወይም ሰዎች የምንፈልጋቸውን ነገሮች እንዲያከናውኑ ለማድረግ መሞከር ነው:: ይህ ለምንም ዓይነት ዓላማ ቢታሰብም ክፉ ተግባር ነው:: እግዚአብሔር የትኛ ውንም ዓይነት የጥንቆላ ሥራ እንደሚቃወም ከቃሉ እንረዳለን (ዘጸአት 22:18፣ ዘዳግም 18:10፣ ሚክያስ 5:12፣ ገላትያ 5:20):: ይህ እግዚአብሔርን እንደመሳደብ ነው::

## የሰንበትን ቀን ትቀድሳት ዘንድ አስብ

የዕብራውያን መጽሐፍ ሰንበት ለክርስቲያኖች ምን ዓይነት አስፈላጊነት እንዳለው ያብራራል:: ሰንበት ለሙሉ መዳን በእግዚአብሔር ማረፋችንን (መታመናችንን) የሚያሳይ ተምሳሌት ነው:: ዕብራውያን ምዕራፍ 3 እና 4 እስካልተቀደሰን ድረስ ወደዚህ ዕረፍት እንዳልገባን ያስረዳሉ:: እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲያገኝ የሚፈልገውን ዕረፍት የምናውቀው ስንቀደስ ብቻ ነው:: ይህም አራተኛው ትእዛዝ፣ «ሕይወትህን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ልትሰጥና መንፈስ ቅዱስ እንዲቀድስህ ማድረግ እንዳለብህ አስታውስ» ተብሎ ሊነበብ እንደሚችል ያሳያል::
ሰንበት እግዚአብሔር ለራሱ ክብር የለየው ተምሳሌታዊ ዕለትም ነው:: ይህም ለአምልኮና ከእግዚአብሔር ለመማር የተለየ ዕለት ነው:: ክርስቶስ

ይህ ቀን ለሰው ጥቅም እንደተፈጠረ ገልጾአል (ማርቆስ 2:27)። በተጨማሪም፣ ይህ ቀን መልካም ተግባር የሚፈጸምበት እንደሆነ ተናግሯል (ማቴዎስ 12:12)። ክርስቲያኖች ይህንን ቀን ከቅዳሜ ወደ እሑድ ለውጠውታል። ለዚህም ምክንያቱ እሑድ ክርስቶስ ከሞት የተነሣበት «የጌታ ቀን» መሆኑ ነው። በዚህ ቀን እግዚአብሔርን እያስከበርንና ከርሱ እየተማርን ልንውል ይገባል።

## አባትህንና እናትህን አክብር

ታላላቆቻችንን ማክበር የተረጋጋና ጽኑ ማህበረሰብ ይፈጥራል። አለመከባበር ግን ሁከትን ይፈጥራል። በትዕዛዙ ውስጥ እግዚአብሔር በምድር ላይ የአክባሪዎቹን ዕድሜ እንደሚያረዝም በአፅንኦት ገልጾአል (ዘጸአት 20:12)።

## ክርስቲያኖች ሰው አይገድሉም

ክርስቶስ በማቴዎስ 5:21 እንደገለጸው፣ የግድያ ሥሩ ጥላቻ ነው። በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ይህንን ሕግ ብንጠብቅ፣ ከጥላቻም ሆነ ከግድያ ነጻ እንሆናለን። ይህ ሊሆን የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ልባችንን እንዲያነጻና በፍቅሩ እንዲሞላን ከጠየቅነው ብቻ ነው።

## ክርስቲያኖች አያመነዝሩም

*ዝሙትና ሴሰኝነት*: በማቴዎስ 5:27-32 ክርስቶስ ዝሙት ከምኞት እንደሚጀምር በመግለጽ ከዚህ ዓይነቱ ተግባር እንድንቆጠብ ይመክረናል። ጳውሎስም ወሲባዊ ፍላጎታችንን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ለማስገዛት መቀደስ እንዳለብን ገልጾአል (1ኛ ተሰሎንቄ 4:3)።

*ፍችና ብዙሃ ጋብቻ*: መጽሐፍ ቅዱስ ጋብቻ ሊፈርስ የማይችል የተቀደሰ ትስስር እንደሆነ ያስረዳል። እግዚአብሔር «መፋታትን እጠላለሁ» ብሏል (ሚልክያስ 2:16)። ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት የሚጣመሩበት ሥርዓት ነው (ማርቆስ 10:8)። ይህም ለወንድ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት የእግዚአብሔር ዕቅድ አለመሆኑን ያስረዳል። ስለሆነም፣ የናዝሬት ቤተክርስቲያን በፍችና ብዙሃ ጋብቻ (ከአንድ በላይ የትዳር ጓደኛ መያዝ) ላይ የጠበቀ አቋም ትይዛለች (መምሪያ፣ አንቀጽ 34)።

*ቤተሰብ*: ጋብቻ ለባል፣ ለሚስትና ለልጆች ሰላማዊ ቤተሰብን መፍጠር አለበት። ባሎች ሚስቶቻቸውን እንዲወዱና እንዲንከባከቡ ተመክረዋል (ኤፌሶን 5:25)። ሚስቶች ባሎቻቸውን ሊያከብሩ (ኤፌሶን 5:33)፣ ልጆችም ለወላጆቻቸው ሊታዘዙ ይገባል (ኤፌሶን 6:1)።

**ውርጃ:** የናዛሪን ቤተክርስቲያን ውርጃ ትክክል የሚሆንባቸው ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ብትገነዘብም፣ ሆን ተብሎ የሚካሄደውን ውርጃ እንቃወማለን (መምሪያ አንቀጽ 35)::

**ግብረሰዶማዊነት:** መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም ዓይነት ወሲባዊ እርኩሰቶች ይቃወማል (ሮሜ 1:26፣ 27):: እንደዚህ ዓይነት ተግባራት በፍጹም ከክርስትና ጋር የማይጣጣሙ አይደሉም (መምሪያ አንቀጽ 36)::

**ወሲብ ቀስቃሽ ጽሑፎች (ፖርኖግራፊ):** ይህ የማህበረሰቡን ሥነምግባራዊ ህይወት የሚያበላሽ ክፉ ተግባር ስለሆነ፣ እንዲህ ዓይነቶቹን ተግባራት በየትኞቹም ተገቢ መንገዶች እንቃወማለን (መምሪያ አንቀጽ 904.9)::

## አትስረቅ

ክርስቲያን ሆኖ መስረቅ አይቻልም:: ሰብሮ በመግባትም ሆነ በማታለል የስርቆትን ተግባር መፈጸሙ ትክክል አይደለም:: እግዚአብሔር ከሕዝቡ ታማኝነትን ይጠይቃል::

## በሐሰት አትመስክር

ክርስቶስ፣ «ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን:: ከነዚህ የወጣ ከክፉ ነው» ብሏል (ማቴዎስ 5:37):: እውነተኝነታችን ከቶውንም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ መሆን የለበትም:: ፍቱን መሆን አለበት:: ክርስቲያኖች እውነትን መናገር አለባቸው:: የሰውን ስም ሊያጎድፉ፣ ሊያሙ ወይም ስለ ምንም ነገር ሊዋሹ አይገባም:: አንደበትን ሊገራ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (ያዕቆብ 3)::

## አትመኝ

ምኞት የሌላ ሰው ንብረት የሆነውን ነገር የራስ ለማድረግ መፈለግ ነው:: ይህም የአገልጋይነት ተቃራኒ ነው:: እውነተኛ አገልጋይ ሌሎችን ለመርዳት እንጂ ከነርሱ ለመውሰድ አይፈልግም:: ምኞት መልካምን ስም፣ ቤተሰብንና ሕይወትን ያጠፋል:: መንፈስ ቅዱስ የሌሎችን የምንመኝ ሳንሆን የምናገለግል ሰዎች እንድንሆን ሊረዳን ይፈልጋል::

## ቤተክርስቲያን ድምዕዋን ያሰማችባቸው ሌሎች ጉዳዮች

**ሰብአዊ ነጻነት:** *ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ነጻነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሰው ክብርና የሕሊና ቅድስና ጽንሰአሳቦች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን እናምናለን:: ምእመኖቻችን እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽንሰአሳቦች*

በመደገፍ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እናበረታታቸዋለን (መምሪያ 904.5)::

## ትምህርት

ትምህርት ለሁሉም ሰው መዳረስ እንዳለበት እናምናለን:: የህዝብ ትምህርት ክርስቲያናዊ መርሆችን በሚያንጸባርቁ የቤትና የቤተክርስቲያን ትምህርቶች መታገዝ እንዳለበት እናምናለን (መምሪያ 32.5)::

**ዘረኝነትና መድልዎ:** እግዚአብሔር ሰዎችን ከአንድ ደም እንደፈጠረ እናምናለን:: የሕግን፣ የትምህርትንና የሥራ ዕድሎችን በመጠቀሙ ረገድ ሰዎች ሁሉ እኩል ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል:: ናዛሪኖች ያለ ምንም የዘር ወይም የቀለም ልዩነት የትኛውንም ግለሰብ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል ሊያደርጉ ይችላሉ (መምሪያ 904:3፣ የጎሳዊ ጉዳዮች መማክርት ቦርድ::)

**መድሃኒቶች:** (ዕፆች) በህክምና ዶክተር ከሚታዘዘው በስተቀር መድሃኒቶችን መጠቀም ተገቢ እንዳልሆነ እናምናለን:: የትኛውንም የትምባሆና የአልኮል አጠቃቀምና አመራረት እንቃወማለን:: እነዚህ ነገሮች አደገኛ ዕፆች ናቸው (መምሪያ 33.5፣6)::

**ምሥጢራዊ ማህበራት:** ምሥጢራዊነት የክርስቲያናዊ ታማኝነትና እውነት መርህ የሚቃረን ተግባር ነው:: ናዛሪኖች ምሥጢራዊ ቡድኖችን አይደግፉም (መምሪያ 33:3)::

**ቁማርና ሎተሪ** በየትኛውም መልኩ እግዚአብሔር ከሕዝቡ የሚፈልገውን ሃላፊነት ያለበት አኗኗር ያንድላሉ:: እንዲህ ዓይነት ልምምዶችን እንቃወማለን (መምሪያ 33:2)::

**መዝናኛ:** በሥነጽሑፍ፣ ቴሌቪዥን፣ ሬድዮ፣ ወዘተ. አማካኝነት ክፉ መርሆች ሕይወታችንን እንዳይቆጣጠሩ፣ ናዛሪኖች የመዝናኛን ዓለም በጥንቃቄ መመርመር ይኖርብናል (መምሪያ 33.1)::

**ቤተክርስቲያንና መንግሥት:** እግዚአብሔር መንግሥት በማህበረሰቡ ውስጥ ሥርዓትንና ሰላምን እንዲያሰፍን አዟል:: «ለቄሣር የሚገባውን ለቄሣር መስጠት» የናዛሪኖች ሃላፊነት ነው:: እንዲሁም፣ በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ በመንግሥት ፊት የጽድቅን መመዘኛ ማስጠበቁ የኛ ሃላፊነት ነው (መምሪያ 902፣ 4፣5)::

**ቤተክርስቲያንና ለውጥ**፡ በዓለም ውስጥ ነገሮችን ለማስተካከል ሲባል የሚካሄደውን ጭካኔያዊ ተግባር እንቃወማለን። ክርስቶስ ሰዎችን ለመለወጥና ለዘላለማዊ ህይወት ለማዘጋጀት እንደመጣ እናምናለን። ስለሆነም፣ ክርስቲያኖች ማህበረሰቡን በመለወጡ ተግባር ላይ ሊሳተፉ ይገባል። እንዲህ ዓይነቱ ለውጥ የግለሰቡን ውስጣዊ ሕይወት ከለወጠ እጅግ ውጤታማ ነው። በጆን ዌስሊ የተካሄው መነቃቃት በእንግሊዝ አገር ከፍተኛ ለውጥ እንዳስከተለ የታሪክ ምሁራን አጢነዋል። በዚህም ለውጥ ምክንያት የባሪያ ፍንገላ፣ ልጆችን ማሠራትና ሌሎችም የበደል ተግባራት ሊወገዱ ችለዋል። በ1850ዎቹ አጋማሽ ላይ የተካሄደው የቅድስና መነቃቃት በአሜሪካ የባሪያ ፍንገላ እንዲቆም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

# ምዕራፍ 8
# ቤተክርስቲያን

## ቤተክርስቲያን እንዴት ተመሠረተች?

ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በበዓለ ሃምሳ ቀን ሲሆን፣ ይህም የተከናወነው መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ተከታዮች ላይ በወረደና ታላቅ የክርስቶስ አካል አድርጎ ባጣመራቸው ጊዜ ነው:: ይህንንም የክርስቶስ አካል ጥምረት ቤተክርስቲያን ብለን እንጠራለን::

የቤተክርስቲያን ሥር የሚገኘው በእስራኤል አገር ነው:: እግዚአብሔር ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ተስማሚ ሁኔታዎችን ሲያዘጋጅ ብዙ መቶ ዓመታት አልፈዋል:: በቤተልሄም የተወለደውና በተናቀችው ገሊላ ያደገው ኢየሱስ የተወሰኑ ሰዎችን አሰባስቦ ለሦስት ዓመታት ያህል አስተምሯቸዋል:: መልካምን ተግባር እያከናወነ የኖረ ቢሆንም የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ በማለቱ በመስቀል ላይ እንዲሞት ተፈረደበት:: ይህም የኛ የሰው ልጆች ክፋት ውጤት ነበር:: ደቀመዛሙርቱ በዚህ ሁኔታ በጣም ተረብሸው ተበታተኑ:: በመሆኑም በአዲሱ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ከሞት በመነሣቱ ተደነቁ:: ከሃምሳ ቀን በኋላም መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ላይ በመውረዱ ወደ ቤተክርስቲያንነት ተቀየሩ::

በበዓለሃምሳ ዕለት በሰገነቱ ላይ የተሰባሰቡት ደቀመዛሙርት 120 ብቻ ነበሩ:: ነገር ግን በዓለሃምሳው እንዳለፈ ብዙም ሳይቆይ ቁጥራቸው ወደ 5000 ማደጉን የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይተርካል:: በፍልስጥኤም አገር ውስጥ በፍጥነት ይጨምር የነበረው የደቀመዛሙርት ቁጥር ወደ ሮም ግዛትና ወደ ሌሎም ሩቅ አገሮች ሊስፋፋ ቻለ::

## ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ስንል ምን ማለታችን ነው?

ከበዓለሃምሳ ዕለት ጀምሮ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የመጨረሻው እስከሞተበት ጊዜ ድረስ የነበረችው ቤተክርስቲያን የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ትባላለች:: ቶማስ ወንጌልን ወደ ሕንድ ሄዶ እንደሰበከ እናምናለን:: ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም እንዲሁ ወንጌልን ወደ ኢትዮጵያ ወስዷል:: ሌሎች ደቀመዛሙርትም በባቢሎን፣ በሰሜን አፍሪካ፣ በአውሮፓና በቻይና ወንጌሉን ሰብከዋል:: ለዚህ የወንጌል መስፋፋት አስተዋጽኦ ካበረከቱት ነገሮች መካከል በአይሁድ መሪዎች የተቀሰቀሰው ስደት አንዱ ነበር:: የአይሁድ መሪዎቹ የያዕቆብን አንገት ሲቀሉ፣ ጴጥሮስን አስረውታል:: ከዋነኛ አሳዳጆች አንዱ የነበረው ጳውሎስ ተለውጦ ጠንካራ ክርስቲያን መሪና የአሕዛብ ሚሲዮናዊ ሊሆን በቅቷል::

## ቤተክርስቲያን እንዴት አደገች?

ቤተክርስቲያን እየተስፋፋች ስትሄድ በተለያዩ ስፍራዎች የተለያዩ መልኮች ነበሯት። ኢየሩሳሌም፣ ሮም፣ ኤፌሶንና ግብጽ ጠቃሚ የቤተክርስያን ማዕከላት ሆኑ። አንዳንድ ጊዜ በነዚህ ቡድኖች መካከል ያለመስማማት ይታይ ነበር። አሁንም በቤተክርስቲያን ላይ ስደት ተነሣ። ይህም የሆነው ከሮማው ቄሣር ነበር። በ250 ዓ.ም. ክርስቲያኖችን በመጨፍጨፍ፣ በማሠቃየትና በባርነት በመግዛት ክርስትናን ለማጥፋት ጣሩ። ነገር ግን ከፍተኛ ስደት በተነሣባቸው በነዚያው ስፍራዎች የነበረችው ቤተክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ እያደገች ትሄድ ጀመር። ሮማውያን የሰማዕታት ደም አዳዲስ ክርስቲያኖችን እንደሚያፈራ ለማጤን ቻሉ። ንጉሥ ቆንስጣንጥኖስ ክርስቲያን በሆነ ጊዜ ለክርስትና ሃይማኖት ሕጋዊ እውቅና ሰጠ። በ392 ዓ.ም. ደግሞ ክርስትና የሮም መንግሥታዊ ሃይማኖት መሆኑ ታወጀ። ይህም ከፍተኛ ትምህርታዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞችን አስገኝቷል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ይልቅ በመንግሥት ላይ ጥገኛ የመሆንንም ችግር አስከትሏል።

## የተለያዩ አብያተክርስቲያናት እንዴት ተፈጠሩ?

በአምስተኛውና ስድስተኛው ክፍለዘመን መካከል አያሌ የተለያዩ አብያተክርስቲያናት ተፈጥረዋል። እነዚህ አብያተክርስቲያናት ከተለያዩ አካባቢዎች ጋር የሚዛመዱ ናቸው። መሪያችን ቶማስ ነው የሚሉት የሶርያ ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት ከባቢሎን እስከ ሕንድ ድረስ ያለውን ስፍራ ያካልላሉ። የሰሜን አፍሪካው አካባቢ ደግሞ በኮፕቲክ ቤተክርስቲያን የተያዘ ነበር። የኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ቅርንጫፍ የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደግሞ ከሁሉም ተነጥላ በኢትዮጵያ ተራራማ ስፍራዎች ትኖራለች። የካቶሊክ ቤተክርስቲያን በሮም ግዛት ውስጥ የተስፋፋ ሲሆን፣ እንደ ፖለቲካዊ አገዛዙ ሁሉ በምሥራቅና በምዕራብ ተከፋፍሎ ነበር።

ምሥራቃውያን ካቶሊኮች ራሳቸውን ኦርቶዶክሶች እያሉ የሚጠሩ ሲሆን፣ በምሥራቅ፣ በትሩ፣ በግሪክና በሩሲያ ቅርንጫፎች ይከፋፈላሉ። ምዕራባውያን ካቶሊኮች በሮም ሥር ካለችው ቤተክርስቲያን ሥር ሆነው እጅግ እየተስፋፉ መጡ። ስያሜያቸውም የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የሚል ሆነ። መሪያቸው ሆኖ የሚሠራው ጳጳስ በአውሮፓ ከፍተኛ ሀይል ያለው የፖለቲካ ሰው ሊሆን በቃ።

የእስልምና ሃይማኖት ብቅ ያለው በዚህ ጊዜ ነበር። ለኃይማኖታቸው ወደኋ የማይሉ ጨካኝ የእስልምና ወታደሮች አካባቢው የሙስሊሞች እንደሆነ በማወጅ በመካከለኛው ምሥራቅና በሰሜን አፍሪካ ላይ ዘመቱ። በዚህ ጊዜ የሰሜን አፍሪካና የባቢሎን አብያተክርስቲያናት ሊወድሙ ተቃርበው ነበር። ችግሩ ሁሉም ዜጎች የክርስትና ሃይማኖትን እንዲከተሉ

እየተፈለገ፣ የክርስቶስ ተከታዮች ለመሆን የመረጡት ግን እጅግ ጥቂቶች ብቻ መሆናቸው ነበር::

## ቤተክርስቲያን ሁልጊዜም ለእግዚአብሔር እውነተኛ ሆና ትኖራለች?

በመካከለኛው ዘመን (1000-1400 ዓ.ም.)፣ ቤተክርስቲያን በአውሮፓ የሕዝቡን ባህል፣ ትምህርት፣ ፖለቲካና ሥራ ተቆጣጥራ ነበር:: አውሮፓ ራሷ ከፍተኛ ሀይል እያገኘች የሄደች ስትሆን፣ የዚህም ሀይል ማዕከል ጳጳሱ ነበር:: ይህም የቤተክርስቲያኒቱን መንፈሳዊ ሙቀት አቀዘቀዘው:: ከጳጳሱ ጀምሮ እስከ ተራው ካህን ድረስ ሁሉም በሙስና ውስጥ ተዘፈቁ:: ካህናት ለራሳቸው ወይም ለቤተክርስቲያናቸው ገቢ ለማስገኘት ሲሉ የሐጢአትን ይቅርታ በገንዘብ ይሸጡ ጀመር:: ጳጳሱ ገና ወደፊት ለሚፈጸሙ ሐጢአቶች ይቅርታን (indulgence) በመሸጥ በሮም አዲስ የቤተክርስቲያን ሕንጻ በማሠራት ላይ ነበር:: ይህም እግዚአብሔርን ለሥራ አነሣሣው::

## የፕሮቴስታንቶች መምጣት

በሮም ቤተክርስቲያን ውስጥ በሚታየው በዚህ ችግር ብዙ ሰዎች ተረብሸው ነበር:: ይህን ሁሉ በደል የሚፈጽመው ጳጳስ እንከንየለሽ ነው እየተባለ እሱን የሚቃወሙ ሰዎች በጭካኔ ይደመሰሱ ነበር:: ይህንኑ ውጤታማ ተቃውሞ ይዘው ከተነሡት ሰዎች መካከል የጀርመን ተወላጅ የሆነው ማርቲን ሉተር አንዱ ነበር:: ሉተር የይቅርታን መሸጥ በይፋ የተቃወመ ካህን ነበር:: በዚህ ተግባሩም የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ችሎት ላይ ካቀረበችው በኋላ አውግዛዋለች:: ይሁንና፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትንና ተራ ዜጎችን ጨምሮ ብዙ የጀርመን ክርስቲያኖች ለሉተር ድጋፋቸውን ሰጡ:: ይህም የፕሮቴስታንት ተሃድሶ እንዲወለድ አደረገ:: የሉተር አቋም የክርስትና አስተምህሮና ልምምድ መመዘኛው መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ ጳጳሱ ሊሆን እንደማይገባ የሚያረጋግጥ መርህ መሠረተ:: ጽድቅ የሚገኘው በእምነት ብቻ እንጂ ከካህኑ በሚሸመት ይቅርታ ሊሆን እንደማይችልም አስታወቀ:: ሰዎች ሁሉ ያነቡት ዘንድ ሉተር መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ ተረጎመ::

## የተለያዩ የፕሮቴስታንት አብያተክርስቲያናት እንዴት ተመሠረቱ?

ሉተር በሕይወት በነበረበት ጊዜ ሌሎች ብዙ የፕሮቴስታንት መሪዎች ተነሥተው ነበር:: እነዚህ መሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ቀዳሚው ባለሥልጣን እንደሆነ በማመናቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተረጎመ:: በዚህም ጊዜ በተለያዩ ሰዎች የሚመሩና

በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሠረቱ ብዙ ቤተእምነቶች ተመሠረቱ።

**የሉተራውያን ቤተክርስቲያን** ሉተርን በመከተል በጀርመንና በእስካንድንቪያ እየተጠናከረች መጣች።
**የክርስትና ሃይማኖት ድንጋጌዎች** (The Institutes of the Christian Churches) በሚል ርእስ ጆን ካልቪን የጻፈው መጽሐፍ ለፕሮቴስታንት መነቃቃት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የካልቪን ሥነመለኮታዊ አቋም እንደ ዳች ሪፎርምድ እና ፕረስቢተሪያን ቤተክርስቲያን ለመሳሰሉት የተሃድሶ አብያተክርስቲያናት መገኘት ጠቃሚ ሚና ተጫውቷል።
**የመጥምቃውያን አብያተክርስቲያናት** ለክርስቲያኖች ጥምቀት ጠቃሚ በመሆኑ ላይ ያተኩራሉ። ብዙዎቹ ካልቪናውያን (Reformed) የተሃድሶውን ጎዳና ቢከተሉም፣ መጥምቃውያን የተለያዩ ሥነመለኮታዊ አመለካከቶችን በትዕግሥት አስተናግደዋል።
**የእንግሊዝ** የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሪዎች ሉተርን በጥብቅ ተቃውመውት ነበር። የእንግሊዝ ንጉሥ ሉተርን በመቃወሙ የእንግሊዝ ጳጳስ «የእምነት ጠባቂ/መካች» የሚል ማዕረግ ሰጥተውታል። በኋላ ግን በንጉሡና በጳጳሱ መካከል የተከሰተው አለመግባባት የእንግሊዝ ቤተክርስቲያን ከሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እንድትነጠል አድርጓል። የእንግሊዟ ቤተክርስቲያን ራሷን አንግሊካን ብላ በመጥራት ወደ ፕሮቴስታንት ሥነመለኮት እየተቃረበች ትሄድ ጀመር።
**የቅድስና ሕይወት አራማጆች፡** አንዳንድ የፕሮቴስታንት አብያተክርስቲያናት እውነተኝነትና ታማኝነት በመጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት የተሰጠባቸው ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው የሚል አቋም አራማጆች ነበሩ። በዚህም ምክንያት ሥርዓቶችና ተምሳሌቶች አርባናቢስ መሆናቸውን ገለጹ። በግላዊ እውነተኝነትና ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ላይ አጽንኦት አደረጉ። እነዚህ ወገኖች የቅድስና አጥባቂዎች ተብለው ይጠሩ ነበር። የዚህ ቡድን አባላት ከነበሩት አካላት መካከል የእንግሊዞቹ ኩዌከሮችና የጀርመኖቹ ሞራቪያኖች ይጠቀሳሉ።

## ተሃድሶው በሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ ያሳደረው እንዴት ነበር?

በመጀመሪያ የሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የፕሮቴስታንት ተሃድሶን ለማስወገድ ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች። ጦርነቶችም ተካሂደዋል። ጭካኔ በተሞላበት ምርመራ እየታደኑ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ከኢጣሊያና ከስፔይን እንዲጠፉ ተደርጓል። በቅዱስ በርጠሎሜዊ ጭፍጨፋ ምክንያት የተሃድሶ ቤተክርስቲያን ከፈረንሳይ መካከለኛ የህብረተሰብ ክፍል

ውስጥ እንድትጠፋ ተደርጓል:: ከዚህ ሁሉ ባሻገር የፕሮቴስታንቶች ቁጥር እየጨመረ ሄደ:: የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተወሰኑ ክፍሎች የለውጥ ጥሪ በማቅረባቸው ምክንያት ብዙ በደሎችን ያስወገደ «የካቶሊኮች ተሃድሶ» ተካሄደ::

## የፕሮቴስታንት ሥነመለኮት እምብርት ምን ነበር?

የፕሮቴስታንት ተሃድሶ ለሥነመለኮት የታደሰ ፍላጎት አስከትሏል:: በዚህም ጊዜ አራት መሠረታዊ ነገሮች ተመሥርተዋል::

1. ጳጳሱ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ የአስተምህሮና የልምምድ ባለሥልጣን እንዲሆን ተወስኗል::
2. ክርስቲያኖች ሁሉ ካህናት ስለሆኑ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ ይችላሉ::
3. የዳንነው በመልካም ሥራችን ወይም ለቤተክርስቲያን በምንከፍለው ገንዘብ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው::
4. የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች (ቅዱስ ቁርባንና ጥምቀት) ለደህንነት ዋስትና የሚሰጡ ምትሃታዊ ቀመሮች ሳይሆኑ፣ እግዚአብሔር በአማኙ ልብ ውስጥ የፈጸመውን ሥራ የሚያሳዩ ምልክቶችና ተምሳሌቶች ናቸው::

## ጄምስ አርሚኒስ

የዳች ተሃድሶ ምሁር የሆነው አርሚኒስ ከካልቪን የቅድመውሳኔ ጽንሰአሳብ ውስጥ ስህተትን ተመለከተ:: ካልቪን እግዚአብሔር ማን እንደሚድንና ማን ወደ ሲዖል እንደሚገባ አስቀድሞ ወስኗል ሲል አስተምሮ ነበር:: አርሚኒስ ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር እንደማይስማማ ተገነዘበ:: ስለሆነም፣ አርሚኒስ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ለሰው ልጅ የመምረጥ ሀይል እንደሰጠ አስተማረ::

## ጆን ዌስሊ

ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት የማድረግ ፍላጎት የነበረውና የአንግሊካን ካህን የሆነው ጆን ዌስሊ በአርሚኒስና በሞራቪያንስ ትምህርት ተማረከ:: ዌስሊ መንፈሳዊ ለውጥን በማግኘቱ ታላቅ የሃይማኖት መሪ ሊሆን በቃ:: በእንግሊዝና በአሜሪካ የዌስሊ የመነቃቃት ትምህርት እየተስፋፋ ሲሄድ፣ ተከታዮቹ መተዲስቶች እየተባሉ ይጠሩ ጀመር:: ለዚህም ስያሜ መነሻ የሆነው የክርስትናን ልምምድና ጥናት በዘዴ ማካሄዳቸው ነበር:: (በእንግሊዝኛው የጥናትና የአኗኗር ዘዴያቸው Methodical ሲባል፣ ስማቸውም Methodists ሆነ ማለት ነው::) ዌስሊ የክርስቶስ ተከታዮች ፍጹማን መሆን እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥቶ ይሰብክ ነበር::

## የቅድስና አብያተክርስቲያናት እንዴት ተመሠረቱ?

በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለዘመን በአሜሪካና በብሪታኒያ ታላቅ የቅድስና መነቃቃት ተካሄደ:: እንደ ቤቨርሊ ካራዲን፣ ሳሙኤል ሎጋን ብረንግል፣ አሳ ማሆን፣ ፌቤን ፓልመር፣ ሴት ሪስ፣ ኤ.ቢ. ሲምፕሰን፣ ዳንኤል ስቲል፣ ሃና ስሚዝ፣ ኤ.ም. ሂልስ እና ሌሎችም ብዙ መሪዎች ከበርካታ ቤተእምነቶች ውስጥ ብቅ ብቅ አሉ::

ሁሉንም ቤተእምነቶች ያገለገሉ የቅድስና ድርጅቶችም ተመሠረቱ:: የካምፕ ስብሰባዎችም ይካሄዱ ጀመር:: የአንዳንድ አብያተክርስቲያናት መሪዎች እነዚህን «የቅድስና» ሰዎች ባለመፈለጋቸው ከቤተክርስቲያኖቻቸው አስወጧቸው:: በብዙ ስፍራዎች የቅድስና ጉባኤዎች ተከፈቱ:: እነዚህ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ማህበራትንና ቤተእምነቶችን መሠረቱ:: ብዙ አብያተክርስቲያናት ተሃዋዱ:: ከሁሉም ትልቁ የቅድስና ቤተእምነቶች ውህደት የተካሄደው በናዛሪን ቤተክርስቲያን ነበር::

## የጴንጠቆስጠና የቅድስና አብያተክርስቲያናት የሚዛመዱት እንዴት ነው?

በመጀመሪያ የጰንጠቆስጠና የቅድስና አብያተክርስቲያናት እንደ አንድ ቤተእምነት ይሠሩ ነበር:: ቀስ በቀስ እንደታየው፣ የጴንጠቆስጠ አብያተክርስቲያናት የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ተከትሎ በሚታየው አካላዊ ምልክት ላይ ሲያተኩሩ፣ የቅድስና አብያተክርስቲያናት የግለሰቦችን ሕይወት በሚለውጠው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ያተኩሩ ጀመር:: የናዛሪን ቤተክርስቲያን የዌስሊን ትውፊት የምትከተል የቅድስና ቤተክርስቲያን መሆኗን ለማሳየት ስትል በ1919 ከስሟ ላይ ጴንጠቆስጠ የሚለውን አስወገደች:: ይህም ልዩነት የተፈሰገው የጴንጠቆስጠ አብያተክርስቲያናት ከሥነመለኮታዊ ግንዛቤ ወይም ከሥነምግባራዊ አኗኗር ይልቅ ሐሴታዊ ልምምዶችን በሚገልጹ አካላዊ ምልክቶች ላይ በተደጋጋሚ ትኩረት በማድረጋቸው ምክንያት ነው::

# ምዕራፍ 9
# የናዛሪን ቤተክርስቲያን ታሪክ

## የናዛሪን ቤተክርስቲያን መሥራች

ለናዛሪን ቤተክርስቲያን መመሥረት ሃላፊነት የወሰደው አንድ ግለሰብ ነበር ልንል አንችልም። ለቤተእምነታችን መመሥረት በአሜሪካና በብሪታኒያ የሚገኙ ብዙ ታላላቅ መሪዎች አስተዋጽኦ አደርገዋል። ይህም ሆኖ፣ ዶ/ር ፊንሃስ ኤፍ. ብረሲ ካበረከቱት ታላቅ አስተዋጽኦ የተነሣ ብዙውን ጊዜ የናዛሪን ቤተክርስቲያን አባት እየተባሉ ይጠራሉ።

## ዶ/ር ብረሲ ማን ነበሩ?

ዶ/ር ብረሲ በአዮዋና በካሊፎርኒያ በመጋቢነት ያገለገሏቸውን አብያተክርስቲያናት ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ የሜተዲስት አገልጋይ ነበሩ። በአዮዋ የብረሲ ቤተክርስቲያን 678 አባላትን ስትጨምር፣ በካሊፎርኒያ 856 አዳዲስ አባላትን ወደ ሦስት የተለያዩ አብያተክርስቲያናት ከፋፍለዋል። ዶ/ር ብረሲ በትምህርት ላይ ትኩረት በመስጠት ትምህርት ቤቶችንና ዩኒቨርስቲዎችን ለመመሥረት የሚከናወኑትን እርምጃዎች አግዘዋል። የሳውዘርን ካሊፎርኒያ ዩኒቨርስቲ የቦርድ አባል ሆነውም አገልግለዋል። ከ37 ዓመታት አገልግሎቸው በኋላ፣ የቤተክርስቲያናቸው ጳጳስ ከሎስ አንጀለስና ከሀብታም የሜተዲስት ጉባኤ የትኛውን በመጋቢነት ለማገልገል እንደሚፈልጉ ምርጫቸውን እንዲያስታውቁ አስገደዷቸው። ዶ/ር ብረሲ ሜተዲስቶቹን ለማገልገል ባለመቻላቸው ከፍተኛ ሐዘን እየተሰማቸው በሎስ አንጀሎስ የሚገኘውን የሚሲዮን ጣቢያ ለማገልገል ተስማሙ። የቅርብ ወዳጃቸው የነበሩት ዶ/ር ጄ.ፒ. ዊድኔይም አብረዋቸው አገለገሉ። ለሚሲዮኑ «የናዛሪን ቤተክርስቲያን» የሚል ስያሜ ሰጡ። በቀጣይ ዓመታት ዶ/ር ብረሲ ጉባኤያቸውን በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች የቅድስና አብያተክርስቲያናት ጋር ለማዋሃድ ተግተው ሲሠሩ ቆዩ።

## በአሜሪካ የተካሄደው
## የመጀመሪያው የቅድስና ቤተክርስቲያን ውህደት

መጀመሪያ የተመሠረተችውና በኋላም የናዛሪን ቤተክርስቲያን አካል የሆነችው ቤተክርስቲያን በ1887 በሮድ ደሴት የተመሠረተችው ነበረች። ይህች በኤፍ.ኤ. ሂሌሪ የተመራችው ቤተክርስቲያንና ኒውዮርክ የነበረችው ቤተክርስቲያን ተዋህደው የአሜሪካ የጴንጠቆስጠ አብያተክርስቲያናት ማህበር በሚል ስያሜ ይጠሩ ጀመር። እነዚህ አብያተክርስቲያናት በ1907 48 ማህበረምእመናንና 2371 አባላት ነበሯቸው። ከመሪዎቻቸውም አንዱ

ንቁ ወጣት የነበረው ኤች.ኤፍ. ሬይኖልድስ ነበር። ይህ ሰው በኋላ በናዛሪን ቤተክርስቲያን ውስጥ ሚስተር ሚሽን ሊባል በቅቷል።
በ1985 በሎስ አንጀለስ በብረሲ «የክብር ጎተራ» ውስጥ የተጀመረው ጉባኤ አዳዲስ ማህበረምእመናንን እየመሠረተ በፍጥነት ያድግ ጀመር። እንደ ቡድ ሮቢንሰንና ሲ.ደብልዩ. ሩት የመሳሰሉ ወንጌላውያን አገልግሎቱን ያግዙ ጀመር። በ1898 እነዚህን እንቅስቃሴዎች ማስተባበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ብረሲ የመጀመሪያውን «የናዛሪን ቤተክርስቲያን መምሪያ» አዘጋጁ። በ1904 በቀጠናዎች ከተከፋፈሉ በኋላ ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ ጀመሩ። በ1907 ከፍተኛ ዕደገት በመታየቱ 3827 አባላትን ያቀፉ 45 ማህበረምእመናን ሊገኙ ቻሉ።
የሦስቱም ቤተእምነቶች መሪዎች መዋሃድ አስፈላጊ እንደሆነ አሰቡ። ይህም ውህደት በ1907 ሁለቱ ቡድኖች በሺካጎ ጠቅላላ ጉባኤ ባካሄዱበት ወቅት ተግባራዊ ሊሆን ችሏል። አዲሱ ማህበረምእመናን የናዛሪን ቤተክርስቲያን ተብሎ ሲጠራ፣ ከኮንግርጌሽናልና ከኤጵስቆጳል የቤተክርስቲያን አስተዳደር የተዘጋጀውን መዋቅር ተከትሏል።

## የቅድስና ቤተእምነቶች ሁለተኛ ውህደት

በሰሜንና ደቡብ የአሜሪካ መንግሥታት መካከል የተካሄው የርስበርስ ጦርነት በአሜሪካ ውስጥ የሚደረጉትን ግንኙነቶች በከፍተኛ ደረጃ ጎድቷቸው ነበር። ደቡቦቹ በተለይ ሰሜናዊ ያንኪዎችን ይጠሏቸው ነበር። በዚህ ጊዜ የቅድስና መልእክት በደቡብ ላይ ከፍተኛ ለውጥ አስከትሏል። በ1894 የአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በአር.ኤል. ሄሪስ አማካኝነት ተመሠረተች። በ1901 ጀርማኒን ነጻ የቅድስና ቤተክርስቲያን መሠረቱ። እነዚሁ ሁለቱ በ1905 ተዋህደው የክርስቶስ የቅድስና ቤተክርስቲያን በሚል ስያሜ ይጠሩ ጀመር። ይህች ቤተክርስቲያን በስተደቡብ በፍጥነት በመስፋፋት የሰሜን ምሥራቅንና የምዕራብን የቅድስና ተከታዮች አገኙ። ኦክቶበር 8/1908 የናዛሪን ቤተክርስቲያን ልዑካን ከክርስቶስ የቅድስና ቤተክርስቲያን ልዑካን ጋር በፓይለት ፖይንት ቴክሳስ ተገናኝተው በአንድ ቤተእምነት ሥር ስለመዋሃድ ተወያዩ። የሰሜንና የደቡብ ክፍሎች በመታረቃቸው ምክንያት በተከሰተው ታላቅ የደስታ ወቅት ልዑካኑ በአንድነት ተዋህደው የናዛሪን ጴንጠቆስጠ ቤተክርስቲያን በሚል መጠሪያ ለመጠራት ተስማሙ።
በዚህ ጊዜ የቤተእምነቱ ተከታዮች ቁጥር 10414 ነበረ። ከምዕራብ ፒ.ኤፍ. ብረሲ፣ ከምሥራቅ ኤች.ኤፍ. ሬይኖልድስና ከደቡብ ኢ.ቢ. ኢሊስን የመጀመሪያዎቹ የጠቅላይ ሃላፊዎች ቦርድ አባላት ሆኑ። ከጴንጠቆስጠ እንቅስቃሴ ጋር ላለመመሳሰል ሲባል በ1919 «ጴንጠቆስጠ» የሚለው ስም ከቤተእምነቱ እንዲወገድ ተደረገ።

## ሌሎች ውህደቶች

በቀጣይ ጥቂት ዓመታት አያሌ አብያተክርስቲያናትና ድርጅቶች ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር ተዋህደዋል። ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ነበሩ።

**የጴንጠቆስጠ ሚሲዮን** በ1915 ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር ተዋህዷል። የነዚህ ሚሲዮኖች ማህበረምእመናን በአሜሪካ ደቡባዊ ግዛቶች ውስጥ ተበታትነው ይገኙ ነበር።

**ጴንጠቆስጠ የእስኮትላንድ ቤተክርስቲያን** በጆርጅ ሻርፕ ተመርቶ በ1915 ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር ተቀላቀለ። ይህም ቤተእምነቱ በብሪታኒያ ሥር እንዲሰድ አድርጓል። ሚሲዮኖቻቸው የነበሩት ዴቪድና ካነማ ሃይንድ በማንዚኒ ስዋዚላንድ የናዛሪን ሆስፒታል መሥርተዋል።

**የምእመናን የቅድስና ማህበር** በ1922 ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር ተወሃደ።

ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የሚገኘውና በአሜሪካ የሚደገፈው **የሄፍዚባ የእምነት ሚሲዮናዊ ማህበር** ከናዛሪን ቤተክርስቲያን ጋር በ1950 ተዋሃደ።

በደቡብ አፍሪካ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደርግ የነበረው **የእንግሊዙ ዓለምአቀፍ የቅድስና ሚሲዮን** በ1952 ተቀላቀለ።

**የእንግሊዙ ጎልጎታ የቅድስና ቤተክርስቲያን** በ1955 ተዋሃደ።

**የካናዳ የወንጌል ሠራተኞች ማህበር** በ1958 ተዋሃደ።

የቤተእምነቱን **መምሪያ** ተከትሎ በአገሬው ተወላጆች የተመሠረተው የናይጄሪያው የናዛሪን ቤተክርስቲያን በ1988 ተዋሃደ።

እንዲህ ዓይነቶቹ ውህደቶች በዓለም ዙሪያ የሚገኙትን የቅድስና ተከታዮች በአንድነት የሚያስተሳስሩ በመሆናቸው፣ የናዛሪን ቤተክርስቲያን ተግባር ጠቃሚ ክፍሎች ሆነው አገልግለዋል። አሁንም በዚህ መልኩ ቀጥለዋል።

## የናዛሪን ቤተክርስቲያን ዕድገት

በመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት የናዛሪን ቤተክርስቲያን በዓመት በአማካይ የ13 በመቶ (ከ10 000 እስከ 100 000 አባላት) ዕድገት ታሳይ ነበር። ይህ ዕድገት ሊገኝ የቻለው በተወሰነ ደረጃ ከውህደት ሳቢያ ሲሆን፣ አብዛኛው ዕድገት የተገኘው ግን ከአብያተክርስቲያናቱ ጤናማ መስፋፋት ነበር። በሚከተሉት አሠርተዓመታት ውስጥ የነበረው ዕድገት ጤናማ ቢሆንም፣ ዘገምተኛ ነበር። በ1958 የቤተክርስቲያኒቱ አባላት ቁጥር 350 000 ከደረሰ በኋላ፣ በ1996 ወደ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አካባቢ ሆኖ ነበር። ምንም እንኳዋን በአሁኑ ጊዜ በሌሎች የዓለም ክፍሎች የአባላቱ ቁጥር እያደገ ቢሆንም፣ ግማሽ ያህሉቹ የናዛሪን ቤተክርስቲያን አባላት የሚገኙት

አሜሪካ ውስጥ ነው:: በአሁኑ ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ 150 000 የናዛሪን ቤተክርስቲያን አባላት ሲኖሩ፣ ይህ ቁጥር በዓመት በ14 በመቶ እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል::

## የናዛሪን ቤተክርስቲያን አስተዳደር

እግዚአብሔር ለቀድሞዎቹ የናዛሪን ቤተክርስቲያን መሪዎች ከዲሞክራሲያዊና አምባገነናዊ የአስተዳደር መርሆች የተውጣጣ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲመሠርቱ መርቷቸዋል:: ይህም የናዛሪን ቤተክርስቲያን አስተዳደር በፕረስቢቴሪያን፣ ሜተዲስት፣ ኮንግሪጌሽናል፣ አንግሊካንና በሌሎችም ራሳቸውን ችለው በሚንቀሳቀሱ አብያተክርስቲያናት መሪዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው አድርጓል:: እያንዳንዱ አጥቢያ ማህበረምእመናን የራሱን መጋቢ የመምረጥ መብት ሲኖረው፣ ሊመረጡ የሚችሉት መሪዎች ከቀጠናው የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸው መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም፣ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ምርጫ በቀጠና ሃላፊዎች መጽደቅ አለበት:: መጋቢያን ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ምእመናን ወደ እግዚአብሔር ሊቀርቡ ይችላሉ ብለን ስለምናምን፣ የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ አካላት ከምእመናንና ከአገልጋዮች የተውጣጡ ናቸው::

## ቤተክርስቲያናችን ድሆችን ታገለግላለች

አያሌ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት በድሆች አካባቢ ነው የተመሠረቱት:: የቅድስና መልእክት ሰዎችን በድህነት የሚያስሩትን ብዙ ክፋቶች ያስወግዳል:: በዚህ ምክንያት አብያተክርስቲያኖቻችን ብዙውን ጊዜ ድሆች ሆነው መቀጠላቸው ያበቃል:: ቤተክርስቲያናችን ችግሮች ባሉባቸው አካባቢዎች አጥቢያ አብያተክርስቲያናትን ለመመሥረት ልዩ ጥረቶችን ታደርጋለች:: በአሁኑ ጊዜ በመንፈሳዊ ሁኔታቸው ቸል በተባሉት የዓለም ክፍሎች የሚሲዮን ሥራዎቻችንን ለማስፋፋት ከፍተኛ ተግባራትን በማከናወን ላይ እንገኛለን::

## የናዛሪን ቤተክርስቲያን ለትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ትሰጣለች

በናዛሪን ቤተክርስቲያን ሁልጊዜም ለወጣቶች ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሲሰጥ ቆይቷል:: መጽሐፍ ቅዱስ ወጣቶቻችንን በእግዚብሔራዊ መንገድ እንድናስተምራቸው ይመክረናል:: እኛም ለዚህ ምክር ትልቅ ስፍራ እንሰጣለን:: በ1908 በአሜሪካ በዲግሪ ደረጃ የሚያስተምሩ አምስት ኮሌጆች ተከፍተው ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያናችን በዓለም ዙሪያ 52 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ታንቀሳቅሳለች:: በአፍሪካ ብቻ አንድ ዩኒቨርስቲ፣ አራት በዲግሪ ደረጃ የሚያስተምሩ ኮሌጆች፣ ሠላሳ ሁለት የተከታታይ

ትምህርት ማዕከላት፣ የቴክኒክ ትምህርት ቤቶች፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተከፍተዋል።

## ናዛሪኖች በክርስቲያናዊ ሥነጽሑፍ ላይ ትኩረት ይሰጣሉ

ቤተክርስቲያናችን የቅድስና ሥነጽሑፎች እንዲሰራጩ ከፍተኛ ጥረት ታደርጋለች። በ1908፣ ስምንት የተለያዩ ህትመቶች ይዘጋጁ ነበር። እነዚህ ህትመቶች በአንድ ላይ ተዋህደው «የቅድስና ብሥራት» በሚል መጠሪያ ይወጡ ጀመር። ይህ መጽሔት ለቤተክርስቲያን ዜናዎች እንደ ዋንኛ መሣሪያ ሆኖ አገልግሏል። ከዚያም ማተሚያ ቤት በመቋቋሙ የሰንበት ትምህርት፣ የሚሲዮን፣ የሥነመለኮትና የጽሞና መልእክቶች ሊታተሙ ችለዋል። ዛሬ ለመዝሙር «ሊለናስ»፣ ለጠቅላላ ሥራዎች ደግሞ «ቤከን ሂል» በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የናዛሪን አሳታሚ ድርጅት ከቤተክርስቲያን ዋና ዋና አሳታሚ ድርጅቶች አንዱ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል። የአፍሪካ የናዛሪን አሳታሚ ድርጅት የሰንበት ትምህርት፣ የወጣቶችና የሚሲዮን፣ የተለያዩ ሃይማኖታዊ መጻሕፍትና ትራንስ አፍሪካ የተባለ አካባቢያዊ ጽሑፍ ያሳትማል።

## ናዛሪኖች ለሚሲዮን ትኩረት ይሰጣሉ

ቅድስናና ሚሲዮን ጎን ለጎን የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። በ1910 በሰባት የዓለም አካባቢዎች፣ ማለትም በአፍሪካ፣ ሕንድ፣ ጃፓን፣ ሜክሲኮ፣ ጓቲማላ፣ ኬፕ ቨርደና ኩባ የናዛሪን ሚሲዮናውያን ነበሩ። በፍጥነት እያደገ በመሄድ ላይ የነበረውን የሚሲዮን እንቅስቃሴ ለማገዝ ጠቅላላ ቦርድ ተቋቋመ። በ1996 ቤተክርስቲያኒቱ ወደ 110 አገሮች ስትስፋፋ 150 ቀጠናዎች ሊከፈቱ ችለዋል። 17 000 አገልጋዮችም ተሰማርተዋል። ከነዚህም መካከል አንደኛው አስደሳች ተግባር ቀደም ሲል የኮሚኒዝም ርዕዮተዓለም በተስፋፋባቸው የአውሮፓና የእስያ አገሮች የተካሄደው የሚሲዮን ሥራ ነበር።

## ዓበይት የናዛሪን መሪዎች

ከታላላቅ መሪዎቻችን መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

ፊንሃስ ኤፍ. ብረሲ የእግዚአብሔር ክብር በሕዝቡ መካከል እንዲያድር ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ብርቱ መሪ ነበሩ። ጄምስ ቢ. ቻፕማን የጠቅላይ ሃላፊዎች ተግባር ምሳሌ ለመሆን በቅተዋል። ሱዛን ቢ. ፊትኪን ለዓለም ወንጌልን በማድረሱ፣ የሚሲዮን ጣቢያዎችን በማቋቋሙና ሆስፒታሎችን በመመሥረቱ ረገድ የሴቶችን አስተዋጽኦ አነሣሥተዋል። ለናዛሪን አሳታሚ ድርጅት መመሥረት ከኤም. ሉን የተበረከተው እገዛ እጅግ ከፍተኛ ነበር። ከመጀመሪያዎቹ ጄኔራሎች በዕድሜ ወጣት የሆኑት ሂራም ኤፍ. ሬይኖልድ ለ25 ዓመታት የሚሲዮን ሥራችን ዳይሬክተር

ሆነው አገልግለዋል፡፡ ብዙዎች አንክል ቡድ የሚሏቸው ቡድ ሮቢንሰን የትምህርትና የንግግር ብቃታቸው አነስተኛ የነበረ ቢሆንም መሰናክሎችን ተቋቁመው ውብ የወንጌላዊነት ሚና ተጫውተዋል፡፡ ስቲፈን ኤስ. ዋይት የቅድስና ብሥራት ለናዛሪን አማኞች ታላቅ ጠቀሜታ ያለው ጋዜጣ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ የትምህርት፣ የአስተዳደርና የሥነመለኮት ምሁር የሆኑት ኤች. ኦርተን ዊሊ ለቤተክርስቲያኒቱ የሥነመለኮት መሠረት ጥለዋል፡፡

ስለ አፍሪካ የሚስዮን መሪዎችስ ምን ልንል እንችላለን? ሄርመን ኢስ. ሽመልዘንበች በአፍሪካ ክፍለዓለም የቤተክርስቲያንን ሥራ መሥርተዋል፡፡ ከ1914 እስከ 1967 አብዛኛውን ጊዜ የበላይ ሃላፊ ሆነው የሠሩት ዊሊያም ሲ. ኢሰልስቲን፣ በሞዛምቢክ የቤተክርስቲያኒቱን ሥራ የጀመሩት ቻርልስ ጀንኪንስ፣ በስዋዚላንድ ሆስፒታል የከፈቱትና ሌሎንም ብዙ ተግባራት ያካሄዱት ዴቪድ ሃይንድ፣ ማሺክ፣ ላታ፣ ፔን፣ ዴይሆፍ፣ ጆነስ፣ ሸርሊ....

ይህም ሆኖ፣ ሁልጊዜም ቁልፉ ብሄራዊ አመራር ነበር፡፡ ለዚህም የሚከተሉት መሪዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በአስቸጋሪው ኬፕ ቨርደ ፊር የመቅደድ ሥራ የሠሩት ጃኦ ዲያስ፣ የሄርመን ሽመልዘንባች ቀኝ እጅ የነበሩት ጆሴፍ ምክዋናዚ፣ መጋቢና ቆራጥ መሪ የነበሩት ሳሙኤል ድላሚኒ፣ በደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው የቀጠና ሃላፊ የነበሩት ታይተስ ድላሚኒ፣ በሞዛምቢክ የፈርቀዳጅነትን ሚና የተጫወቱት ሳሙኤል ሙላት፣ ዳንኤል ሙከቲና ቲሞቲ ሙካቬል፣ የብርቱ ሰባኪና ታላቅ ሰባኪ የጁልየት ድዚማንዝን አባት የነበሩት ሰሎሞን ድዚማንዝን፡፡ የህትመት አገልግሎት ቁልፍ የነበሩት ሪቻርድ ማማያንና ራልፍ ኩነነ፣ ከጠንቋይ አባት የተወለዱትና ከሞዛምቢክ ለስዋዚላንድ ህዝብ በወንጌላዊነት ያገለገሉት ጆን ማዚቪላ፣ በደቡብ አፍሪካ ነጮች መካከል ከዶ/ር ቻርልስ ስተሪክላንድ ጋር አብረው በቀዳሚነት የስብከት አገልግሎት ያበረከቱት ጆስያስ ማክሎውሊን፡፡

ዝርዝሩን የት ጋ ልንጨርስ እንችላለን? እነዚህ ሁሉ ሽልማቶቻቸውን ለመቀበል ወደ ጌታ ሄደዋል፡፡ አሁን ደግሞ በክፍለዓለሙ ሁሉ ስለሚያገለግሉት እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡፡

ምዕራፍ 10

# የአፍሪካ ክልል

## የአፍሪካ ክልል የትኛውን ክፍል ያካትታል?

የአፍሪካ ክልል በሜድትራኒያን ባህር ዳርቻ ከሚገኙት አገሮች ውጭ የሚገኙትን የአፍሪካ አገሮችና ደሴቶች ያካትታል:: ከስድስት ጠቅላላ የበላይ ሃላፊዎች አንዱ በዚህ ክልል ውስጥ በየሁለት ዓመቱ በዝውውር ይሠራል:: ክልላዊ ዳይሬክተር ለጠቅላላው ቦርድ ተጠሪነት ሲኖረው፣ ጠቅላላ የበላይ ሃላፊዎች የናዛሪን ቤተክርስቲያን አስተዳደር በክልሉ ለሚካሄደው ተግባር ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል:: የመስክ ዳይሬክተሮችን፣ የትምህርት ዳይሬክተሩንና ተመራጭ ተወካዮችን የሚያቅፈው ክልላዊ የአማካሪዎች ኮሚቴ ለክልላዊ ዳይሬክተር ምሪትን ይሰጣል::

## ክልላዊ ቢሮዎች የሚገኙት የት ነው?

የክልሉ ቢሮዎች የሚገኙት በደቡብ አፍሪካ ጉተንግ፣ ሩድፑርት፣ ኦንትደክርስ ጎዳና ላይ ነው:: አድራሻውም ፖ.ሳ.ቁ. 44፣ ፍሎሪዳ፣ 1710፣ ደቡብ አፍሪካ ነው:: ስልክ: ደቡብ አፍሪካ (27)፣ ክልል (11)፣ 472-3615::

## ክልሉ የሚተዳደረው እንዴት ነው?

ክልሉ በስድስት መስኮች የተከፈለ ነው:: እነዚህም፣ ምዕራብ አፍሪካ፣ ምሥራቅ አፍሪካ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ማዕከላዊ አፍሪካ፣ ደቡብ ምሥራቅ አፍሪካና ደቡብ አፍሪካ ናቸው:: የነዚህ መስኮች ቢሮዎች የሚገኙት እንደ ቅደምተከተላቸው በአቢጃን፣ ናይሮቢ፣ አዲስ አበባ፣ ሃራሬ፣ ማንዚኒና ፍሎሪዳ ነው:: እያንዳንዱ መስክ ዳይሬክተር ያለው ሲሆን፣ ዳይሬክተሩም ለክልላዊ ዳይሬክተር ተጠሪ ነው::

## የቀጠና አደረጃጀት

በያንዳንዱ መስክ ውስጥ የሚገኙ አብያተክርስቲያናት በቀጠናዎች ይዋቀራሉ:: መጀመሪያ ሥራው በተጀመረበት አካባቢ ከተጀመረ በኋላ ለቀጠና መዋቅር የሚካሄዱ ሦስት ደረጃዎች አሉ:: ሥራው የተጀመረበት አካባቢ በሠራተኞች ቡድን የሚከፈተው አዲስ አካባቢ ነው::

### ብሄራዊ የሚሲዮን ቀጠና

ፈርቀዳጁ ቡድን ለስልታዊ ዕድገትና የወንጌል ስርጭት (የመተዳደሪያ ደንብ 200.2) የተሰጡትን መምሪያዎች ማሟላት እንደቻለ ወዲያውኑ ይመሠረታል:: የቀጠና የበላይ ሃላፊ የሚሾመው በአጠቃላይ የበላይ ሃላፊ ሕጋዊ ሥልጣን ነው::

የሚሲዮን ቀጠና ደረጃ የሚገኘው ቀጠናው 10 የተደራጁ አብያተክርስቲያናት፣ 500 ሙሉ አባላትና 5 የተሾሙ ሽማግሌዎች

ያሉት፣ እንዲሁም ለቀጠናው አስተዳደር ወጪ ሃምሳ በመቶ ገንዘብ ማዋጣት ሲችል ነው። በሥልጣን ላይ ያለው አጠቃላይ የበላይ ሃላፊ ከዚህ ደንብ ውጭ የተለየ መመዘኛ ሊያወጣ ይችላል። የቀጠና የበላይ ሃላፊ በምርጫ ወይም በሹመት ይሰየማል።

መደበኛ ቀጠና ሊመሠረት የሚችለው ቀጠናው 1,000 አባላት ሲኖሩትና ለአስተዳደራዊና የቤተክርስቲያን ማስፋፊያ ሥራዎች ሙሉ እንክብካቤ ማድረግ ሲችል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ቀጠና ከሌሎች ዓለምአቀፍ ቀጠናዎች ጎን ለጎን ይሠራል።

## የአፍሪካ ቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ምን ምንድናቸው?

የእያንዳንዱ መስክ የመጀመሪያው ሃላፊነት አብያተክርስቲያናትን መመሥረትና ለወንጌሉ መስፋፋት እነዚህኑ አብያተክርስቲያናት በቀጠና ማደራጀት ነው። ቀጠናዎች እያደጉ ሲሄዱ በአካባቢያቸው ወንጌልን ለማስፋፋት ተጨማሪ ሃላፊነቶችን ይወስዳሉ። ጠቅላላይቱ ቤተክርስቲያን ለቤተክርስቲያን አስተዳደር ትምህርትን ለመስጠት የመዋቅር ድጋፍ መስጠቷን ትቀጥላለች።

ከሕዝቡ ፍላጎትና የቤተክርስቲያኒቱ ዓቅም ጋር በማጣጣም መልኩ/የህዝቡ ችግር ታይቶና የቤተክርስቲያን አቅም በፈቀደ መጠን/ የርህርሄ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ የእርሻ ፕሮጀክቶች፣ የረሃብና የአደጋ እርዳታና ነፃ የትምህርት እድሎች ከአገልግሎቶቻችን መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

## የትምህርት ተቋሞቻችን

ናዛሪኖች ለአገልጋዮች፣ ለቤተክርስቲያን መሪዎችና ለምእመናን ትምህርት በመስጠቱ ላይ ያተኩራሉ። ከ1996 ጀምሮ በኬንያ አንድ ዩኒቨርስቲ፣ በደቡብ አፍሪካና በስዋዚላንድ አራት በድግሪ ደረጃ የሚያስተምሩ ተቋማት፣ በማላዊ፣ ሞዛምቢክ፣ ኬፕ ቨርደ፣ ኮት ዲቯር፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳና ዛየር የሥነመለኮት ትምህርት ቤቶች፣ እንዲሁም ከስሃራ በታች ባሉት የአፍሪካ አገሮች የተጠናከረ የተከታታይ ትምህርት መርሃግብሮች ተዘርግተዋል። የተከታታይ ትምህርት መርሃግብር ከአካባቢያዊ ድርጅቶች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የሚካሄድ ሲሆን፣ ሁሉም የምስክር ወረቀቶችና ዲፕሎማዎች የሚሰጡት በማዕከላዊ ተቋም ነው።

እያንዳንዱ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አለው። ይህም

የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚመረጠው በሚያገለግላቸው ቀጠናዎች ነው። ከ3000 የሚበልጡ ተማሪዎች በተለያዩ ፕሮግራሞች ተመዝግበው እየተማሩ ይገኛሉ።

የትምህርት አገልግሎት ዳይሬክተር በሁሉም መስክ ተቋሞቹን ያግዛል። ይህም ማስተባበርን፣ ዕድገትን፣ የገንዘብና የውጭ ዜጋ ሠራተኞችን ጉዳይ የሚያካትት ነው። ከዋና ዋና ፕሮጀክቶች አንዱ ነፃ የትምህርት እድል

አገልግሎት ሲሆን፣ ይህም በተቋሞቻችን ሁሉ ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚውል ነው::

## የናዛሬን ሥራ በአፍሪካ እንዴት ተጀመረ?

### ኬፕ ቨርዴ

በአፍሪካ የመጀመሪያው የናዛሬን ሥራ የተጀመረው በ1901 በኬፕ ቨርዴ ደሴት ነበር:: ጆን ዲያዝ አሜሪካ በመርከብ ለሥራ በሄዱ ጊዜ በቅድስና ቤተክርስቲያን ውስጥ ደህንነትን አግኝተው ተቀደሱ:: ወደ አገራቸው በተመለሱ ጊዜም ሙሉ በሙሉ የሮም ካቶሊኮች በተቆጣጠሩት አካባቢ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን የመመሥረቱን ከባድ ሃላፊነት ይወጡ ጀመር:: ይህም ሆኖ፣ ሥራቸው ፍሬያማ ሆኖ በመገኘቱ ዛሬ በዚያች ደሴት የናዛሬን ቤተክርስቲያን ዋናዋ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ልትሆን በቅታለች::

## የናዛሬን ቤተክርስቲያን በስዋዚላንድ ተመሠረተች

ሄርመንና ሉሉ ሽመልዘንባችና ኤታ ኢኒስ በ1908 ወደ አፍሪካ መጡ:: ቤተክርስቲያናቸው ከናዛሬን ቤተክርስቲያን ጋር በተዋሃደች ጊዜ በአፍሪካ ውስጥ የሚካሄደውን ሥራ እንዲቀላቀሉ ተጠየቁ:: በዚህም ጊዜ በስዋዚላንድ ኤንድዚንጅን ለመጀመር ፈለጉ:: ይህም ጅማሬ የናዛሬን ቤተክርስቲያን ከአሥራ አምስት ወደሚበልጡ የአፍሪካ አገሮች እንድትስፋፋ አደረገ:: የሥራው ጅማሬ አነስተኛ ቢሆንም፣ በትጋት የሚንቀሳቀሰው ሚሲዮናዊ ቡድን ፒግስ ፒክ፣ ማንዚኒና ሲተኪ ደረሰ:: ሽመልዘንባች በወባ በተበከለችው ሎውቨልድ ቤተክርስቲያን በመመሥረቱ ተግባር ላይ እንዳሉ በ1928 ዐረፉ:: በዚያን ጊዜ የናዛሬን ቤተክርስቲያን ከስዋዚላንድ ዳርቻዎች አልፋ ወደ ሞዛምቢክና የደቡብ አፍሪካ ሪፓብሊክ ተዳርሳ ነበር::

ሕክምና: ዶ/ር ዴቪድ ሃንድ ከሠራተኞቹ ጋር በመቀላቀል በ1925 በማንዚኒ ሆስፒታል ከፈቱ:: ይህ ተቋም አሁን አቢይ የስዋዚ የህክምና ድርጅት ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል::

የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ: በፒግስ ፒክ ተጀምሮ እየተስፋፋ በመሄድ እያደገ የሚሄደውን ሥራ ሊረዳ ወደሚችልበት የሲተኪ እርሻ ተዛወረ:: ለወንጌሉ መስፋፋት ከፍተኛ እገዛ ያደረጉ ታላላቅ የአፍሪካ መሪዎች የወጡት ከዚህ ኮሌጅ ነበር::

ትምህርት ቤቶች በአመቺ ስፍራዎች ሁሉ ተከፈቱ:: በስዋዚላንድ፣ ሞዛምቢክና ደቡብ አፍሪካ ትልቅ የትምህርት እጥረት ይታይ ስለነበር ትምህርት ቤቶች ተቋቋሙ::

## የመጀመሪያው መስፋፋት

አብዛኛው የሚሲዮን ሥራ የሚሠራው በምሥራቃዊ የትራንስቫልና ጆሃንስበርግ የወርቅ ቁፋሮ አካባቢ ዎች ነበር:: ለዚህም ምክንያቱ ሠራተኞቹ

ከደቡብ አፍሪካ አካባቢዎች ሁሉ ወደነዚህ ማዕከላት መምጣታቸው ነበር። ሬቨረንድ ጄ.ኤፍ.አር. ፔንና ባለቤታቸው የናዛሪን ሥራ ለማካሄድ ወደ ሳቢ ሄዱ። የማዕድን ቁፋሮው በዚያ ቦታ ሲጠናቀቅ የወንጌል ሥራው ሰዎች ወደሚኖሩበት አኮርንሆክ ወደሚገኘው ሎውቨልድ ይዛወራል። ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ ደህንነትን በማግኘታቸው ወንጌሉን ለማስራጨት ወደ አካባቢያቸው ተመልሰዋል። በ1925 ሪቨረንድ ሲ.ኤስ.ጄንኪንስና ባለቤታቸው ወደ ሞዛምቢክ ሄደው እነዚህን ሰዎችና የቤተክርስቲያንን ምሥረታ እንዲያግዙ ተጠየቁ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህ አዲሱ ሥራ በፍጥነት እያደገ በመሄዱ፣ በአፍሪካ ከሚገኙ ታላላቅ አብያተክርስቲያናት አንዱ ለመሆን በቃ።

በ1939 የተከሰተው ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ውድቀትና ጦርነት የወንጌሉ ግስጋሴ በእጅጉ አዝጋሚ እንዲሆን አደረገው። በነዚህ ዓመታት ውስጥ የቤተክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ጥንካሬ ጨምሯል። የገንዘቡ ፍሰት ሲቆም የአገር ልጆች የሆኑት መጋቢዎች ምእመኖቻቸውን ጥለው አልሄዱም። ሚሲዮናውያን አነስተኛ ደመወዛቸውን ከአገሬው ነዋሪ ወንድሞች ጋር ተካፈሉ። በዚህም እንቅስቃሴ አማካኝነት ለታላቅ የወንጌል መስፋፋት መሠረት ተጣለ።

## ሁለተኛው መስፋፋት

በ1948 መንፈሳዊ ትጋት የነበራት የናዛሪን ቤተክርስቲያን ከገደቧ አልፋ ወጣች። ይህም ሁኔታ ለአሥራ አምስት ዓመታት ቀጥሏል። ጥቁሮችና ነጮች በአንድነት ወንጌሉን ወደ ህዝቦች ለመውሰድ ተባበሩ። ሥራው የተጀመረው በጸሎት ነበር። በ1943 ዓላማዎች ተነድፈው የቤተክርስቲያኒቱ ምእመናን በሙሉ በጸሎት እንዲንቀሳቀሱ ተደረገ። እግዚአብሔርም ይህንን ጸሎት በሚያስደንቅ ሁኔታ መለሰው። የበላይ ሃላፊ በሆኑት ዊሊያም ሲ. ኤሰልስቲን መሪነት አብያተክርስቲያናት ከማላዊና ዛምቢያ እስከ ኬፕ ፖይንት ድረስ ሊቋቋሙ ቻሉ። በ1948 ሬቨረንድ ቻርልስ ኤች. ስትሪክላንድ በአውሮፓውያን መካከል ቤተክርስቲያንን ለመመሥት እዚያው ደረሱ። ለዚህም ተግባር የጥቁሮች ቤተክርስቲያን ስትጸልይ ነበር።

በዚያው ዓመት (1948) ጥቁሮችን፣ ነጮችንና ህንዶችን የሚያገለግሉ አራት ቀጠናዎች በጆሃንስበርግ፣ ደርባን፣ በፖርት ኤልሳቤትና በኬፕ ታውን ተመሠረቱ። ደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ እስራት ከመፈታቷና ብዙ ቀጠናዎች በአንድነት ከመዋሃዳቸው በፊት፣ እነዚህ አራት ቀጠናዎች በአገሪቱ ውስጥ በፍጥነት የሚያድጉ ታላላቅ ድረጅቶች ነበሩ። የስዋዚ መጋቢያን በፍጥነት እያደጉ ወደሚገኙ የደቡብ አፍሪካ ከተሞች እንዲሄዱ የቀረበላቸውን ጥሪ በመቀበላቸው በጆሃንስበርግ አካባቢ የመጀመሪያዎቹ የጥቁሮችና የቅልቅል ህዝቦች ቀጠናዎች ተቋቋሙ።

የአፍሪካ መሪዎቻችን ወንጌሉ ላልደረሰባቸው የገጠር አካባቢዎች ሸክም ይሰማቸው ነበር፡፡ በመሆኑም በሰሜን ትራንስቫዓል የፔዲ ህዘቦች፣ እንዲሁም በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ትራንስቫዓል ገበሬዎች መካከል ወንጌልን የማሠራጨቱ ሥራ ተጀመረ፡፡ ለዚሁ ሥራ መሳካት የስዋዚላንድና የምሥራቃዊ ትራንስቫዓል ህዝቦች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን፣ በዚሁ ምክንያት የሰሜን ትራንስቫዓሏ ብሉበርግ «ትንሽዋ ስዋዚላንድ» እስከመባል ደረሰች፡፡

ዓለምአቀፍ የቅድስና ሚሲዮን በ1952 ከቤተክርስቲያኒቱ ጋር ተቀላቀለ፡፡ ይህም የቤተክርስቲያኒቱን ብርታት በመጨመሩ በደቡብ አፍሪካ ሰሜናዊና ምሥራቃዊ ክፍሎችና በሞዛምቢክ አዳዲስ ቀጠናዎች ተመሠረቱ፡፡ በፍራንኮንጎ፣ ሰሜናዊ ሞዛምቢክ የነበረችው አነስተኛ የሚሲዮን ጣቢያ የቤተክርስቲያኒቱ ትኩረት ወደ ማዕከላዊ አፍሪካ እንዲሳብ በማድረግ ግዙፍ ሚና ተጫውታለች፡፡

የፍራንኮንጎን ሥራ ለመደገፍ ሲባል በ1956 ማላዊ ተጨመረች፡፡ አሁንም ከስዋዚላንድና ምፑማላንጋ የተውጣጡ ሚሲዮናውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች በማስተማርና የመጋቢነትን አገልግሎት በመስጠት አብያተክርስቲያናቱን አገልግለዋል፡፡ ይህም በ1996 አራት በፍጥነት የሚያድጉ ቀጠናዎች እንዲገኙ ለማድረግ ችሏል፡፡ በ1958 ቤተክርስቲያን ከማላዊ ወደ ዛምቢያና ዚምባቡዌ ተስራጨች፡፡ በነዚህ ስፍራዎችም የአካባቢው ሚሲዮናውያን አብያተክርስቲያናትን በመትከሉና ቀጠናዎችን በመመሥረቱ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በ1965 አሮጌዎቹ የአስተዳደር መዋቅሮች ብቁዎች ሆነው ባለመገኘታቸው የሽግግር ወቅት አስፈለገ፡፡ ዶ/ር ዊሊያም ኤስልስቲን ጡረታ ሲወጡ ማዕከላዊው አስተዳደር ፈርሶ ለሥራው እንቅስቃሴ የሚያግዙ አያሌ ቢሮዎች ተከፈቱ፡፡ በዚህም ምክንያት የወንጌል መስፋፋት ከአሥር ለሚበልጡ ዓመታት ተቋረጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ቀጠናዎች ስታቋቁም ቆየች፡፡

## ሦስተኛው መስፋፋት

በምዕራፉ መጀመሪያ ላይ የተገለጸው አካባቢያዊ መዋቅር በ1980 ተግባራዊ ሆነ፡፡ ይህም በአፍሪካ ውስጥ አዲስ መስፋፋትን አስከተለ፡፡ በዶ/ር ሪቻርድ ዛነር ጠንካራ መሪነት የቤተክርስቲያኒቱ ራእይ ሰፊ መስክ ወደመመልከቱ የላቀ ደረጃ ደረሰ፡፡ በዚህ ጊዜ አፍሪካ ለመከር ተዘጋጅታ ስለነበር ራእዩ ወቅታዊ ነበር፡፡ በቀጣይ አሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ ቤተክርስቲያን አዳዲስ አካባቢዎችን ባካለለች ቁጥር የምእመናኑ ቁጥር በእጥፍ ማደጉን ቀጠለ፡፡ ይህም በ1980 22,525 የነበረው የምእመናን ቁጥር በ1996 ከ150,000 እንዲልቅ አድርጎታል፡፡ ከአፍሪካ አህጉር አሳዛኝ ድህነትና የብዙ

አገሮች መለያ ከሆነው ጦርነት ባሻገር፣ የቤተክርስቲያኒቱ የገቢ መጠንም እያደገ ሊሄድ ቻለ።
ቦትስዋና እና ናሚቢያ የወንጌሉ ሥራ ከሚካሄድበት ስፍራ ተጎራብተው የሚገኙ በመሆናቸው ቀጣዮቹ ዒላማዎች ሆኑ። ከነዚህ አገሮች የተገኘው ምላሽ ቅጽበታዊ ባይሆንም፣ አሁን እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል። በሰሜን በኩል ቀደም ሲል ወንጌልን የሰበከንባት ኬንያ በሚያስደንቅ ፍጥነት ለማደግ በቅታለች። የወንጌሉ አዝመራ ከኬንያ ወደ ዩጋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ኢትዮጵያ፣ ሩዋንዳ እና ዛየር ተስፋፍቷል።
ምዕራብ አፍሪካ አስገራሚ ፈተና የተጋፈጥንበት አካባቢ ነበር። ቀደም ሲል በኬፕ ቨርደ ጠንካራ የወንጌል አገልግሎት ስናካሂድ የቆየን ስንሆን፣ በናይጀሪያ የናዛሪን ማህበረምእመናን ማግኘታችን በዚያች አገር የወንጌል ሥራዎችን እንድንከፍት አስችሎናል። ብዙ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛቶች የነበሩ አገሮች (ፍራንኮፎን) ገና ያልተነኩ ሲሆን፣ አንድ ቡድን ከፈረንሳይ ወደ ኮትዲቯር ተላከ። ይህ ሥራ መልካም ውጤት በማሳየቱ በአሁኑ ጊዜ በነዚህ አገሮች፣ በጋናና በላይቤሪያ ጠንካራ ሥራ በመሠራት ላይ ይገኛል። በሴኔጋልም ጥሩ መሠረት ተጥሏል።
የፈተኞቹ ማዕከላዊ፣ ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የአገልግሎት መስኮችም ዳርቻቸውን አስፍተዋል። ወደ ሌሶቶ፣ አንጎላና ማዳጋስካርም መግባት ተችሏል። በተለይ ከማዳጋስካር የተገኘው ውጤት የሚያበረታታ ነበር። እግዚአብሔር አሁንም በክልላችን እየሠራ ነው።

# ምዕራፍ 11
# ናዛሪኖች አብረው ይሠራሉ

## ቤተክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካል

ክርስቶስ በዚህች ምድር ላይ የሚያከናውነው ተግባር አለው:: እኛም የርሱ አካላት እንደመሆናችንን ይኸው ተግባር የሚከናወነው በኛው ነው:: ይህንኑም ተግባር ጠቅላላዎቹ የአካሉ ክፍሎች አብረው ማከናወናቸው ወሳኝ ነው:: ለዚህም ግንኙነቶችንና ሃላፊነቶችን፣ ደንቦችንና ዓላማዎችን በግልጽ የሚያሳይ መዋቅር ያስፈልገናል:: የናዛሪን ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ ይህንኑ መምሪያ ይሰጠናል::

## የናዛሪን ቤተክርስቲያን መዋቅር

በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ አራት የሥራ ደረጃዎች አሉ:: የመጀመሪያውን የአጥቢያ ደረጃ ብለን እንጠራዋለን:: ይህም ማህበረምመኑንና በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያከናውነውን ተግባር የሚያሳይ ነው:: ይህ በክርስቶስ ሥራ ውስጥ ግንባር ቀደም ነው:: ይህ የክርስቶስን ሥራ ለማከናወን ዋንኛው የትኩረት ማረፊያ ነው::

ሁለተኛው ቀጠና ነው:: ይህም አጥቢያ አብያተክርስቲያናት በቤተክርስቲያን ተከላ፣ የወንጌል ስርጭትና በአቅራቢያቸው ለሚገኙ ወንጌል ያልደረሰባቸው አካባቢዎች የርህራሄ ተግባራትን ለመፈጸም ሲሉ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉበትና የሚበረታቱበት ማህበር ነው::

ቀጠናዎች ለትምህርታዊ ወይም አስተዳደራዊ ዓላማዎች ሲባል በክልሎች ሊዋቀሩ ይችላሉ:: በአሁኑ ጊዜ ክልሎች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ለአስተዳደራዊ ዓላማዎች በሚገባ የተደራጁ ሲሆኑ፣ ቀደም ሲል ቤተክርስቲያን በተጠናከረችባቸው አካባቢዎች ግን ክልሎች የትምህርት ቀጠናዎችን አዋቅረዋል::

አራተኛው ደረጃ ጠቅላላ ቤተክርስቲያን በመባል ይታወቃል:: ቀጠናዎች ተሰባስበው ጠቅላላ ጉባኤን በመመሥረት በአመራር፣ ደንቦች፣ አስተዳደርና የእምነት አንቀጾች ላይ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ:: የቤተክርስቲያኒቱ የሚሲዮን አገልግሎቶችና እንደ ጡረታ፣ ሥነጽሑፍ፣ የቤተክርስቲያን ትምህርት ቤቶች፣ የወንጌል ስርጭትና ሬድዮን የመሳሰሉት የቀጠናዎችና የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ከጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ ናቸው:: የጠቅላላ ጉባኤ ዓለምአቀፍ ማዕከል የሚገኘው ካንሳስ ከተማ፣ ሚዙሪ፣ አሜሪካ ሲሆን፣ ክልላዊ ቢሮዎች በዓለም አካባቢ በተለያዩ ስልታዊ ማዕከላት ይገኛሉ:: የአፍሪካ ክልል የጠቅላላ ጉባኤ ቢሮ በሩድፑርት፣ ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ይገኛል::

## ጠቅላላ ቤተክርስቲያን

ጠቅላላ ቤተክርስቲያን ሦስት ክፍሎች አሏት:: እነዚህም ጠቅላላ ጉባኤ፣ ጠቅላላ ቦርድና የጠቅላይ (የበላይ) ሃላፊዎች ቦርድ ናቸው::

ጠቅላላ ጉባኤ ከዓለምአቀፍ የናዛሪን ቤተክርስቲያን ቀጠናዎች የተውጣጡ ልዑካን ስብስብ ነው:: ጠቅላላ ጉባኤ የናዛሪን ቤተክርስቲያን ትልቁ ህጋዊ አካል ሲሆን፣ በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ይሰባሰባል:: የጉባኤው ልዑካን ያልሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ለታዛቢነትና በበዓሉ አከባበር ላይ በሚቀርቡ ዝግጅቶች ላይ ለመሳተፍ ከስፍራው ይገኛሉ:: ከጠቅላላ ጉባኤው ልዑካን መካከል ግማሾቹ አገልጋዮች ያልሆኑ ምእመናን፣ ግማሾቹ ደግሞ አገልጋዮች መሆን አለባቸው:: አንዳንድ የጠቅላላ ቤተክርስቲያን መሪዎች የዚህ ጉባኤ አባላት ናቸው::

የጉባኤው ዋንኛ ተግባር የቤተክርስቲያኒቱን የበላይ ሃላፊዎች፣ የጠቅላላ ቦርድ አባላትን፣ እንዲሁም ጠቅላላ ቤተክርስቲያንን የሚያገለግሉትን ሌሎች ቦርዶችና አገልጋዮችን መምረጥ ነው:: በተጨማሪም፣ ጠቅላላ ጉባኤው የተለያዩ አካላትና ቀጠናዎች ለውሳኔ ያቀረቧቸውን የፖሊሲና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያዎችን አይቶ ውሳኔዎችን ይሰጣል::

የበላይ ሃላፊዎች ቦርድ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ ስድስት ሽማግሌዎች የሚገኙበት አካል ነው:: እነዚህ አገልጋዮች በዓለምአቀፍ ደረጃ የናዛሪን ቤተክርስቲያንን ይቆጣጠራሉ:: ዓበይት ኮሚቴዎችን፣ ቦርዶችንና የቤተክርስቲያን የአገልግሎት ክፍሎችን ይመለከታሉ:: የቀጠና ጉባኤዎችን ሊቀመንበሮች ይሾማሉ:: ምናልባትም የነዚህ ወገኖች ትልቁ ተግባር የቀጠና ጉባኤዎች ለሽምግልና ወይም ዲቁና ያቀረቧቸውን ሰዎች መሾም ይሆናል::

ጠቅላላ ቦርድ በእኩል ቁጥር ከሽማግሌዎችና ከምእመናን በተውጣጡ ሰዎች የሚመሠረት ሲሆን፣ የሚመራውም በበላይ ሃላፊዎች ነው:: ይህ አካል በጠቅላላ ጉባኤዎች መካከል የቤተክርስቲያን ፖሊሲን የማውጣት ሃላፊነት አለበት:: ጠቅላላ ቦርድ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ ሲሆን፣ ፖሊሲዎቹ በዓለምአቀፍ ማዕከል አማካኝነት ተፈጻሚነትን ያገኛሉ:: ጠቅላላ ጉባኤ ይህንን ክፍል በማደራጀት በጀታቸውን ይቆጣጠራል:: ይህ ክፍል በሥራ ቡድኖች (ዲፓርትሜንቶች) የተከፋፈለ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ቡድን ሃላፊነቱን ለሰጡት የአገልግሎት ክፍሎች ፖሊሲን ያወጣል:: የአገልግሎት ክፍሎች የሚባሉት የቤተክርስቲያን ዕድገት፣ የዓለም የሚሲዮን አገልግሎት፣ ገንዘብ፣ ተግባቦት (Communication)፣ ናዛሪን አሳታሚ ድርጅት፣ ዓለምአቀፍ የትምህርት ቦርድና የሰንበት ትምህርት አገልግሎቶች ናቸው::

ዓለምአቀፍ ማዕከል የበላይ ሃላፊዎችን፣ ጠቅላላ ቦርድንና የጠቅላላ ቤተክርስቲያንን መሪዎች የሚያገለግል ክፍል ነው:: ዓለምአቀፍ ማዕከል ከላይ በተዘረዘሩት የአገልግሎት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን፣ እያንዳንዱ የራሱ ዳይሬክተር አለው:: የዓለም የሚሲዮን ክፍል በዓለምአቀፍ ደረጃ

ወደ 600 ሚሲዮናውያንን የሚያካትትና የቤተእምነቱን የወንጌል ስርጭት የሚደግፍ በመሆኑ ከአገልግሎት ክፍሎች ሁሉ ትልቁ ነው።
ክልል የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው። የአፍሪካ ክልል ክልላዊነት ስለተስፋፋበት ሁኔታ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። እነዚህ አብያተክርስቲያናት የጠቅላላ ዋና ጽ/ቤቶች ቅርንጫፎች ሲሆኑ፣ ለአፍሪካ አብያተክርስቲያናትና ቀጠናዎች ጠቅላላ የቤተክርስቲያን አስተዳደሮችንና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። እነዚህ ቢሮዎች በዋና ጽ/ቤቶችም የዓለም የሚሲዮን ክፍል ቅርንጫፎች ናቸው።

## ቀጠና

የናዛሬን ቤተክርስቲያን ቀጠና ሦስት ክፍሎች አሉት። እነዚህም የቀጠና ጉባኤ፣ የቀጠና የበላይ ሃላፊና የቀጠና ቦርዶች ናቸው። በዚህ ክፍል መደበኛ ቀጠናዎች የሚተዳደሩባቸውን ደንቦች እንገልጻለን። አዳዲስ ቀጠናዎች በአነስተኛ አደረጃጀት ሊጀምሩና የመደበኛነትን ደረጃ በሚይዙበት ጊዜ ሙሉ ዕድገት ሊያገኙ ይችላሉ።
የቀጠና ጉባኤ በቀጠናው ውስጥ ከሚገኙ አብያተክርስቲያናት የተውጣጡ ልዑካን ስለ ቀጠናው ዕድገት የሚቀርበውን ማብራሪያ ለመስማትና ለቀጠናው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማድረግ የሚያካሂዱት ዓመታዊ ስብሰባ ነው። የቀጠናው ዋንኛ ተግባር ወንጌሉን መስበክ እንደሆነ ሁልጊዜም ሊታወስ ይገባል። እያንዳንዷ ቤተክርስቲያን ምእመናንን በልዑካንነት ትመርጣለች። በቀጠናው ውስጥ የምትገኝ አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባላት የሆኑ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናትና ሚሲዮናውያን የጉባኤው አባላት ስለሆኑ እንደ ልዑካን ሊናገሩና ድምፅ ሊሰጡ ይችላሉ።
የቀጠና ጉባኤ ዋንኛ ተግባር የቀጠና ሃላፊን መምረጥ ነው። የተለያዩ የቀጠና ቦርዶችን መምረጥ፡ በቤተክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በተደነገገው መሠረት የቀጠናውን ሥራ ማካሄድና በጀት መመደብ ይኖርበታል። ለሰባኪያን፣ መጋቢያን፣ ወንጌላውያንና ላልተሾሙ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች የአገልግሎት ፈቃድ መስጠት የቀጠና ጉባኤ ተግባር ነው። መመዘኛዎችን ሁሉ ያሟሉትንና በተገቢዎቹ ቦርዶች ለጉባኤው የቀረቡትን ሰዎች በሽምግልና ወይም በዲቁና መምረጥ፣ ልዑካንን ለጠቅላላ ጉባኤ መምረጥ እንደዚሁ ሌሎች ተግባራቱ ናቸው።
የቀጠና ቦርዶች። ትልቅ ቀጠና ብዙ ቦርዶችን ሊያዋቅር ይችላል። ሙሉ በሙሉ የተደራጁ ቀጠናዎች ቢያንስ ሁለት ቦርዶችን ማዋቀር አለባቸው። እነዚህም የቀጠና አማካሪ ቦርድና የቀጠና የአገልግሎት ብቃቶች ቦርድ ናቸው። የአማካሪ ቦርዱ ከአገልግሎት ብቃቶች በስተቀር ሁሉንም ቦርዶች ሊያገለግል ይችላል። ይህ ቦርድ ቀጠናውን በማስተዳደሩ በኩል የቀጠና ሃላፊውን የሚረዳ ሲሆን ምእመናንና አገልጋዮች የሚገኙበት ነው።
የአገልግሎት ብቃቶች ቦርድ ሽማግሌዎች ብቻ የሚገኙበት ነው። ይህ ቦርድ የአገልግሎት ሹመትን ወይም ፈቃድን የጠየቀ ክርስቲያን

ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉ ስጦታዎችና ጸጋዎች እንዳሉት፣ ብሎም ለዚሁ ጥሪ በሚገባ መዘጋጀቱን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል::
የቀጠና ሃላፊ በቀጠናው ተግባራት ላይ ሃላፊነት ይኖረዋል:: የሥራ ሃላፊነቱም አገልጋዮችንና አብያተክርስቲያናትን ማማከር፣ መጋቢያንን መሾም ወይም ሹመታቸውን ማጽደቅ፣ ለአዳዲስ አብያተክርስቲያናት ተከላ መመሪያዎችን መስጠትና በቀጠናው ውስጥ የሚገኙትን አብያተክርስቲያናት ማደራጀት፣ እውቅና መስጠትና መቆጣጠር ነው:: ይህ ግለሰብ በራእዩና በትጋቱ ቀጠናውን ወደፊት የሚያንቀሳቅስ መሪ ነው:: ይህ መሪ መጋቢዎቹ ፍሬያማ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል::

## አጥቢያ ቤተክርስቲያን

አጥቢያ ቤተክርስቲያን የቤተእምነታዊ መዋቅር እጅግ አስፈላጊ መዋቅር ነች:: ሌላው ነገር ሁሉ የሚያስፈልገው የአጥቢያ ቤተክርስቲያንን ስኬታማነት ለማረጋገጥ ነው:: አምልኮ፣ ምስጋና፣ ምስክርነትና ትምህርት ተግባራዊ የሚሆነው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው:: ሰውና እግዚአብሔር የሚገናኙትና የደህንነት ሥራ የሚከናወነው በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው:: እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ መጋቢ ትመራለች:: የቤተክርስቲያኒቱ ቦርድ ለመጋቢ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን፣ እንዲህ ዓይነቶቹ ቦርዶች ጠቃሚዎች መሆናቸው እሙን ነው:: ብዙ ቦርዶች ሊኖሩ ይችላሉ:: መጋቢው፣ የተለያዩ ቦርዶችና የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መሪዎች ለዓመታዊ የቤተክርስቲያን ስብሰባ ሪፖርት ያደርጋሉ::
የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች የቤተክርስቲያኒቱን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችሉ ሲሆኑ፣ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይካሄዳሉ:: በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ወቅት ከሚካሄዱት ተግባራት መካከል የመሪዎችና የቦርዶች ምርጫ፣ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ ዕድገት የሚያስረዱ ሪፖርቶች መቅረብና መደመጥ ይጠቀሳሉ:: በቀጠና ጉባኤ ላይ የሚሳተፉ ልዑካንም ይመረጣሉ:: ማህበረምእመኑ የአንድን መጋቢ የአገልግሎት ጥሪ እንዲመረምር ከተፈለገ ልዩ ስብሰባዎች ሊካሄዱ ይችላሉ:: ሁሉም የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ምእመናን በስብሰባው ላይ ድምፅ እንዲሰጡ ሊደረግ ይችላል:: አጥቢያ ቤተክርስቲያኒቱ ያስፈልጉኛል እስካለች ድረስ ብዙ ቦርዶችና ኮሚቴዎች ሊኖሯት ይችላሉ::
የቤተክርስቲያን ቦርድ የሚመራው በመጋቢው ሲሆን፣ የቤተክርስቲያኒቱን ሥራዎች፣ ማለትም ደመወዝ፣ በጀት፣ መሬት፣ ህንጻዎችና የተቀረውን ሁሉ ያስተዳድራል:: የቦርዱ የመጀመሪያው ተግባር ቤተክርስቲያኒቱ እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ዕቅድ መፈጸሟን ማረጋገጥ ነው:: ብዙውን ጊዜ ቦርዱ ንብረትን በሚንከባከቡ ባለአደራዎችና ለአገልግሎቶች፣ ለቤተክርስቲያኒቱ ሠራተኞችና በተለይም ለመጋቢው እንክብካቤ በሚያደርጉ ባለአደራዎች ይከፈላል::

የወንጌል ስርጭትና የቤተክርስቲያን አባልነት ኮሚቴ ስለ ወንጌል ስርጭት መስፋፋትና የወንጌልን ፍሬዎች ጠብቆ ስለማቆየት መጋቢውን ለመምከር የሚያግዝ ሲሆን፣ ሁሉም አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ሊያዋቅሩት የሚገባው ኮሚቴ ነው።
የሰንበት ትምህርት አገልግሎቶች ቦርድ ወይም የትምህርት ቦርድ የአጥቢያ ቤተክርስቲያንን የተለያዩ ምእመናን የክርስቲያናዊ ትምህርቶች ፍላጎቶች ለማሳደግና ለመመሥረት የሚያስችሉትን መርሀግብሮች የመዘርጋት ሃላፊነት ያለው አካል ነው። የሰንበት ትምህርት ቤቶችና የወጣቶች እንቅስቃሴዎች የዚህ ቦርድ ማዕከላት ናቸው።
የናዛሬን የዓለም ሚሲዮን ማህበር በሁሉም ማህበረምእመናን ዘንድ ዓለምን በወንጌል የመድረስ ራእይ ህያው ሆኖ እንዲኖር የሚያደርግ አካል ነው። የማህበሩ ፕሬዚዳንት የቤተክርስቲያን ቦርድና የቀጠና ጉባኤ አባል ነው።
መጋቢ የቤተክርስቲያን ሃላፊ ሲሆን፣ ለቤተክርስቲያኒቱ መንፈሳዊና ቁሳዊ ጉዳዮች ሃላፊነት ይኖረዋል። መጋቢ ህዝቡን በመምራትና በማስተማር ያገለግላል። የእውነትን ቃል ያካፍላቸዋል። መጋቢ ቃሉን በመስበክ፣ መደበኛ ሥርዓቶችን በማካሄድ፣ በመጎብኘት፣ በማማከርና ሰዎችን የቤተክርስቲያን አባላት በማድረግ አገልግሎቱን ያከናውናል። የመንጋውን መንፈሳዊ ፍላጎቶች ያሟላል። አማኞችን ማጥመቅ፣ ለማህበረምእመናኑ የጌታን እራት ማደል፣ የመንጋውን አባላት ለጌታ አሳልፎ መስጠት፣ ማጋባትና የቀብር ሥነሥርዓትን ማስፈጸም የመጋቢ ሃላፊነት ነው።
አጥቢያ ቤተክርስቲያን መጋቢዋን የመንከባከብ ሃላፊነት አለባት። ደመወዝ መክፈል፣ የመኖሪያ ቤትን ማዘጋጀት፣ የጡረታ አበልና ሃላፊነቶቹን ለመወጣት የሚፈልጋቸውን ነገሮች ማሟላት የቤተክርስቲያኒቱ ሃላፊነት ነው። አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን አያሌ መጋቢዎች ሊኖሯት ይችላሉ። የቤተክርስቲያኒቱ የመጋቢያን ቦርድ ቤተክርስቲያኒቱ ባላት ዓቅም ሁሉ ለመጋቢያኑ እንክብካቤ ማድረጓን ይቆጣጠራል። ለመጋቢው የሚሰጠው የደመወዝና የጥቅማቅም መጠን ገደብ የለውም።
የቤተክርስቲያን አባል፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን ትጉ የቤተክርስቲያን አባል መሆን ይጠበቅበታል። እያንዳንዱ ክርስቲያን የክርስቶስ አካልነቱን ተግባራዊ የሚያደርግበትን ስፍራ ማግኘት ይኖርበታል። የመጨረሻው ምዕራፋችን ክርስቲያኖች ሊሳተፉ የሚችሉባቸውን የተለያዩ የአገልግሎት መንገዶች እንደሚከተለው ያቀርባል።

## ምዕራፍ 12
# የቤተክርስቲያን ተልእኮ
## የኢየሱስ ክርስቶስ ትእዛዝ

ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የሚከተለውን ትእዛዝ ሰጥቷል (ማቴዎስ 28:19-20፣ ማርቆስ 16:15፣16፣ ሉቃስ 24:47):

> ደህንነትን ያገኙ ዘንድ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ:: እውነትን ያውቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን መንገድ አስተምሯቸው:: ክርስቶስን ይከተሉ ዘንድ ያመኑትን አጥምቋቸው:: የአካሉ ክፍሎች ሆነው ይጣመሩ ዘንድ አማኞችን አጥምቋቸው:: (ጥቅሶቹ ቃል በቃል አለመወሰዳቸውን አጢን::)

ክርስቶስ ለቤተክርስቲያኑ የሥራ ዕቅድ ሰጥቷል (የሐዋርያት ሥራ 1:8):

> ኢየሩሳሌም- በቅርብህ ላሉት ሰዎች ወንጌልን አካፍል::
> ይሁዳ- ለጎረቤቶችህ ወንጌልን አዳርስ::
> ሰማርያ- የተናቁ ጎረቤቶችህን አትለፋቸው::
> የምድር ዳር- የምሥራቹ ቃል ለሰዎች ሁሉ ነው::

ክርስቶስ ወደ ሌሎች ስፍራዎች ከመሄዳችን በፊት በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ማመን አለባቸው አላለም:: መልእክቱ ለሁሉም እንደሆነና ራእያችን ከራሳችን ማለፍ እንዳለበት በግልጽ አስረድቷል:: ይህን መልእክት ያስተላለፈው ለሐዋርያት ብቻ ሳይሆን ለህዝቡ ሁሉ ነው:: የመመስከሩ ሃላፊነት የሁላችንም ነው::

## የቤተክርስቲያን ዓለምአቀፍ ተልእኮ

የናዛሪን ቤተክርስቲያን ሁልጊዜም ዓለምአቀፍ ተልእኮ ስታካሂድ ቆይታለች:: የናዛሪን ክርስቲያኖች ሁሉ በአጥቢያ ቤተክርስቲያኖቻቸው እግዚአብሔርን ማገልገልና ዓለምን በዓለምአቀፍ ደረጃ በመስበኩ በኩል ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው እናምናለን:: የናዛሪን የዓለም ሚሲዮናዊ ማህበራችን የዓለም አቀፉን ሥራ ከፊታችን በማኖር በንቃት እንድንሳተፍ ይጠይቀናል:: የቅድስናን መልእክት መስማት ያለባቸው ብዙ አገሮች አሉ (ሮሜ 15:20):: የአጥቢያ ቤተክርስቲያን ቦርዶቻችን በአጥቢያዊ ሁኔታ ውስጥ የምናገለግልበትን ማበረታቻና ዕድል መስጠት ይኖርባቸዋል:: ቀጠናዎቻችን ራእዮቻችን ወደ ጎረቤቶቻችንና ከዚያም ርቀው ወደሚገኙ አካባቢዎች እንዲዳረሱ ማገዝ አለባቸው:: ቤተክርስቲያን ሕያው ሆና እንድትኖር የሚያደርጋት እንዲሁ ዓይነቱ ራእይ ነው::

## ለአፍሪካ አህጉር ያለን ራእይ

ከ1996 ጀምሮ በሚከተሉት አገሮች ውስጥ አብያተክርስቲያናት አሉን፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| አንጎላ | ኬንያ ለሴቶ | ሴኔጋል | ዚምባብዌ |
| ቦትስዋና | ላይቤሪያ | ደቡብ | ዛምቢያ |
| ኬፕ ቬርደ | ማዳጋስካር | አፍሪካ | |
| ኮትዲቯር | ማላዊ | ሰዋዚላንድ | |
| ኤርትራ | ሞዛምቢክ | ታንዛኒያ | |
| ኢትዮጵያ | ናሚቢያ | ዩጋንዳ ዛየር | |
| ጋና | ናይጄሪያ | | |
| | ሩዋንዳ | | |

ይህም ከ1946 ጀምሮ አብያተክርስቲያናት በእጥፍ እየተባዙ መሄዳቸውን ያሳያል:: በዚያው ዓመት በ3 አገሮች ውስጥ የነበርን ሲሆን፣ በ1966 በ6 አገሮች፣ በ1986 ይህ ቁጥር በእጥፍ አድጎ በ12 አገሮች ውስጥ ልንሠራ ቻልን:: ባለፉት አሥር ዓመታትም እንደገና ቁጥሩ በእጥፍ አድጎ በ24 አገሮች ውስጥ ልንስፋፋ ችለናል:: ገና ልናዳርሳቸው የሚገቡ 26 አገሮችና ደሴቶች ይቀሩናል:: ይህንን በ10 ተጨማሪ ዓመታት ውስጥ ልናከናውን እንችላለን? አዎን፣ ሁላችንም ተግተን ከሠራን የማይቻልበት ምክንያት የለም::

የሚቀሩን አገሮች የሚከተሉት ናቸው::

| | | | |
|---|---|---|---|
| አሰንሽን | ሪፓብ. | ጊኒ ቢሳው | ሲይሸልስ |
| ቤኒን | ኮሞሮስ ኮንጎ | ማሊ | ሶማሊያ |
| ቡሩንዲ | ሪፓብ. | ሞሪታኒያ | ሱዳን |
| | ጅቡቲ | ሞሪሽየስ | ቶጎ ምዕራብ |
| ቡርክናፋሶ | ኢኩዋ. ጊኒ | ኒጀር | ሰሃራ |
| ካሜሩን | ጋቦን | ሳኦ ቶም | |
| ማዕከላዊ | ጋምቢያ. ጊኒ | ቅድስት | |
| አፍሪካ ቻድ | | ሄሌና | |

## የቤተክርስቲያን የሚሲዮን አገልግሎት እኔን እንዴት ይመለከተኛል?

ክርስቶስ ማህበረሰቤን፣ አገሬ አፍሪካንና ዓለምን በሙሉ በወንጌል የማዳረስ ሃላፊነት እንዳለብኝ ያዛል:: ዓለም በክፉ መሞላቱ ለሁላችንም ግልጽ ነው:: የተረጋጋ ቤተሰብ፣ ታማኝ ማህበረሰብ፣ ፍትሃዊ መንግሥትና ሰላማዊ ዓለም ለመፍጠር የሚያስችል መልስ በእጃችን አለ:: ይህ የተላላነት አሳብ ሳይሆን ሀቅ ነው:: በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይህንን መፍትሄ ለዓለማችን ማስተላለፍ አለብን::

## ምን ልናደርግ እንችላለን?

ልናጤናቸው የሚገቡን አራት ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ፣ እግዚአብሔር እንድሆን የሚፈልገውን ዓይነት ሰው መሆን አለብኝ። ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር እንዳከናውናቸው የሚሰጠኝን ተግባራት መፈጸም አለብኝ። ሦስተኛ፣ እግዚብሔር በሚመራኝ መሠረት መስጠት አለብኝ። አራተኛ፣ እግዚአብሔር ለተለየ አገልግሎት ከጠራኝ መታዘዝ አለብኝ።

### መሆን

እግዚብሔርን በጣም የሚያሳስበው ጉዳይ የእኔ በሥራ መጣደፍ ሳይሆን፣ ባለማቋረጥ መንፈስ ቅዱስ ይበልጥ ክርስቶስን እንዲመስል ይረዳኝ ዘንድ መፍቀድ መቻሌ እንደሆነ ማስታወሱ ወሳኝ ነው። የአገልጋይነትና የታዛዥነት መንፈስ ለክርስቲያን መሠረታዊ አስፈላጊ ነገር ነው። ኩሩ፣ ዕቡይ፣ ወይም መራርና ሌሎችን በመተቸት የተካነ ሰው ለክርስቶስ አካል ደህንነትና ተልዕኮ መልካም አስተዋጽኦ ሊያበረክት አይችልም።

### መፈጸም/ማድረግ

መንፈስ ቅዱስ ለኛ የሚሰጠን ስጦታዎች (ኤፌሶን 4:11-15) በቤተክርስቲያን ውስጥ የትኛውን አገልግሎት ልናካሂድ እንደምንችል ለይተን እንድናውቅ ይረዱናል። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ ፍላጎቶችም ላደርጋቸው የሚገቡኝን ነገሮች ይጠቁሙኛል። ለዚህም ምክንያቱ የቤተክርስቲያንን ፍላጎቶች ለማሟላት የምፈልግ መሆኔ ነው። በዚህ ረገድ ላከናውናቸው የምችላቸው አንዳንድ የአገልግሎት በሮች የሚከተሉት ናቸው።

ማስተማር፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ የማስተማር ስጦታ ያላቸውና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈቅዱ የሰንበት ትምህርትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አገልጋዮች እጅግ ይፈለጋሉ።

የታመሙትን መጎብኘት፡ ብቸኝነትና ህመም ያጠቃቸው፣ ወይም መንፈሳዊ ማበረታቻ የሚፈልጉ ሰዎች ብዙ ናቸው። ለነዚህ ሰዎች የደስታንና የሰላምን በረከት የሚያዳርስ አገልጋይ ማግኘቱ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

ማጽዳትና ማዘጋጀት፡ ይህ ለቤተክርስቲያን በጣም ጠቃሚ አገልግሎት ነው። ይህ ቀላል አገልግሎት አይደለም። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ስም ክብርን የሚያመጣ፣ ለርሱ ያለንን አክብሮት የሚያሳይና ሁሉም ሰው በቤተክርስቲያን ደስ እንዲሰኝ የሚያደርግ ነው።

ጸሎት: ለመሪዎቻችን፣ ለቤተክርስቲያን አገልግሎትና መንፈሳዊና ሥጋዊ ችግሮች ለሚያስጨንቋቸው ሰዎች የመማለድ አገልግሎት ለሌሎች የሚገዳቸው ክርስቲያኖች የሚያከናውኑት ነው። የጸሎት ተዋጊዎች ለቤተክርስቲያን ብርታትን ይሰጣሉ።

እንግዳን መቀበል: ለጎብኝዎች፣ ወዳጅነትን፣ መጠለያን ወይም ምግብን ለሚሹ ወገኖች ልባቸውንና ቤታቸውን ከፍተው የሞቀ አቀባበል የሚያደርጉ ምእመናን ለሁሉም አብያተክርስቲያናት አስፈላጊዎች ናቸው።

የግል የወንጌል ስርጭት: በግል ወንጌልን የማዳረስ ስጦታ ያላቸው ክርስቲያኖች ሌሎችን እንዴት ደቀመዛሙርት እንደሚያደርጉና በወንጌል እንደሚደርሱ መማር አለባቸው። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ለቤተክርስቲያን አገልግሎቶችና ለወንጌል ስርጭት አገልግሎቶች በጣም ጠቃሚዎች ናቸው።

መዝሙር: ጥሩ ዝማሬና የሙዚቃ መሣሪያዎችን መጫወት ታላቅ በረከትን ያመጣል። ይህንን ስጦታ ማግኘቱ ትልቅ ዕድል ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ መዘመር አገልግሎት እንጂ ችሎታን ማሳየት አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ የተባረከ የአገልግሎት አሸንዳ ለመሆን መዘጋጀትንና መጸለይ አስፈላጊ ነው።

ደስታና ሐሤት: ሁሉም ክርስቲያን አመስጋኝ ሊሆን ይገባል። ለሌሎች ደስታን የሚያፈከፍክ ሰው ሁልጊዜም በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ በረከት ነው። የሚያጉረመርም፣ ተቺ መንፈስ አጥፊ ነው። ለቤተክርስቲያኔ ላበረክት ከምችላቸው ታላላቅ አገልግሎቶች አንዱ ሐሤትን እያደረግሁ መመላለስ ነው።

## መስጠት

መንፈስ ቅዱስ ወደ ልግስና የህይወት ዘይቤ ስለሚመራን ናዛሪኖች ለጋሾች ነን። ናዛሪኖች አሥራትንና ምጽዋትን ለጌታ በደስታ እንዲሰጡ እንጠብቃለን። ገንዘባችንን ለቀጠና አገልግሎት፣ ወጣቶቻችንን ለማስተማር፣ ብሎም ለዓለም የወንጌል ስርጭትና የርህራሄ አገልግሎት እናውላለን። የምናዝነው የምንሰጠው ብዙ ገንዘብ ባለመኖሩ ነው።

## ጥሪ መቀበል

እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ ልዩ ሚናዎችን እንድንጫወት ይጠራናል። በእንዲህ ዓይነት ጊዜያት ጥሪውን የሚያቀርበው ራሱ እግዚአብሔር ነው። ቤተክርስቲያን ተጠርቻለሁ ያለው

ግለሰብ ጥሪውን ለማሟላት የሚያስችል ስጦታና ጸጋ እንዳለው ማረጋገጥ አለባት።

## ቤተክርስቲያን እውቅና የምትሰጠው ለየትኞቹ ጥሪዎች ነው?

ለሦስት ጥሪዎች እውቅና እንሰጣለን። እነዚህም ስብከት፣ የድቁናና የሚሲዮን ጥሪዎች ናቸው። የስብከት ጥሪ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብክና አጥቢያ ቤተክርስቲያንን በመጋቢነት እንዲያገለግል የሚቀርብለት ጥሪ ነው። ብቃት ያለው መጋቢ በወንጌላዊነት፣ ወይም በቀጠና ሃላፊነት ወይም በጠቅላላ ሃላፊነት ለማገልገል ሊመረጥ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሽማግሌ ይባላል።

የዲቁና ጥሪ አንድ ሰው በአስተማሪነት ወይም የአጥቢያ ቤተክርስቲያንን መጋቢ በማገዝ ራሱን ለቤተክርስቲያን የሚሰጥበት ነው።

የሚሲዮናዊነት ጥሪ ወንጌሉን ወደ ሌሎች ባህሎችና ስፍራዎች ለመውሰድ ራስን መስጠት ነው። ሚሲዮናውያን ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናት፣ ወይም በርህራሄ አገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ምእመናን ሊሆኑ ይችላሉ።

## እግዚአብሔር እኔን እንደጠራኝ እንዴት ላውቅ እችላለሁ?

የእግዚአብሔርን ጥሪ የሚያሳይ አንድ ቁርጥ ያለ ምልክት የለም። በፊትህ ስላሉት ምርጫዎች ራስህ የምታደርገው ግምገማና ከልብህ የምታምንበት ጉዳይ የጥሪህ አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው። እግዚአብሔር ልዩ ራእይ ወይም ምልክት ሊሰጥ ቢችልም፣ ይህ ግን ሁልጊዜም የሚከሰት አይደለም። ብዙውን ጊዜ ጥሪያችን ጥልቅ ውስጣዊ ግንዛቤያችን ነው። የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ጥሪያችንን በማረጋገጥ ረገድ ጠቃሚ እገዛ ያደርጋሉ።

## እግዚአብሔር በሚጠራኝ ጊዜ እንዴት ምላሽ ልስጠው?

የእግዚአብሔርን ጥሪ መታዘዝና ጥሪውን ለመፈጸም ሕይወቴን አሳልፌ መስጠት አለብኝ። የመጀመሪያው እርምጃ ለመጋቢዬ መናገር ነው። ከዚህ በኋላ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች እሱ ምሪት ይሰጠኛል። የጥሪዬን እውነተኝነት እያሳየሁ በቤተክርስቲያኔ ውስጥ በትጋት መሳተፍ አለብኝ። አጥቢያ ቤተክርስቲያኔ በጥሪዬ እውነተኛነት እምነት አድሮባት ለቀጠና ቦርድ የአገልግሎቶች ብቃት የድጋፍ ደብዳቤ መጻፍ አለባት። ጥሪዬ ሚሲዮናዊ አገልግሎት ከሆነ፣ ከአፍሪካ ክልላዊ ዳይሬክተር ጋር ግንኙነት በማድረግ ከቢሮው ምሪት ማግኘት አለብኝ።

## እግዚአብሔር በሚጠራኝ ጊዜ መዘጋጀት አለብኝ

2ኛ ጢሞቴዎስ 2:15 ተልዕኮአችንን ለመወጣት ራሳችንን ማዘጋጀት እንዳለብን ይናገራል። ለእግዚአብሔር የበለጠ ጠቃሚ የምሆነው የተሻለ ዝግጅት ሳደርግ ነው። ሁሉም መጋቢዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ

ስልጠና እንዲከታተሉ እንመክራቸዋለን:: በተቻለን አቅም ከፍተኛ ስልጠና መስጠት ስላለብን ተገቢው ዝግጅት ከዚህ የበለጠ ስልጠና ሊጠይቅ ይችላል::

እግዚአብሔር ስለሚወደን በተቻለ መጠን የላቀ አስተዋጽኦ እንድናበረክት ይፈልጋል:: እርሱ ከኛ የሚፈልገው ጠንካራና ብርቱ ሰዎች እንድንሆን እንጂ በመንፈሳዊ ህይወታችን እንድንዳከም አይደለም:: በህይወት ዘመናችን ሁሉ እንደሚመራን በመገንዘብ ልንታመንበት እንችላለን::